# ትግላችን

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፣
የማርክሲያዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት፣
የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል
የወዛደር ሊግና
የአብዮት ሰደድ
ፕሮግራሞች፡፡
የአምስቱ ድርጅቶች የጋራ መርሃ ግብር፡፡

---

የመፅሔት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 2

ግንቦት 1969

## ይ ዘ ት


— ፕሮግራሞች፡፡

— የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፣ ---------- 6

— የማርክሲያዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት፣ ---- 22

— የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል --------- 34

— የወዛደር ሊግ ------------------------ 41

— የአብዮት ሰደድ ---------------------- 55

— የአምስቱ ድርጅቶች የጋራ መርሃ ግብር፡፡---- 68

## ፫፬፲_፩፪፻፬

አብዮት ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ አብዮታዊ ፓርቲ ያስፈልጋል:: አብዮታዊ ፓርቲ ከሌለ በማርክሲዝምና በሌኒኒዝም አብዮታዊ ቴዎሪ የተመረከዘና በማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮታዊ ያሰራር ስልት የታነፀ ፓርቲ ከሌለ፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቡችሎቹን ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል ወዛደሩንና ሰፊውን ሕዝብ ወደ ድል መምራት አይቻልም::

ማኦ ትሴ ቱንግ::

የኢትዮጵያ ተራማጆች ከአያሌ ዓመታት ሰፊት ይህንን ሃቅ ተረድተው፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የነፃነት ትግል ለማደራጀትና የተበታተነውን ትግል ሰብስበው ወደ ተጨባጭ አብዮታዊ ሃይል ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: አሁን ባለንበት የትግል ደረጃ፣ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት አብዮት ብሄራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት መሆኑ ከታመነበት ወዲህ የኢትዮጵያ ተራማጆች ሰፊውን ጭቁን ሕዝብ በአንድ አብዮታዊ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ግንባር ለመሰብሰብ፣ እንዲሁም ደግሞ ይህን ግንባር የሚያቋቁሙትን ፓርቲዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች በተለይም የግንባሩን መሪ የወዛደሩን ፓርቲ ለመገንባት ታግለዋል እየታገሉ ናቸው::

በኢትዮጵያችን ከጥቂት አመታት በፊት የተደራጁ ኃይሎች ነበሩ ቢባል፣ አንዳንዱ የብሄረሰቦች የአርነት ግንባሮችና የተማሪው ንቅናቄ ነበር:: አብዮታዊ ምሁራንም በየፊናቸው የጥናት ክበቦች ማቋቋም የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው:: እነዚህ ጥናት ክበቦች ወደ ድርጅት ተለውጠው በማሀላቸው ሰፊ ርዕዮተ ዓለም ትግል ይካሄዱ እንደነበር ዛሬ የማይታበል ሃቅ ነው:: ይሁንናም የየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ በፈነዳበት ሰዓት እነዚህ ድርጅቶች ንቅናቄውን ለመምራትም ሆነ የፈለጉትን አቅጣጫ ለማስያዝ በበቂ ከሕዝቡ ዘንድ ያልተዋሃዱ እንደነበርም ራሱ የየካቲት እንቅስቃሴ ይዘት ያስረዳናል::

የአብዮታዊው እንቅስቃሴ መፋፋም በተለያዩ ድርጅቶች ማሀል የነበረውን የመስመር ትግል ጥርት ብሎ እንዲወጣ አድርጎታል:: ከፊሎም ከጊዜ ወደጊዜ ወደ ፀረ አብዮት ሰፈር ጓዛቸውን ጠቅለው ገብተዋል፣ ኢህአፓ አንዱ ምሳሌ ነው:: ከፊሉ ደግሞ ከተቀጣጠለው አብዮት አያሌ ትምህርቶችን በመቅሰም ስህተቶቻቸውም በማረም፣ የመስመር ጥራትና የአብዮታዊ የትግል ስልት እየተቀዳጁ መጥተዋል:: ስለሆነም ከጊዜ ወደ ጊዜ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እያገኙ የጎከሩና በስለት ማግኘታቸው አልቀረም::



መኢሶን ከነዚህ ድርጅቶች አንዱ ነው:: መኢሶን ከሌሎች ቡድኖች ጋር ባደረገው የመስመር ትግል፣ እንዲሁም በራሱ ውስጥ የሁለት መስመር ትግል በማካሄዱና ከሕዝቡ ጋር አብሮ በመራመዱ ዛሬ ከፍተኛ ድርጅት ሆኗል::

እንዲሁም ደግሞ በትግሉ አፍላ የተወለዱ ሌሎች ድርጅቶች ዛሬ በፀረ-ፊውዳል ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት የትግል መስመር የሚሰለፉ ድርጅቶች ፈልቀዋል:: ከነሱ ውስጥ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል፣ የወዛደር ሊግ፣ የአብዮት ሰደድና ማሌሪድ ይገኛሉ::

አሁን የደረስንበት የትግል ደረጃ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት የምናደርግበት በመሆኑም እነዚህ አምስት ድርጅቶች ለዚሁ ዓላማ በመተባበር የትግል አንድነታቸውን የሚያሰበር መርሃ ግብር አውጥተዋል::

በኛ ግምት የአምስቱ ድርጅቶች መተባበር የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር በሚደረገው ትግል አንዱ ከፍተኛ እርምጃ ነው:: በኢትዮጵያ ሕዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥም ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝ አንጠራጠርም::

ይህ ሆኖ ሳለ ግን የዚህን ትብብር ትክክለኛ ትርጉም መስጠት የአብዮታውያን ግዴታ እንደሆነ ለገረዳ ይገባናል:: በበኩላችን ባምስቱ ድርጅቶች ማሀል የተደረሰውን ስምምነት እንደ አንዱ ትልቅ እርምጃ እንደምንቆጥረው ሁሉ ራሱን የቻለ ግብ አድርገን አናየውም:: የወዛደሩ ፓርቲ የሚፈጠረው ማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድኖች በጠራ መስመር ላይ አንድነታቸውን ሲገነቡና ሲዋሃዱ እንዲሁም ደግሞ በሰፊው ወዛደር ዘንድ ተቀባይነት ሲያገኙ ነው የሚል እምነት አለን::

ስለሆነም ዛሬ የጋራ መርሃ ግብር የፈረሙት አምስት ድርጅቶች የተስማሙባቸውን ነጥቦች በስራ ለመተርጎም በሚያደርጉት ትግል በማሀላቸው ከፍተኛ የርዕዮተ ዓለም ትግል እንደሚኖር አንጠራጠርም:: ከዚህም የርዕዮተ ዓለም ትግል፣ የጠራ መስመር በሚወጣበት ጊዜ፣ በአብዮቱ ሰፈር የሚቆዩ እንዳሉ ሁሉ ከአብዮቱም ሰፈር ሊገለሉ የሚችሉ ይኖሩ ይሆናል:: ይህ በታሪክ የተረጋገጠ የአብዮት ሂደት እንደመሆኑም መጠን በበኩላችን ልንዘጋጅለት ያስፈልጋል እንላለን::

"አብዮታዊት ኢትዮጵያ" ቁ.15 በሚገባ እንዳስቀመጠው "በማንኛውም አብዮታዊ ትግል ወቅት በያለበት ብዙ ቡድኖች ብቅ ብቅ ማለታቸው የተለመደ ነገር ነው ... የአብዮቱ መግፋትና የመደቦች ትግል እየከረረ መሄዱ ያሉትን ቡድኖች ሁሉ እንዲሽጋሸጉ ወይ በአብዮት ሰፈር ወይ በፀረ አብዮት ሰፈር እንዲቆሙ ያስገድዳቸዋል:: ከአብዮቱ መግፋት ጋር የነዚህ ቡድኖች አሰላለፍ መደበላለቁ ይቀርና በአብዮት ወይ በፀረ አብዮት ሰፈር መቆማቸው ለማንም ግልጽ እየሆነ ይሄዳል::" አሁን ባለንበት ደረጃ የማይካድ ሃቅ በኛ አምስቱ ድርጅቶች የተራማጆች ህብረት መሠረትን መጣሉና ወደ ወዛደሩ ፓርቲ መፈጠር እንደምናመራ ነው::

ይህ ፖርቲ የሚመሰረተው በጠራ ማርክሲስት ሌኒኒስት መስመር ላይ በመሆኑም፣ ይህ መስመር የሚፈልቀው የተባሉት ድርጅቶች ለወደፊት በሚያካሄዱት ትግልና በሚኖራቸው አቋም ሰፊ ርዕዮተ ዓለም ትግል ቢደረግ መሆኑን እናምንበታለን:: ማለትም ዛሬ የተጣለው የተራማጅ ቡድኖች ሕብረት መሰረት ለሰፊ የርዕዮተ ዓለም ትግል በር እንደሚከፈት ሁሉ፣ ከዚህ የርዕዮተ ዓለም ትግል የጠራና የተፈተነ ጠንካራ የርዕዮተ ዓለም አንድነት ይፈልቃል ማለት ነው:: ያኔም የወዛደሩ ፖርቲ ለመሰረት ይቻላል::

በኛ ግምት በተለይ ባለፉት ሶስት ዓመታት በተካሄዱት ትግሎች እነዚህ ድርጅቶች ተከበሩና መስመር ይዘው መተዋል:: ሆኖም ግን የአብዮቱ ሂደት ገና ብዙ ፈተና እንደሚቀረው ለደቂቃ አንጠራጠርም::

ለወደፊት ትግል የነዚህ ድርጅቶች አቋም ምን ይሆናል እነዚህ ድርጅቶች በሕዝቡ ዘንድ ይፀናሉ አይፀኑም የሚሉት ጥያቄዎች የድርጅቶቹን አብሮ መሄድ የሚወሰንበት ጊዜ ይመጣል:: ስለዚህም ከሰፊው ሕዝብ ጋር የቆሙት አንድነታቸውን በጠራና በተፈተነ የርዕዮተ ዓለም አንድነት ሲመሰርቱ በሌላም ከወዛደሩ ሲዋሃዱ የወዛደሩን ፖርቲ መፍጠራቸው አይቀርም::

ይህ ሁኔታ ሳይሟላ፣ የወዛደር ፖርቲ ካሁኑ ይቋቋም ቢባል፣ መሰረተ ቢስ የወዛደር ፖርቲ ይሆናል:: ግን ደግሞ ለዚህ ሁኔታ መሟላት አመቺ ሁኔታ ፈጥረዋልና፣ በአምስቱ ድርጅቶች የተፈረመው መርሃ ግብር አንድ ታሪካዊ እርምጃ ነው እንላለን::

ለነዚህ ድርጅቶች ካሁኑ የቀረበላቸው ፈተና የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የፈጠረው አዲስ ሁኔታ አለ::

እንደሚታወቀው፣ በተለይ ከነተፈሪ በንቲ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መክሸፍና ያሜሪካን የስለላና የጦር ወኪሎች የነበሩ አራት ድርጅቶች ከተባረሩ ወዲህ ባገራችን ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ ውርደት ተከናንቧል:: በደርጉ ውስጥም ቢሆን በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ላይ የተደገፉ ፀረ ሕዝቦች እስከነጭራሹ ባይደመሰሱም በሚገባ ተዳክመዋል ለማለት ይቻላል:: ስለሆነም ዛሬ በኢትዮጵያችን የፀረ አብዮት ሰፈር ራሱን ካዲሱ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ላይ ነው:: በደርጉ ውስጥም ቢሆን ያሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ በመታገል እስከተወሰነ ደረጃ ተራማጅ ሚና የተጫወቱ ግለሰቦችም ሆኑ፣ ራሳቸውን ከንዑስ ከበርቴነት ወደ ቢሮክራቲክ ከበርቴነት ለመለወጥ ከመጀመሪያውም ጀምሮ እቅድ የነበራቸው ግለሰቦች ዛሬ ራሳቸውን ከሁኔታው ጋር የማዛመድ አዝማሚያ ይታይባቸዋል::ቢሮክራቲክ ከበርቴውንም ቢሆን ካዲሱ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ እየሞከረ ነው::



የነዚህ አድሃሪ ኃይሎች አላማ ዛሬ ግልጽ ሆኖ በመታየት ላይ ነው:: ቢሮክራሲውን በሚመለከተው በኩል የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 53 ላይ ""በደርጉ ውስጥ ያሉት አድሃሪያት ከተደመሰሱ በኋላ ፖሊሲያቸው ግን ይቀጥል እንጂ በመደቦች ትግል ፋንታ የመደቦች እርቅ እንደገና በመፈክርነት ይቀርብ እንደሆነ እነኚህ በሚመጡት ቀናትና ሳምንታት ውስጥ ለሰፊው ሕዝብ ግልጽ እንደሚሆን እናምናለን::"" የሚል አስተያየት ሰፍሮ ነበር:: በበኩላችን አዝማሚያውን እንዳየነው ምርጫው ወደ ቢሮክራሲው ማጠናከር ያዘነበለ ይመስላል::

ቢሮክራሲውን የማጠናከሩ ፍላጎት ለብቻው የመነጨ አይደለም:: ዛሬ አብዮታችን ተከቦ ባለ የሕዝቡ መታጠቅና መደራጀት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲቀርብ፣ የሰፊውን ሕዝብ መጠናከር እንደጦር የሚፈሩ ንዑስ ከበርቴዎች ከሰፊው ሕዝብ ይልቅ፣ በቢሮክራሲው በሰራዊቱ በውጭ ኃይሎች ዕርዳታ ላይ መመርኮዝን መርጠዋል:: ለነዚህ ሃይሎች እርዳታ ድጋፍ እንጂ መሠረት አይሆንም ፣ ቢሮክራሲው ይደምሰስ እንላቸዋለን::

የውጭ እርዳታን በሚመለከተው በኩል ሃቀኛ ተራማጆች መሠረት አድርገው መያዝ ያለባቸው የኢትዮጵያን አብዮት የሚሠሩት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች መሆናቸውንና እኩሪ ታሪካቸውም እንዳረጋገጠላቸው ብሄራዊ ነፃነታቸውን በምንም አይነት መንገድ እንደማያስደፍሩ ነው::ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ቢሮክራሲው በሚገባ ስላልተመታ ለፀረ አብዮት ሃይሎች ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ ተገን ሆኖ ስለሚቀርብ ካለምንም ማወላወል ዛሬውኑ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ያስፈልጋል::ከዚሁ ጋር ተያይዞ የጊዜው አጣዳፊ ተግባሮች ሆነው የሚቀርቡት:— ተጀምሮ የነበረው የአድሃሪያች የትጥቅ ማስፈታት ዘመቻ መቀጠል፣ የውጭና የውስጥ ጠላቶችን ለመቋቋም ሰፊውን ሕዝብ የማስታጠቅ ተግባር እንዲፋፋምና የታቀደው ዘመቻ በአብዮታዊ አመራር ስር እንዲሆን ማድረግ፣ የተራማጆች ሕብረት እንዲጠነክር ዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ካለ ገደብ እንዲለቀቁ ማድረግ ናቸው::

እንግዲህ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህ ሆኖ ባለ፣ የተራማጅ ድርጅቶች በዚሁ አንፃር የሚኖራቸው አቋም፣ ተራማጅነታቸውን ይወስናል:: ከፍ ብለን አምስቱ ድርጅቶች ከመዋሃዳቸው በፊት ገና ብዙ ፈተና ይኖራቸዋል፣ ሊዋሃዱ የሚችሉት በተባሉት ፈተናዎች የሕዝብ ወገንነታቸውን ሲያስመሰክሩ ነው ስንል፣ በጊዜያዊ የኢትዮጵያ ሁኔታም ሆነ ለወደፊት በሚፈጠሩት ሁኔታዎች እነዚህ ድርጅቶች መፈተን ይኖርባቸዋል ማለታችን ነው::

ለሚቀጥሉትም ወራት ለዚህ ጥያቄ መልስ እንደምናገኝ አንጠራጠርም።
የመጣው ቢመጣ ግን ለአብዮታዊያን ድርጅቶች ለቀረበላቸው ፈተና ብቁ ሆነው አንድነታቸውን በጠንካራና በተፈተነ የርዕዮተ ዓለም አንድነት እንደሚመሠርቱ በሎም የወዛደሩን ፓርቲ እንደሚያቋቁሙ አንጠራጠርም።

ዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለ ገደብ
የተራማጆች አንድነት ይጠንክር
ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል።



## የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ
## ወርሃ-ገበር /ገርገሬዎ/

### ክፍል 1፡ መግቢያ

የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ለዘመናት የተጫነባቸውን የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ቀንበር አሽቀንጥረው ለመጣል ሲተናነቁ በጀግንነት፣በመስዋዕትነትና በደማቸው የፃፉት እጅግ አኩሪ የሆነ የትግል ታሪክ አላቸው።

በተለይም ከሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ወዲህ በአገራችን ላይ የበዘበዙና የጭቆና ድሩን በማደራት የኢትዮጵያን ህዝቦች ኢሰብአዊ በሆነ አገዛዝ ስር አውተብትበና እፍኝ ለመያዝ ያንሰራራው የከፊል ፊውዳል ና የከፊል ካፒታሊስት ስርዓት ማህበር የኢትዮጵያን ህዝቦች በኋላቀርነታቸው፣በድህነታቸው፣በመሃይምነታቸው ከዓለም ህዝቦች መሃል ተወዳዳሪ የሌላቸው አድርጓቸዋል።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ጭቁኖች በመላ ታሪካቸው ባርነትን አሜን ብለው የተቀበሉበት ወቅት በታሪካቸው ገጽ ላይ እንዳለመኖሩ ሁሉ ይህንን ኢሰብአዊ የሆነ የባርነት ቀንበር ሁኔታው በሚጠይቀውና በሚፈቅደው ታታሪነት፣ቆራጥነትና መስዋእትነት እየተቋቋሙና እየተጋፈጡ ታገሉ እንጂ ከባርነት ጋር ተባብረው አልተቀመጡም።

በዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ የኢትዮጵያ ጭቁኖችና ተራማጆች ነፍሳቸውን፣ክብራቸውንና ሀብታቸውን ሳለማስደፈር ከተደነቀ ጀግንነታቸው ሳይቀጠቡ፣ከአድሃሪው ስርዓት ጋር ሲተናነቁ ብዙ ወገኖቻችን በአደባባይ ተረሽነዋል፣በምስጢር ታፍነዋል፣ተጋዘዋል፣ታስረዋል፣ተሰደዋል።ትግሉ ግን እየወደቀ እየተነሳ ወደፊት መገፋቱን ቀጠለ እንጂ አንድም ጊዜ ጋብ አላለም።እርግጥ የተደራጀና ከእግር እስከ ራሱ የታጠቀው የአድሃሪው ስርዓት ሃይል በየተራ በያለበት የሚነሱትን ህዝባዊ አመጾች ለጊዜው ሊቋቋማቸው፣እንደገና ጊዜም ሊያዳፍናቸው ችሏል።ነገር ግን ወደሞ ተደረጁ፣በተለይ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ያደረጉት ትግሎች በከንቱ አልነበረም።ከህዝቡ ትግል፣በህዝቡ ትግል አፍላ ውስጥ ብዙ ግንባር ቀደም ታጋዮች ተወለዱ።እየወደቀ እየተነሳ ወደፊት የሚገሰግሰውን የአብዮት ችቦ ለመረከብ የአዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ ቆራጥ ክንድ ተዘረጋ።ተማሪዎች፣ወጣት ላብአደሮችና ተራማጆች ፋሽስታዊውን የሃይለሥላሴ አገዛዝ ለመጣል በግንባር ቀደምነት ተሰለፉ።

ይህ ታሪካዊ ተጋድሎ ያስከተለውና ያፈራው ሕዝባዊ ንቅናቄ፣በተለይ ከየካቲት ወር 1966 ዓ.ም እንስቶ፣ኢትዮጵያን በታሪኳ አብዮታዊ ማእበል ውስጥ ከቷታል።ይህ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውጣ ውረድ በፈራረቁበት፣በጣም ፍጡን በሆነ እርምጃ በመካሄድ ላይ ነው።የተጀመረው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ትክክለኛ መሥመር በመከተል ወደፊት ገፍቶ ግቡን እንዲመታ ተራማጆች ሁሉ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ማንኛውም አብዮታዊ ንቅናቄ ከግቡ ለመድረስ እንዲችል በርካታ ዋና ነገሮችን አሟልቶ መያዝ አለበት።በመጀመሪያ ደረጃ ንቅናቄው በአብዮታዊ ርእዮተ-ዓለም መመራት አለበት።ቀጥሎ፣በዚሁ ርእዮተ-ዓለም ላይ የተመሠረተና ይህን ርእዮተ-ዓለም የሚያንፀባርቅ፣የንቅናቄውን አቅጣጫ የሚያመለክት፣የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ፕሮግራም መንደፍ ያስፈልጋል።በመጨረሻም፣ይህን ፕሮግራም በትክክልና በቅልጥፍና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለው ድርጅታዊ መዋቅር ሊኖረው ይገባል።

ማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ትግሉን ወደፊት እንዲገፋ፣የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታዎች በጥልቅ መልክ ከሁሉም አንፃር ማጥናት፣በዚሁ ጥናት ላይ የተመረኮዘ ስትራተጂ ማውጣትና የየጊዜውን የትግል ታክቲክ መቀየስ ይኖርበታል።ለዚህ የመጀመሪያው፣ወዳጅና ጠላትን በሚገባ ለይቶ ማወቅ ሲሆን፣በመሃል የሚዋልሉ ክፍሎችን ደግሞ፣በዚያው ቦታቸው እንዲቆሙ ሲሆን፣ወደአብዮት ሃይሎች የሚያዘነብሉበትን መንገድ መፈለግ ነው።ሁለተኛው፣በማናቸውም ጊዜና ቦታ የራስንም ሆነ የጠላትን አቅም በትክክል መመዘን ይጠይቃል።ቀጥሎም፣በየጊዜው ለሚደረገው ትግል ተገቢ ድርጅቶችን ማቋቋምና የትግል መርሆችን ማንገብ ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዋና ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም —በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም— ናቸው።ስለዚህም የኢትዮጵያ አብዮት ፀረ ፊውዳል፣ፀረ ቢሮክራሲያዊ ከበርቴና ፀረ ኢምፔሪያሊስት መሆን አለበት።

እነዚህን ዋና ዋና ጠላቶች የሚቃወሙ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ፣/ከኢትዮጵያ ህዝብ 90 በመቶ የሚሆኑት የዚሁ ወገን ናቸው/ ሃይሎቻቸውን ሁሉ አስተባብረውና ተጋግዘው መታገል አለባቸው።ከየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ጀምሮ የሚካሄደው የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ ሃይሎች ሁሉ ለዚህ የህብረት ትግል አመቺ የሆነ አብዮታዊ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።



ፊውዳሊዝም በመንግሥት ስልጣን ደረጃ በመጠኑ ተደምስሷል።የየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም አዋጅ፣የፊውዳሉ ስርዓት የቆመበትን የመሬት ስሪት አናግቶታል።ሰፊው አርሶ አደር ህዝብ፣ዲሞክራሲያዊ ሃይሎችና አገርወዳጆች ሁሉ፣የየካቲቱ አዋጅ በአብዮታዊ መንገድ በስራ ላይ እንዲውል መራራ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው።በአጠቃላይ ሲታይም፣የፊውዳሉ መደብና ርዝራዦቹ የሚደመሰሱበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

በአሁኑ ወቅት በተለይም ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ተሻርኮ የኢትዮጵያን ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊገታና ሊቀለብስ የሚሞክረው የቢሮ ከበርቴው ነው። የቢሮ ከበርቴው በመደብ አቋም ሆነ በአስተሳሰቡ በልምዱ ከፊውዳሉ መደብና ከትኩቱ ካሳደገው ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሺህ ድሮች የተሳሰረ ነው።በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በበለጠ ለመተሳሰርና በነርሱም እርዳታ አብዮቱን ለመቀልበስ ሸር ጉድ ሲል ይታያል።በሌላ በኩል ደግሞ፣ገና ባልተደመሰሰው የፊውዳል ቢሮክራሲ በመጠቀም አብዮቱን አቅጣጫ ለማሳትና ለመበረዝ በሺህ የሚቆጠሩ ፀረ ህዝብ ድሮችን በመድራት ላይ ይገኛል።የፊውዳሉ መደብና ኢምፔሪያሊስቶች የደርጉን ቀኝ ክንፍና የቢሮ ከበርቴውን አስተባብረውና ወታደሩን ከፍለው አብዮቱን ለመቀልበስ ትልቅ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው።የቢሮ ከበርቴው በበኩሉ፣በኢምፔሪያሊስቶች •ተረድቶና ከፊውዳሉ መደብ ጋር ተቃቅፎ አብዮቱን ለመቀልበስና በስልጣን ላይ ለመንጠልጠል የማይገለብጠው ድንጋይ የለም።

እስካሁን የተካሄደው አብዮታዊ እንቅስቃሴ፣ኢምፔሪያሊዝም —በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም— በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ያሰፈናቸው ልዩ ልዩ ሃይሎች እስከዚህም አልተነኩም።የኢትዮጵያ ህዝቦች ኢምፔሪያሊዝም ከተበተባቸው የፖለቲካ፣የኢኮኖሚ፣የባህልና ወታደራዊ ተጽእኖዎች ለመላቀቅና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነት ለማስከበር ከኢምፔሪያሊዝም ጋር —በተለይም ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር— ረጅም፣መራራና የተወሳሰበ ትግል ማድረግ ይኖርባቸዋል።ለዚህ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግላቸው የጊዜው አለም—አቀፍ ሁኔታ በጣም አመቺ ነው።

የአለም ህዝቦች ሁሉ ዋና ጠላት የሆነው ኢምፔሪያሊዝም ዛሬ በየቦታው እየተጋለጠ፣እየተዋከበና እየተንኮታኮተ ነው።የሶሺያሊስት አገሮች በፖለቲካ፣በኢኮኖሚና በጦር ሃይል በበለጠ እየተጠናከሩ ናቸው።ከአለም ህዝቦች መካከል አንድ ሶስተኛው የሚሆኑት በሶሺያሊስት ስርዓት ስር ይተዳደራሉ።በርከት ያሉ አገሮችና በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች በየአገሩ ወደሶሺያሊዝም ዓለም በመገስገስ ላይ ናቸው።የአፍሪካ፣የእሲያና የደቡብ አሜሪካ ህዝቦች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አምርረውና ክንዳቸውን አጠንክረው በኢምፔሪያሊ

ዝምና በአድሎ—አዘር ቀኝ አገዛዝ ላይ ተነስተዋል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ፣የኢ
ምፔሪያሊስት አገሮች በመላ፣ተደጋግሞ በሚደርስባቸው የኤኮኖሚ ችግር ምክኒ
ያት ተውጥረው ተይዘዋል፡፡በያንዳንዱ የኢምፔሪያሊስት አገር /ሰሜን አሜሪ
ካ፣ምእራብ ጀርመን፣እንግሊዝ፣ኢጣሊያ፣ፈረንሳይ፣ጃፓን.../ በየጊዜው የሚ
ፈነዳው የላብአደሮች ትግልና በመካከላቸው ያለውም የጥቅም ግጭት የኢምፔሪ
ያሊስቶችን ሃይል በበለጠ ያዳከመዋል፡፡

የዘረዘርነው ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ለሚያ
ደርጉት መራራ ትግል ታላቅ ድጋፍ የሚሰጣቸው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡የኢት
ዮጵያ ህዝቦች ብሄራዊ ነፃነታቸውን ለማስከበር ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚያ
ደርጉት ትግል ደግሞ፣ለሰላም፣ለእድገት ለእኩልነት ከቆሙ አገሮችና ከ
ፀረ ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ጋር በበለጠ በኅብር ይተባበራሉ፡፡

ሆኖም በዚህ አመቺ ሁኔታ ላይ የሚገኘውን ትግል በአብዮታዊ ቲዎሪ እያነፁ
ና ከዓለም ህዝቦች የትግል ታሪክም ሆነ ከቀደሙት የኢትዮጵያ ጭቁኖች ተጋ
ድሎ ድሎችና ጉድለቶች ጋር እያገናዘቡ መሥራት ያስፈልጋል፡፡በዚህም ላይ
ያለ አብዮታዊ ድርጅት አብዮት ሊኖር እንደማይችል መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡
ስለሆነም የኢትዮጵያን አብዮት ከግቡ ለማድረስ ካለፉት ትግሎች አስፈላጊ
ትምህርቶችን ከመቅሰምም በላይ የህዝቡን ትግል በአንድ አብዮታዊ ድርጅት
አማካይነት ሰብስቦና አስተባብሮ መምራት አስፈላጊ በመሆኑ አንዳንድ ተራማ
ጅ ኢትዮጵያዊያን ከጥቂት ዓመታት ጀምረው በዚህ በኩል ከፍተኛ ጥረት ማድ
ረግ ጀመሩ፡፡

በዚህም መሠረት እነዚህ ተራማጅ ሃይሎች ፋሽስታዊውን የሃይለ ስላ
ሴ መንግሥት በግንባር ቀደምትነት በያለበት ከመታገል አሰረው በአብዮታዊ
የጥናት ክበቦችና በተናጠል ማርክሲስት ቡድኖች ራሳቸውን በማደራጀት የመጀ
መሪያዎቹን እርምጃዎች መውሰድ ጀመሩ፡፡በነዚህም የተበጣጠረ ግንባር ቀደሞ
ቹ መካከል አስፈላጊ ስለሆነው የርእዮተ—ዓለም አንድነት፣የፕሮግራም ጥራት
ና ይህን ፕሮግራም ከሥራ ላይ ለማዋል ስለሚያስፈልገው ድርጅታዊ መዋቅር
ሰፊና ረጅም ውይይት ከተደረገ በኋላ የእነዚህ ቡድኖች ተወካዮች የመሥረ
ቻ ጉባዔ ላይ "የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ" /መ.ኢ.ሶ.ን/ የተ
ባለው ድርጅት ከጥቂት ዓመታት በፊት በምስጢር ተቋቋመ፡፡

መኢሶን የተቋቋመበት ወቅት በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ቀንበር
ስር ብቻ ሳይሆን በዚያ "የህዝቦች እስር ቤት" በተባለች አገር የሃይ
ለ ስላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ በጭቁን ብሄሮች ላይ መጠን የሌለው አመጽ የሚ
ፈጽምበት ወቅት ነበር፡፡የጭቁን ብሄሮች አብዮታዊያን ለእኩልነት፣ለነፃነትና



ለህልውናቸው እጅግ መራራና ከፍተኛ መስዋእት የሚጠይቅ ትንንቅ የሚያደርጉ
በት ወቅት ነበር፡፡በእንደዚሁ አይነት ጊዜ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን
ብቻ ሳይሆን፣የኢትዮጵያ ጭቁኖች በሙሉ ጠላት የሆነውን የብሄር ትምክህተ
ኝነት በአንድ ሃይል መቃወም፣በተራማጆች መካከል የጠነከረ የትግል አንድነ
ት ለመፍጠር ጠባብ ብሄርተኝነትን መከላከል፣በጠቅላላው በአገሪቱ የሚገኙት
ን ተራማጆች ሰብስቦ ለብሄሮች መብት፣ነፃነትና እኩልነት፣እንደዚሁም በመላ
ኢትዮጵያ አብዮታዊ ለውጥ ለማምጣት፣በበይነብሄራዊ ሶሻሊዝም መርሆች እየተመራ
ሃይልን ማስተባበር አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡ስለሆነም በመላ ኢትዮጵያ ብሄሮ
ች የተወጣጡ አብዮታዊያን ይህን "የመላ ኢትዮጵያ" የሚል መጠሪያ
የተሰጠውን ሶሻሊስት ንቅናቄ መሠረቱ፡፡

መኢሶን የሚመራበት አብዮታዊ ቲዎሪ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ነው፡፡ዘላ
ቂ ዓላማው በኢትዮጵያ ሶሻሊስት ስርዓትን ለመመሥረትና ከዓለም ላብአደሮች
ጋር በመተባበር መደብ—አልባ ህብረተሰብ እንዲመጣ መታገል ነው፡፡

መኢሶን በተቋቋመበት ወቅት በብዛት በአባልነት የያዛቸው አብዮታዊ
ምሁራንን እንጂ በላብ አደሩም ውስጥ ሆነ በጠቅላላው በሰፊው ህዝብ መሃለ
ገብቶ፣ሰፊ ቀስቀሳና የማደራጀት ጥረት አድርጎ፣ለመላ ኢትዮጵያ ጭቁኖች ት
ግል ተገቢውን አመራር የሚሰጥ ድርጅት አልነበረም፡፡ይህንንም በመገንዘብ
ከጅቱ ይልቅ ራሱን "ንቅናቄ" ብሎ ሰየመ፡፡አሁንም ቢሆን፣ምንም እን
ኳን ተጠናክሮና ከላብ አደሩና ከሰፊው ህዝብ ተዋህዶ፣ለትግሉ የተጣራ አመ
ራ ለመስጠት ያደረገው ጥረት ተጋድሎ ብዙ ከፍተኛ ፍሬዎችን ቢያስገኝም፣
አንደኛ በላብአደሩ ውስጥ የመዋሃዱ ዘመቻ ገና ብዙ ተጋድሎ እንደሚቀረው
ለማመልከት፣ሁለተኛ የማርክሲዝም—ሌኒኒዝም ተከታይ ቡድኖች ጋር ሃቀኛ የር
እዮተ—ዓለም ትግል አድርጎ፣ከነሱ ጋር ተዋህዶ፣በተጣራ የፖለቲካ መሥመር
የሚመራና በላብአደሩ መደብ ላይ የተመሠረተ ፓርቲ ለመገንባት ያለውን ፍላ
ጎት ለማመልከት "ንቅናቄ" የሚለውን መጠሪያ ይዞ እንዲቆይ ተደርጓል፡፡

መኢሶን መሠረት መጣል የጀመረው በጨለማው የሃይለ ስላሴ ዘመን ነ
በር፡፡ንቅናቄው ባጭሩ እንዳይቀጭ ከጠላት ዐይን ለመከለል ብዙ ጥንቃቄ
ቢያስፈልገውም አባሎችን በተማሪዎችና በሌሎች ህዝባዊ ንቅናቄዎች ውስጥ በግ
ንባር ቀደምነት እያሰማራ መራራ የሆነ ተጋድሎ አካሂዷል፡፡ብዙ ታጋይ አባ
ሎቹ ታስረዋል፣ተገርፈዋል፣[illegible]፣ተሰደዋል፡፡ዛሬ ንቅናቄያችን ህልው
ናውን በይፋ በሚገለጥበት በዚች ታሪካዊ ሰአት በዚህ ትግል የመጨረሻውን
መስዋእትነት ተቀብለው ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ነፃነት ህይወታቸውን የሰጡትን
ጓዶች በሙሉ በክብር ያስታውሳቸዋል፡፡

የየካቲት 1966 ዓ.ም አብዮታዊ እንቅስቃሴ በፈነዳበት ወቅት መኢሶን የህዝብ ትግል አብዮታዊ መሥመርን ሳይለቅ ወደፊት እንዲገፋ ከመቼውም ይበልጥ የመደራጀቱን ጥረት አፋፋመ::ድርጅታዊ አቋሙን ለወቅቱ እንዲስማማ አድርጎ ካስተካከለና ራሱን ካጠናከረ በኋላ ያለማቋረጥ ህዝቡን በማደራጀት፣በበራሪ ወረቀቶችና በሌሎች በልዩ ልዩ የቅስቀሳ ዘዴዎች ለህዝቡ ትግል አቅጣጫ ለመስጠት ሲታገል ቆየ::ትግሉም እየገፋ ሲሄድ መኢሶን እንደዚሁ እያደገና እየተጠናከረ በመሄዱ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ከአብዮታዊ ቲዎሪ ጋር እያዛመደ ለትግሉ አቅጣጫ የሚሰጥና ጥራት ባለው አቋሙ አወናባጅ የንዑስ ከበርቴ ቡድኖችን እያጋለጠ ሃቀኛ ተራማጆችን የሚሰበስብበት ጋዜጣ በማስፈለጉ "የሰፊው ህዝብ ድምጽ" የተባለውን ነፃ ጋዜጣ ማውጣት ጀመረ::

መኢሶን በአገሪቱ በመላ ስር በመስደድና እየተፋፋመ የሚሄደውን የህዝብን ትግል ገለጻና አጠቃላይ በሆነ ፕሮግራም አካባቢ መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣መኢሶን፣ምሥጢራዊ መዋቅሩን ሳይገልጥ፣ህልውናውንና የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ዝርዝር ፕሮግራሙን እነሆ ዛሬ በይፋ ያስታውቃል::

የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት "የፖለቲካ" ፕሮግራም ዋና ዋና ነጥቦች በአጠቃላይ ስነጋገር መሬትን ለአራሹ መከፋፈል፤ የህብረት እርሻዎችን በሚገባ በማቋቋም፣በማጠናከርና በማስፋፋት ለሰፋፊና ለዘመናዊ የወል እርሻዎች መሠረት መጣል፤ ሰፋፊና ዘመናዊ የመንግሥት እርሻዎችን ማስፋፋት፤ ትላልቅ የንግድና የማምረቻ ድርጅቶችንና የውጭ ንግድን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ማድረግ፤ ለሰርቶአደሩ —ለሰራተኛው— ህዝብ የስራ ዋስትና መስጠት፤ ከኢምፔሪያሊስቶች በዘበዛና ቁጥጥር ነፃ የሆነና በአንድ አጠቃላይ የልማት ፕላን የሚመራ ብሄራዊ ኢኮኖሚ መገንባት፤ ትምህርትንና ህክምናን ለሰፊው ህዝብ ማድረስ፤ብሄሮችን በእኩልነት ማስተባበር፤የጾታዎችን እኩልነት ማረጋገጥ፤ የሰፊውን ህዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበርንና የመሳሰሉትን የያዙ ናቸው::

መኢሶን በዚህ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለእድገት ለሚያደርገው ትግል የሰፊው ህዝብ ቀጥተኛ ህብረት እንዲሁም ድጋፍ እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ ሰፊው ህዝብ በዚህ ፕሮግራም አካባቢ እንዲደራጅ ያሳስባል፣ይጋብዛል::

መኢሶን ለኢትዮጵያ ጭቁኖች የተሟላ ነፃነትና ለሶሻሊዝም ቆሟል:: ለዚህ ዓላማ ከሚታገሉ ሃይሎች ጋር ሁሉ የትግል አንድነት ለመመሥረት እጁን ይዘረጋል::ለቆመለት አላማ ያለ እንዳች ማወላወል በምሥጢር፣በይፋ፣በሁ



ጋዊ መንገድና በህገወጥነት፣ በሰላማዊ መንገድና በአመጽ፣ እንደጊዜውና እንደሁኔታው በሚለዋወጥ ታክቲክ፣ ምንም ጊዜ ምንም ሁኔታ በማይለውጠው ቆራጥነትና ታታሪነት የሚታገሉ አብዮታዊያንን አስተባብሮ ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ነፃነትና እድገት አሰልፎአል:: የኢትዮጵያ ጭቁኖች የሚያደርጉትን የተከታተለ ትግል ከዳር እስከዳር አስተባብሮ፣ የተሟላ አብዮታዊ አመራር ለመስጠት በጭቁን ህዝቦችና በታሪክ ፊት የተቀበለውን አደራ እስከመጨረሻው ይጠብቃል:: ጭቁኖች በትግላቸው እንደሚገፉ፣ በትግል እሳት የተፈተኑት አባሎች አብዮታዊ ግዴታቸውን ከመፈጸም ወደኋላ እንደማይሉ የጠነከረ እምነት አለው::ስለሆነም፣ የወሰደውን ጊዜ ይወስዳል እንጂ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ወደ ነፃነትና ወደ ሶሻሊዝም በሚያደርጉት ጉዞ የመጨረሻው ድል የነሱ እንደሆነ ቅንጣት አንጠራጠርም::

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ለዘለአለም ይኑር::
ድሉ የጭቁን ህዝቦች ነው::

## ክፍል 2: ዓላማ

1. ፀረ ፊውዳል፣ፀረ ቢሮክራሲያዊ ከበርቴ ና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማድረግ ህዝባዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግሥት ማቋቋምና የሶሻሊስት ስርዓተ ማህበር በጠበቀ መሠረት ላይ ለመገንባት የሚያስችሉትንና የሚያሟሉትን የኢኮኖሚ፣የሶሻልና የባህል መሠረቶች መጣል::

2. ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ፀረ ኮሎኒያሊስት፣ፀረ ዘረኛነትና ፀረ ጽዮናዊ ከሆኑ ህዝቦች፣መንግሥታት፣ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር በዓለም አቀፍ ደረጃ በኅብር በመተባበር ለነፃነት፣ለእኩልነት፣ለሰላምና ለእድገት መታገል::

## ክፍል 3: ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

### ሀ/ የመንግሥት አቋም

1. የመንግሥት አቋም በላባአደሩ መደብ ርእዮተአለምና በላባአደሩ ፓርቲ ግንባር ቀደምነት የሚመራ፣በላባአደሩ፣በሰፊው አርሶአደር ህዝብና በተራማጁ የንዑስ ከበርቴ ክንፍ የትግል ህብረት ላይ የተመሠረተ፣ህዝባዊ ፈላጭ ቆራጭነትን የሚያሰፍን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ይሆናል::

2. መንግሥቱም ፊውዳሊዝምን፣ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በመታገል፣ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ እንድትመሠረት የታገሉት ድርጅቶችና ግለሰቦች ሁሉ በየደረጃቸው የሚገኙበትና የሚሳተፉበት ሆኖ ይቋቋማል::

3. የመንግሥቱን ከፍተኛ ስልጣን የሚይዘው መንግሥታዊ አካል በሰፊው ህዝብ በቀጥታና በምስጢር የሚመረጡ የህዝብ ተወካዮች የሚገኙበት ብሄራዊ ሸንጎ ይሆናል:: የብሄራዊ ሸንጎውን አባላት ሥራ በማንኛውም ጊዜ የመረጣቸው ህዝብ ወይም ድርጅት ሊቆጣጠር ይችላል::አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም ሊሽራቸው ይችላል::

4. ሃይማኖት ከመንግሥት ፍጹም የተለየ ይሆናል::መንግሥት ለማንኛውም ሃይማኖት በምንም አይነት እንዳያዳላ ይደረጋል::



### ለ/ አስተዳደር

1. ሰፊው ህዝብ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳደር በሰፊው ህዝብ ድርጅቶች ቁጥጥር ስር የሚሆን ህዝባዊ አስተዳደር በያካባቢው ተቋቁሞ በየደረጃው እንዲያያዝ ይደረጋል::

2. ከፊውዳሊዝም፣ከቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የተሳሰረት ግናቸውም የህዝብ መጨቁ ድርጅቶችና መሳሪያዎች ሁሉ /የፖለቲካ ፖሊስ፣የፀጥታ፣የአፋኝ ጓድ ወዘተ./ከነህገጋታቸው፣ከነደንቦቻቸውና ከነስርዓቶቻቸው ተደምስሰው፣በህዝባዊ ጦር ሰራዊት፣በህዝባዊ የፀጥታ ኮሚቴዎችና በህዝባዊ ፍርድ ሸንጎ ይተካሉ::

3. ፀረ ህዝብ የሆነውን የተገማማ ቢሮክራሲ በማፍረስ ለሰፊው ህዝብ አገልጋይ የሆነ አብዮታዊና ዲሞክራቲክ መንግሥታዊ አስተዳደር ይገነባል::

### ሐ/ የሰፊው ህዝብ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች

1. የሰፊው ህዝብ የንግግር፣የጽሑፍ፣የጋዜጣ፣የመሰብሰብ፣በፖለቲካም ሆነ በሙያ የመደራጀት ነፃነቶች፣የሰላማዊ ሰልፍና ስራ ማቆም መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ተከብረው በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል::

2. የያንዳንዱ ዜጋ ህጋዊ ሰውነት፣የመኖሪያ ቤት ነፃነት፣በሰልክና በመሳሰሉት የግል መገናኛዎች ያለ ቁጥጥር የመገልገልና ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብቶች የተከበሩ ይሆናሉ::

3. ማንኛውም ዜጋ ያሻውን ሃይማኖትና ፍልስፍና ለመከተል ሙሉ ነፃነት ይኖረዋል::አንድ ሰው የአንድ ሃይማኖት ወይም ፍልስፍና ተከታይ በመሆኑ፣ወይንም ማንኛውንም ሃይማኖት የማይከተል በመሆኑ ምንም አይነት በደልና ተጽእኖ አይደርስበትም::

4. በጾታዎች መካከል እንዳችም ልዩነት አይደረግም::በተለይም ሴቶች በፖለቲካ፣በኢኮኖሚ፣በባህልና በማህበራዊ ጉዳዮች የሚኖሯቸው መብቶች በማንኛውም ረገድ ከወንዶች እኩል ይሆናሉ::

5. ለነፃነት፣ለዲሞክራሲ፣ለእኩልነትና ለፍትህ በመታገላቸው የታሰሩትንና የተንገላቱትን ግለሰቦች ሁሉ ነፃ በመልቀቅና አስፈላጊውን የማቴሪያል እርዳታ ሁሉ በመስጠት እንዲቋቋሙ ይደረጋል::

መ/ <u>የብሄረሰቦች መብቶችና ነፃነቶች</u>

1. ብሄረሰቦች /ናሽናሊቲስ/ የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት የታወቀ ይሆናል:: የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አንድነት፣ብሄረሰቦችዋ በአንድነት ለመኖር ባላቸው ፈቃደኝነት ላይና በእኩልነት፣እርስ በርስ በመረዳዳት በሚያገኙት ጥቅም፣በመፈቃቀር፣በወንድማማችነት፣በመከባበርና በመተባበር ላይ የተመሰረተና የተገነባ ይሆናል::

2. እያንዳንዱ ብሄረሰብ የራሱን ታሪክ፣ባህሉና ልምዱ ለማስፋፋት፣በራሱ ቋንቋ ለመጠቀም ሙሉ ነፃነት ይኖረዋል::

ሠ/ <u>ብሄራዊ ነፃነት</u>

1. በአገር ውስጥ ጉዳይ የማንንም የውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት በማስቀረት የአገሪቱ የማይገሰስ ብሄራዊ ክብር በማያወላውል አቋም ይከበራል::

2. የአገሪቱን የማይገሰሱ የብሄራዊ ነፃነት መብቶች በመቃረን ከማናቸውም የውጭ መንግሥት ጋር የተደረጉት ውሎች ይፈርሳሉ::

3. በውጭ ፖሊቲካና ፖሊሲ ረገድ ከማናቸውም የኢምፔሪያሊስት አገሮች ተጽእኖ ነፃ የሆነ የውጭ ፖሊቲካ በመከተል የአገሪቱ እውነተኛ ገለልተኛነት ይከበራል::

4. በአገሪቱ ምድር የማንም መንግሥት ጦር እንዳይሰፍር፣ወይንም የማንም የጦር ጣቢያ እንዳይገነባ ይደረጋል::አገሪቱም የማናቸውም አይነት ወታደራዊ ህብረት አባል አትሆንም::

<u>ክፍል 4</u>: <u>ኤኮኖሚ</u>

1. ያገሪቱ ኤኮኖሚ በማእከላዊ ፕላን መሰረት የሚመራ፣በጠበቀ መሠረት ላይ የሚገነባ፣ነፃና ራሱን የቻለ ይሆናል::

2. የቆረቆዘውንና የተዛባውን ኤኮኖሚ በተሟላ አቋም በማቃናት ሃብታም የሆነች አዲስ ኢትዮጵያ እንድታብብ ማናቸውም ጥረት ይደረጋል::



3. ኢምፔሪያሊስት አገሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሚያደርጉት የኤኮኖሚ ቁጥጥር በመላቀቅ "በራስ መተማመን" በሚለው መርህ መሠረት ብሄራዊ የሆነ የኤኮኖሚ ስርዓት ይገነባል::

4. የገጠርን መሬት የህዝብ ያደረገው የየካቲት 25 ቀን 1967 ዓም አዋጅ በተስተካከለ መንገድ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል:: የአርሶአደሩን ህዝብ ኑሮ ለማሻሻልና ለማደራጀት የህብረት እርሻዎች በተለያዩ ደረጃዎች እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ማናቸውም መንግሥታዊ እርዳታ ይሰጣል::በተጨማሪም የአገሪቱን የእርሻ ምርት ከፍ ለማድረግ፣ ሁኔታው በሚፈቅድባቸው አካባቢዎች ሰፋፊና <u>ዘመናዊ</u> የመንግሥት እርሻዎች እንዲስፋፉ ይደረጋሉ::

5. በኢምፔሪያሊስቶችና በአቀባይ ከበርቴዎች ይዞታና ቁጥጥር ስር የሚገኙት የኤኮኖሚ ድርጅቶች ሁሉ በመንግሥት ተወርሰው የህዝብ ሃብት እንዲሆኑ ይደረጋል::በመንግሥት የተወረሱት የማምረቻ፣የማከፋፈያና የንግድ ድርጅቶችም ሁሉ በመንግሥት ይዞታ ስር እንደሆኑ እንዲቆዩ ይደረጋል::

6. ማናቸውም የውጭ ንግድ በመንግሥት ይዞታና ቁጥጥር ስር እንዲሆንና እንዲስፋፋ ይደረጋል::ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችም የተመረጡ፣ ለአገሪቱ እድገት፣ ለሰፊው ህዝብ ጥቅምና አገልግሎት ተፈላጊነት ያላቸው ብቻ ይሆናሉ::

7. በከተሞችና በገጠር መካከል ያለው የተዛባ የኤኮኖሚ ግንኙነት በአስቸኳይ እንዲወገድና በከተሞችና በገጠር መካከልም የሰመረ ምርት ልውውጥ እንዲደረግ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል::

8. <u>እርሻን መሠረት በማድረግ ጠቅላላውን ኤኮኖሚ የሚያዳብሩና የሚመሩ</u> ታላላቅና መጠነኛ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች በአገሪቱ በመላ በየደረጃው በአስቸኳይ እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ማናቸውም ጥረት ይደረጋል::

9. የእጅ ሥራዎች በህብረት ማህበር እንዲደራጁና ባፋጣኝም ወደ መለስተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲያድጉ መንግሥት ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣል፤ ከፍተኛ ጥረትም ያደርጋል::

10. መካከለኛና አነስተኛ ነጋዴዎችና ብሄራዊ የኢንዱስትሪ ከበርቴዎች፣

መንግሥት በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት፣ ለአገሪቱ እድገት ተገቢ ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

ክፍል 5፡ ባህልና ትምህርት

ሀ/ ባህል

1. የኢምፔሪያሊስት አገሮች የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች መልካም ባህል፣ ልምድና ስነምግባር በማርከስና በማጉደፍ የሚፈጽሙትን የኢምፔሪያሊስት የባህል ወረራ ከኢትዮጵያ ምድር ነቅሎ በማውጣት፣ የህዝቦች የባህል ነፃነት የተከበረ እንዲሆን ይደረጋል።

2. በሳይንሳዊ መደብ ርእዮተ—ዓለም ላይ የተመሠረተ ብሄራዊ ባህልና ትምህርት እንዲስፋፋና እንዲዳብር ይደረጋል።

3. የሰፊው ህዝብ መልካም ባህሎችና ጥሩ ልምዶች እንደተጠበቁና እንደተከበሩ ሆነው እንዲዳብሩ ይደረጋል።

4. የስነጽሁፍ፣ የኪነጥበብ፣ የቲአትር፣ የሙዚቃና የስፖርት ስራዎችና ድርጅቶች ሁሉ ለህብረተሰቡ የባህል እድገት የየበኩላቸውን በበቂ ለማበርከት እንዲችሉ አስፈላጊ የሚሆኑትን እርዳታዎች ሁሉ መንግሥት ይሰጣል።

ለ/ ትምህርት

1. ትምህርት ለአገር እድገት፣ ለሰፊው ህዝብ በለጸገና ደህንነት እንዲሰማማ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂን መስፋፋትና መዳበር በፋጣኝ እንዲያረጋግጥ ሆኖ ይደራጃል።

2. የአገሪቱ ስርዓተ ትምህርት በመዋቅሩና በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ ከማናቸውም የኢምፔሪያሊስት ተጽእኖና በከላ፣ እንዲሁም ከተገማው የፊውዳል አስተሳሰብና አሠራር ነፃ ይሆናል።

3. መማር የያንዳንዱ ዜጋ ብሄራዊ መብት እንደመሆኑ ሁሉ፣ "ነፃ ትምህርት ለሁሉም" በሚለው መርህ መሠረት ትምህርት ቤቶች ከማናቸውም አይነት ክፍያ ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል።



4. እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ሁሉ ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ማጠናቀቃቸው ግዴታ ይሆናል። ይህም ግዴታ በተሟላ አኳያን ከሥራ ላይ እንዲውል በመንደሮችና በቀበሌዎች፣ በትናንሽና በትላልቅ ከተሞች ሁሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በብዛት እንዲቋቋሙ ይደረጋል። በዚህም አገባር የሁለተኛ ደረጃና የቴክኒክ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች እንዲቋቋሙና እንዲዳብሩ ይደረጋል።

5. መሃይምነትን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ ከፍተኛና ተከታታይ የመሰረተ ትምህርት ዘመቻዎች ይደረጋሉ።

6. ትምህርት በየብሄረሰቡ ቋንቋ እንዲሰጥና እንዲስፋፋ ጥረት ይደረጋል።

7. ተማሪዎች በማምረት፣ በመደቦች ትግልና በሳይንሳዊ ምርምር፣ እንዲሁም በየት/ቤቶቻቸው ጠቅላላ አመራር እንዲሳተፉ ይደረጋል።

ክፍል 6፡ ጤና

1. የያንዳንዱ ዜጋ ጤንነት በተሟላ አኳያን መጠበቅ የዜጎች ሁሉ ብሄራዊ መብት እንደመሆኑ መጠን፣ "ነፃ ህክምና ለሁሉም" በሚለው መርህ መሠረት ህክምና ነፃ እንዲሆን ማናቸውም አይነት ጥረት ይደረጋል።

2. ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የህክምና ጣቢያዎችና የመድሃኒት ቤቶች በየቦታው በብዛት እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ይደረጋል።

3. የአገር መድሃኒቶችና የህክምና ዘዴዎች እንዲጠኑ፣ እንዲሻሻሉና በሰፊው በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

4. ተላላፊ በሽታዎችን —አባለዘር፣ ወባ፣ ፈንጣጣ፣...ወዘተ— በአስቸኳይ ለማጥፋት ከፍተኛና ተከታታይ ዘመቻ ይደረጋል።

ክፍል 7፡ ሳይንስና ቴክኖሎጂ

1. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለሰፊው ህዝብ አገልግሎት በሚውልበት መንገድ

ይስፋፋሉ ፣ይደረጋሉ፡፡ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ሰዎችና ድርጅቶች ሁሉ ምርምሮችን በተሟላና በአመቺ አኳኋን ለማከናወን እንዲችሉ ማናቸውም አይነት መንግሥታዊ እርዳታ ይሰጣቸዋል፡፡

2. የአገሪቱ አጅጥበብ —ፋቂነት ፣ ቀጥቃጭነት ፣ ሸክላ ሥራ ፣ ሸማኔነት ፣ ወዘተ— እንዲያድግና እንዲበለጽግ ፣ ለአገሪቱ እድገት እንዲጠቅም በምርምርና በመሰብሰብ ማበረታታት ፣ ተመሳሳይ ሸቀጥ ሸቀጦች ከውጭ እንዳይገቡ መከልከል፡፡

ክፍል 8፡ ለሰብአደሪ ፣ ለቢሮ ሠራተኞችና ለጠቅላላው ሠራተኛ ህዝብ ጥቅሞችና መብቶች ለመንከባከብ

1. ሠርቶ መኖር የያንዳንዱ ዜጋ ብሔራዊ መብት እንደመሆኑ ሁሉ ፣ መንግሥት የሥራ ዋስትና ይሰጣል፡፡

2. "ከያንዳንዱ እንደችሎታው ፣ ለያንዳንዱ እንደስራው" በሚለው መርህ መሠረት የሳብአደሩ መደብና የጠቅላላው ሠራተኛ ህዝብ መደብና ደመወዝ በህግ የተወሰነ ይሆናል፡፡በሰፊው ህዝብ ጥቅም ላይ የተመረኮዘ የሠራተኞች መተዳደሪያ ህግ በአስቸኳይ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

3. ሠራተኛው በቀን ከስምንት /8/ ፣ በሳምንት ከአርባ አምስት /45/ ሰአቶች በላይ እንዲሠራ አይገደድም፡፡

4. እያንዳንዱ ሠራተኛ በሳምንት ውስጥ በተከታታይ ቢያንስ አርባ /40/ ሰአቶች የእረፍት ጊዜ ይኖረዋል ፡፡እንዲሁም በአመት ውስጥ የወር ደምወዙ ተከፍሎት በተከታታይ ከሃያ አንድ /21/ የሥራ ቀኖች ያላነሰ የእረፍት ጊዜ ይኖረዋል፡፡የሠራተኛው ህዝብ የእረፍት ጊዜ እንደአገሪቱ የኤኮኖሚ እድገትና ጥንካሬ በየጊዜው እየጨመረ የሚስተካከል ይሆናል፡፡

5. እያንዳንዱ ሠራተኛ እድሜው ለጡረታ በሚደርስበት ጊዜ ከደምወዙ ከሃምሳ በመቶ /ግማሽ/ የማያንስ የጡረታ አበል እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡ይህ የጡረታ አበል እንደ ቤተሰቡ ስፋትና እንደገቢው ማነስ እየታየ ሊያድግ ይችላል፡፡



6. የሳብአደሩን፣ የመንግሥት ሠራተኞችንና የጠቅላላውን ሠራተኛ ህዝብ የኑሮና የሥራ ቦታ ሁኔታዎች ለማሻሻልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ ከፍተኛ ቁጥጥርና ጥረት ይደረጋል፡፡

7. ሴት ሳባደሮችና ሴት የቢሮ ሠራተኞች ለወሊድ ፣ ደምወዛቸው እንደተከፈላቸው ሆኖ ፣ በተከታታይ ከወሊድ በፊት ለሃያ አንድ /21/ ቀናት ፣ ከወሊድ በኋላ ለአርባ /40/ ቀናት የእረፍትና የመታረሻ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡

8. የሠራተኛ ሴቶችን ችግር ለማቃለል የማዋለጃ ቤቶችና የህፃናት መዋያ ድርጅቶች በየቦታው በብዛት ይቋቋማሉ፡፡ለሠራተኛው ቤተሰብ አስፈላጊ የሆኑት እንክብካቤዎች ሁሉ ይደረጋሉ፡፡

9. የመንግሥት ንብረት የሆኑት የማምረቻ ፣ የማከፋፈያና የንግድ... ድርጅቶች አስተዳደርና አመራር <u>የሳብ አደር ቁጥጥር</u> በሚለው መርህ መሠረት እንዲገነቡና እንዲደረጁ ይደረጋል፡፡

10. የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን የመንግሥት ንብረት ያደረገው የሐምሌ 19 ቀን 1967 ዓ.ም አዋጅ ሳብአደሩንና ጠቅላላውን ሰፊ ህዝብ በሚጠቅም አኳኋን እየተስተካከለ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡እንዲሁም የቤት እጥረትን ለማስወገድ መንግሥት አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፡፡

ክፍል 9፡ መከላከያ

1. ያገሪቱ የውስጥም ሆነ የውጭ ጠላቶችን መከላከያ ሃይል በአብዮታዊ ርዕዮተ—ዓለም በታነፀ ህዝባዊ ጦርሰራዊት ላይ የተመሠረተና የተደራጀ ይሆናል፡፡

2. ጾታ ፣ ዘር ፣ ሃይማኖትና ሙያ ሳይለይ እያንዳንዱ ዜጋ በሥራውና በትምህርት ቦታዎች ሁሉ የጦር ትምህርት እንዲሰጠውና ያለማቋረጥ በየጊዜው የሰፊውን ህዝብ ጥቅምና የአገሪቱን ነፃነት በማስከበር ረገድ ሙሉ ብቃትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

3. የህዝባዊ ጦርሰራዊት አባሎች በሰላም ጊዜ የአገሪቱን እድገት ለማፋጠን ፣ በሰራዊቱና በሰፊው ህዝብ መካከል ግንኙነትና ወዳጅነት ለማጠናከር በሚያስችሉ የምርትና የማከፋፈያ ሥራዎች እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

## ክፍል 10፡ የውጭ ጉዳይ

1. ያገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በታወቁት በአምስቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡እነዚህም ፡- ሀ/ ያገሩን አገር ብሄራዊ ክብርና የግዛት አንድነት ማክበር ፣ ለ/ በጠርነት አለመፈለግ ፣ ሐ/ በሌላው አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ፣ መ/ እኩልነትና የጋራ ጥቅም ፣ ሠ/ እርስ በርስ መከባበርና በሰላም አብሮ መኖር ናቸው፡፡

2. ከማናቸውም አገር ጋር የሚደረገው ግንኙነት በነዚሁ ምርሆች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

3. የኢትዮጵያ ህዝቦች ሙሉ ብሄራዊ ነፃነትና ደህንነት እንዲጠበቅና እንዲከበር ከሚቆሙና ከሚጥሩ አገሮች ጋር ሁሉ ቅርብና የጠበቀ የወዳጅነት ግንኙነቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

4. ከአፍሪካ ፣ ከእስያና ከደቡብ አሜሪካ ተበዝባዥ አገሮች ጋር የተለየ የወዳጅነት ግንኙነት ይገነባል፡፡በተለይም ከጎረቤት አገሮች ጋር መልካምና ቅርብ ግንኙነቶች እንዲገነቡ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

5. የአፍሪካ ፣ የእስያና የደቡብ አሜሪካ ህዝቦች ኢምፔሪያሊዝምን፣ የቅኝ አገዛዝና የእጅ-አዙር ቅኝ አገዛዝን፣ ዘረኝነትንና ጽዮናዊነትን በመቃወም ለሚያካሂዷቸው ብሄራዊ የነፃነት እንቅስቃሴዎች በገቢር ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6. የዓለም ህዝቦች ለሰላም ፣ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚያደርጓቸውን ትግሎች ሙሉ በሙሉ ይደግፋል፡፡

7. የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅቶችን ቻርተሮች በመደገፍ ፣ ድርጅቶቹ የቆሙላቸው መሠረታዊ አላማዎች በገቢር እንዲገለጡ ማናቸውንም ጥረት ያደርጋል፡፡

---



## ያ.ግ.ሉ.ፊ.ዶ.....ፕ.ሮ.ግ.ራ.ም

### መ ግ ቢ ያ

ኢትዮጵያ በታላቅ ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች ጨቋኝ መደቦችና አድሃሪ ኃይሎች ባንድ በኩል፣ ተጨቋኝ መደቦችና ተራማጅ ኃይሎች በሌላ በኩል ከባድ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የታሪክ ግዴታ የሆነው ይህ የመደብ ትግል በየካቲት 66 ፈንድቶ በግልጽ ወጣ እንጂ ውስጥ ለውስጥ ሲካሄድ የነበረ ቅረቀብ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው ለእኩልነታቸውና ለሕልውናቸው ለአያሌ ዘመናት መስዋእትነት የከፈሉበት ትግል አድርገዋል፣ አሁንም በበለጠ ሁኔታ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፣ በዚህ ትግላቸውም ብዙ መከራና ግፍን ተቀብለዋል፡፡- ጭቋኝ መደቦችና አድሃሪ ኃይሎች ምንም እንኳን በድርጅታቸውና በትጥቃቸው ከሰፊው ሕዝብ አይለው በመገኘታቸውና የኃይላቸውን የተበጣጠረና በድርጅት ያልተያያዘውን ግብታዊ ትግል በየጊዜያቱ ለማዳከምና ለማዳፈን ቢሞክሩም ጭቁን መደቦች ከቶውንም ቢሆን በምንም ጊዜና ቦታ የጭቆናውን ሥርዓት በሰላምና በእሽታ ተቀብለው አያውቁም፡፡ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየካቲት 66 ወዲህም ሆነ በፊት እጅግ በጣም አኩሪ የሆነ ሪቮሉሽናዊ የትግል ታሪክ አለው፡፡

በጣም ቅርብ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ እንኳን ብንመለከት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች ጋር ታግለው በ2ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ድል መቀዳጀታቸው የታወቀ ነገር ነው፡፡ ከዚያም ከፋሽስቱ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጋር ያለተቋረጠ ትግል ሲያካሂዱ ቆይተው የጭቆናው ሥርዓት ቁንጮ የሆነውን የዘውዱ አገዛዝ ገርስሰው ጥለዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህም ቢሆን በዚሁ ትግላቸው አያሌ መለስተኛ ድሎች ማግኘታቸውን መካድ የሚፈልጉ የሰፊውን ሕዝብ ታሪካዊ ትግል የሚያንቋሽሹ ብቻ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን ተጀምሯል፡፡ እግቡ ለመድረስም ገና ብዙ ውጣ ውረድ እንደሚቀረው የታመነ ነው፡፡ እስካሁንም ድረስ በሰፊው ሕዝብ ትግል የተገኙት ድሎች ትልቅ ግምት ሊሰጣቸው የሚቻለው ምን ያህል ወደፊት ሊያራምዱት ይችላሉ ከሚለው አንፃር ቢታዩ ብቻ ነው፡፡ አንድ ሪቮሉሽን ግቡን መታ የሚባለው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኃይሎች ከአንዱ መደብ ወደሌላው መደብ ሲዛወሩ በተለይም ደግሞ አዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን በፊውዳሊዝም፣ በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ላይ ድልን ተቀዳጅቶ በወዛደሩ መሪነት የጭቁን መደቦች አምባገነንነት ሥርዓት ሲመሠረት ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ ሥርዓት የሰፈነባት በመሆኑ በመካሄድ ላይ ያለው ሪቮሉሽን አዲሱ ዲሞክራሲዊ ሪቮሉሽን ነው:: ይህም ሪቮሉሽን ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ የሪቮሉሽኑ ባለቤትና ባለድል የሆኑት ጭቁን ሕዝቦች ከመቼውም በበለጠ መንቀሳቀስና መታገል አለባቸው:: የሰፊው ሕዝብ መንቀሳቀስ ማለት የሪቮሉሽኑ ወደፊት መገስገስ ነው ጭቁን ሕዝቦች ተንቀሳቅሰው በሙሉ ኃይል በሪቮሉሽኑ ውስጥ ለመሳተፍ የሚችሉት ንቃት፣ ድርጅትና ትጥቅን ባንድ ላይ አዋህደውና አሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው:: የተደራጀውና የታጠቀው የጨቋኞች ኃይል ከዚህ ውጭ በሆነ ሁኔታ ሊደመሰስ አይችልም::

ሰፊው ሕዝብ የራሱን ሪቮሉሽን በሚገባ አካሄዶ ከታሪካዊ ግቡ ለመድረስ ከፈለገ ጠላቶቹንና ወዳጆቹን ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል:: በተጨማሪም ጊዜአዊ ወዳጆችን ከለየላቸው ከቀንደኛ ጠላቶች ለይቶ ተፃራሪ ኃይሎችን በየተራ ቢገጥም [illegible] ሊያጠቃቸው እንደሚችል ማወቅ የሪቮሉሽሉሽኑን ሂደት ያፋጥነዋል:: በመካሄድ ላይ ባለው የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ቀንደኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ናቸው:: የዚህ ሪቮሉሽን ወዳጆች ወይም ደጋፊዎች ዘጠና በመቶ የሆኑት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ናቸው::በዚህ በሁለት ተፃራሪ ሃይሎች መሃል ያለው ቅራኔ ሊፈታ የሚችለው በአመጽ ብቻ ነው::ከሕብረተሰብ የታሪክ ሂደት አንፃር ስንመለከት ይህ የትግል ሂደት የሚያከትመው በሕብረሰባዊ ሪቮሉሽን አሸናፊነት ነው:: ይህም የሕብረተሰብ የታሪክ እድገት ግዴታ ነው::ሆኖም የራሳቸውን ታሪክ የሚሠሩት ሰዎች ራሳቸው ስለሆኑ፣ የጊዜው መርዘም ወይም ማጠር ሁኔታ የሚወሰነው በሪቮሉሽኑ ሠፈር በሚገኙት ኃይሎች ትጋትና ቆራጥነት ነው::ግለሰቦችና ቡድኖች በታሪክ ሂደት ላይ ያላቸው ተጽእኖ የሚለካው ከዚህ አንፃር ሲታይ ብቻ ነው::

የሪቮሉሽኑን ወዳጆችና ጠላቶች ለይቶ ማወቅ ለሪቮሉሽናዊ ትግል እጅግ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻ በቂ ሊሆን አይችልም:: የሪቮሉሽኑን ደጋፊዎች ኃይልና የጠላትን ኃይል ገምቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው:: በሰፊው ሕዝብ ሠፈር የሚገኙትን ድክመቶች ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት እነዚህ ድክመቶች የሚወገዱበትን መንገድ መሻት የጠላት ደግሞ እንዲባባሱ ማድረግ የሪቮሉሽኑን ግስጋሴ ያፋጥነዋል:: ሪቮሉሽናዊያን የራሳቸውንና የጠላትን የኃይል ሚዛን በሚገምቱ ጊዜ ከስሜታዊነት መራቅ ይኖርባቸዋል::ስሜታዊነት ወደ ሃሳባዊነት ያመራል::የኋለኛው ደግሞ የጭቁኖችን ትግል አደጋ ላይ ይጥለዋል::ስለሆነም የራስን ሃይል ከሚገባው በላይ ማጋነን ደ አጉል ጀብደኝነት እንደሚመራ ሁሉ የጠላትንም ኃይል በዚሁ አንጻር መመልከት ወደ ተስፋ ቆራጭነት ይወስዳል::ሪቮሉሽናዊያን ባጠቃላይ ከሁለቱም ስሜታዊ አቋም መራቅ ይኖርባቸዋል::



ከላይ በጠቀስነው ሣይንሣዊ ሃቅ ብርሃን በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለውን ሪቮሉሽንና በመደቦች መሃከል ያለውን የኃይል ሚዛን ስንመለከት ለተራማጅ ኃይሎች በጣም አመቺ የሆነ ሪቮሉሽናዊ ሁኔታ አለ:: ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ በተካሄደው ትግል ሰፊው ሕዝብ ሊናቁ የማይችሉ ታሪካዊ ድሎችን ተጎናጽፏል:: የተገኙት ድሎች እንደ ሰንሰለት የተያያዙና በዲያሌክቲካዊ መንገድ የተደጋገፉ ወደፊትም ለሚገኙት ድሎች መንደርደሪያና መሠረት የሆኑ ናቸው:: በዚህም ምክንያት ነው ተራማጅ ኃይሎች ለነዚህ በሰፊው ሕዝብ ቆራጥ ትግል ለተገኙት ድሎች ከፍ ያለ ግምት የሚሰጡት::

በሰፊው ሕዝብ ትግል ከተገኙት ድሎች ለምሳሌ ያህል የገጠርን መሬት የሕዝብ ያደረገው አዋጅ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያደረገው አዋጅ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች በመንግሥት መወረስና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን ፕሮግራምና ሌሎችም የሪቮሉሽኑን ኃይሎች ሲያጠናክሩ የፀረ ሕዝቡን ሰፈር አዳክመውታል:: እያንዳንዱ ሪቮሉሽናዊ የመጠን ለውጥ አንዱ እርምጃ ወደፊት ወደ ዓይነት ለውጥ ስለሆነ ለተራማጁ ወገን ብርታትን ለአድሃሪው ወገን ደግሞ ድክምን ስላስከተለና ወደፊትም ስለሚያስከትል አሁንም ለሪቮሉሽኑ አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት እንችላለን::

ቢሆንም ለሰፊው ሕዝብ ሪቮሉሽን አመቺ ሁኔታ አለ ማለት ሪቮሉሽኑ ከአደጋ ነፃ ነው ማለት አይደለም:: እስካሁን ከተገኙት ድሎችና ከረዥም ጊዜ የታሪክ አንፃር ከስትራተጂ አንፃር ስንመለከት የሕዝብ ጠላቶች ደካሞች ናቸው:: መደምሰስና መጥፋታቸው የታሪክ ግዴታ ነው:: ይህ ሲባል ግን አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ስንመለከት ጠላት ተሸንፏል ወይም የኃይል ሚዛን ወደ ሰፊው ሕዝብ አዘንብሏል ማለት አይደለም:: ይህን አቋም መወሰድ ከሣይንሣዊ ትንተና ጋር ከመቃረኑም በላይ በመካሄድ ላይ ባለው ሪቮሉሽን ወንጀል እንደመፈጸም ይቆጠራል:: ምንም እንኳን ምቹ ሪቮሉሽናዊ ሁኔታ ቢኖርም ከዚያም አልፎ በሰፊው ሕዝብ ትግል ከዛ የመጠን ለውጦች ቢገኙም ለመጨረሻው ፍልሚያ የሚያበቁት መሠረታዊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች ገና አልተገኙም::

የሪቮሉሽናዊ ሁኔታ መኖር ብቻ ለሪቮሉሽኑ መሳካት ዋስትና አይሆንም:: በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ ሪቮሉሽን ሊሳካ የሚችለው ባለው ምቹ ሁኔታ ላይ ሕሊናዊ ሁኔታዎች/ / ሲታከሉበት ነው:: ከየካቲት 66 ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው ሕዝባዊ ትግል ገብታዊ ነው:: የዚህ ትግል ዋና ዋና ድክመቶች የንቃት፣ የድርጅትና የትጥቅ አለመሟላት ናቸው፣ ሰፊው ሕዝብ በገብታዊ ትግሉ ብዙ የመጠን ለውጦችን ለማግኘት ቢችልም፣ ጠቅላላ የዓይነት ለውጥ ግን እነዚህን ድክመቶች ሳያስወግድ ከቶ ምንም ቢሆን ሊያገኝ አይችልም:: እነዚህም ድክመቶች ሲወገዱ ብቻ ነው አዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን ግቡን የሚመታው::

እነዚህን ድክመቶች የማስወገዱ ኃላፊነት ታሪክ በመጀመሪያ የጣለው በተራማጅ ኃይሎች ላይ ነው:: ተራማጅ ኃይሎችም ይህንን ታሪካዊ ግዳጃቸውን ለመወጣት የሚችሉት በመጀመሪያ እራሳቸው ሲደራጁ ነው:: በሀገራችን በአሁኑ ጊዜ ታሪክ በጣለባቸው ኃላፊነት ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ ባይገኙም ካለፉት ሁለት ሪቮሉሽናዊ ዓመታት በኋላ ብቅ ብቅ ያሉ ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች አሉ:: ከነዚህም መሃል ዛሬ ማሌሪድ በሚል ስም መለስተኛ ፕሮግራሙን ድርጅታዊ መዋቅሩን በሚስጥር አቆይቶ ለሕዝብ ራሱን ያስተዋወቀው ነው:: ማሌሪድ ከወዛደሩ፣ ከአርሶ አደሩ፣ ከጭቁን ወታደር፣ ከተማሪና ከተራማጅ ምሁር መካከል በተራማጅነታቸውና በታጋይነታቸው ሀገሪቱ ልትፈጥር ከቻለቻቸው ሪቮሉሽናዊያን መካከል የሚገኙትን ያቀፈ ነው:: ማሌሪድ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሲሆን፣ በራሽነትን፣ ከሳሽነትንና ቀኖናዊነትን በሀገር ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ሳያወላውል በቆራጥነት ይታገላል:: ማሌሪድ ወዛደራዊ ኢንተርናሽናሊስት እንደመሆኑ መጠን የብሔር ትምክህተኛነትን ይታገላል፣ ጠባብ ብሔረተኝነትንም ይከላከላል:: ማሌሪድ በልዩ ልዩ የትግል መስኮች በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭም ሲታገሉ በነበሩት ማርክሲስቶች-ሌኒኒስቶች በሚስጥር ከተቋቋመ በኋላ ያልተያያዘውንና ግብታዊ የሆነውን ሕዝባዊውን ትግል ለማቀናበር ይታገል ዘንድ ተራማጅ ግለሰቦችንና ማርክሳዊ ሌኒናዊ የጥናት ቡድኖችን በማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው በዚህ ረገድ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከፍ ያለ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል:: ዛሬ ከብዙ ትግል በኋላ ይህ ድርጅት የአሰራር ዘርፉን በመላ ሀገሪቱ ዘርግቷል:: በአድሃሪያንና በአናርኪ-ፋሽስቶች ላይ ከተሰለፉት ኃይሎች ጎን ለጎን ሆኖ ባደረገው ትግል በተገኙት ድሎች የሰፊውን ሕዝብ ሰፈር ድክመቶች በመጠኑም ቢሆን ሲያቃልል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአድሃሪያንን ሠፈር ድክመቶች አባብሷል:: ማሌሪድ ተራማጅ ግለሰቦችንና ማርክሳዊ ሌኒናዊ የጥናት ክበቦችን ለመሰብሰብና ለማደራጀት ሪቮሉሽን በተባለው ጋዜጣው ሲጠቀም ቆይቷል:: ከጥቂት ጊዜ ወዲህም ሪቮሉሽናዊ ወጣት የሚል ጋዜጣ በማውጣት በወጣቱ አካባቢ ቅስቀሳውን ይዟል:: ሪቮሉሽን ሰባት ይሆናል::

በመካሄድ ላይ ያለው አዲሱ ዲሞክራቲክ ሪቮሉሽን ሊሳካ የሚችለው በሕዝብ ሠፈር በአሁኑ ጊዜ የሚገኙት የንቃት፣ የድርጅትና የትጥቅ ድክመቶች ሲወገዱ ነው ብለናል:: ሰፊውን ሕዝብም ከነዚህ ድክመቶች ማላቀቅ ኃላፊነቱ በመጀመሪያ ደረጃ የሚወድቀው በተራማጅ ኃይሎች ላይ ከሆነ፣ የኋለኞቹ ለዚህ ታሪክ ተግባር ብቁ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል:: ለዚህ ታሪካዊ ኃላፊነት ብቁ ሆነው መገኘት ማለትም የግለሰብኝነትንና የጠባብ ቡድን ስሜትን በዲሞክራሲያዊ ውይይት አስወግደው አሁን በየፊናቸው ተለያይተው በግላቸው የሚታገሉት የፖለቲካ ቡድኖች ሕብረትን ሲመሰርቱ ነው:: ተራማጅ ኃይሎች የሰፊውን ሕዝብ ድክም የሚያስወግዱት በመጀመሪያ የራሳቸውን ድክም ሲወጡ ነው::



ከጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄዎች አንዱና ዋነኛው የተራማጅ የፖለቲካ ቡድኖች የተቀነባበረ የጋራ የትግል ሕብረት መፍጠር ነው:: የወዛደሩን ፖርቲ ለመፍጠር መሠረት የመጣሉ ጊዜ አሁን ነው:: ማሌሪድ የወዛደሩ ፖርቲ ጽንስ የሚፈጠረው አሁን ተለያይተው ለየብቻቸው ከሚታገሉት የፖለቲካ ቡድኖች ነው ብሎ ያምናል:: ይህንን እምነቱንም መኢሶን ከተባለው ታጋይ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅት ጋር በፈጠረው የትግል ሕብረት በተግባር አስመስክሯል:: በመኢሶንና በማሌሪድ ሕብረትም በሚወጣው እውነት በተባለው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ጋዜጣ ለሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች ተመሳሳይ ሪቮሉሽናዊ ጥሪ አድርገዋል፣ ወደፊትም ከማድረግ አይቆጠቡም::

ማሌሪድ መለስተኛ ፕሮግራሙን ማውጣቱ እራሱን ችሎ በግሉ ለመቆየት ስለፈለገ አይደለም:: ማሌሪድ ከቶ ምን ቢሆን ይህንን አያደርግም:: በእርግጥ ማሌሪድ የጠባብ ቡድን ስሜትን ያሸነፈ ድርጅት ነው:: ከመኢሶን ጋር የጀመረውን የውህደት ሂደት በይበልጥ በማፋጠን ለወዛደሩ ፖርቲ ባስቸኳይ መሠረት የሚያስመሰክርበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ለማስገንዘብ ይወዳል:: ማሌሪድ መለስተኛ ፕሮግራሙን በይፋ ለማውጣት የበቃው ለሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች ይህ ታጋይ ድርጅት በተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ያለውን አቋም ለማሳወቅና በዚህም ምክንያት በተራማጅ ቡድኖች የትግል ሕብረት ለመፍጠር ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል ብሎ ስለሚያምን ብቻ ነው:: ማሌሪድ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ የወዛደሩን ፖርቲ መመሥረት መሆኑን ለተራማጅ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ ቡድኖች በድጋሚ ለማስገንዘብ ይወዳል:: ለዚሁ ሁኔታ መፈጠር በራሱ በኩል የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል:: ሌሎችም ለዚህ ታሪካዊ ተግባር ሪቮሉሽናዊ ጥሪውን ያቀርባል::

የወዛደሩ ፖርቲ እስኪመሠረት ድረስ በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ ሪቮሉሽን ከቅልበሳ ነፃ የመሆን እድሉ በጣም የመነመነ ነው:: በሪቮሉሽናችን ላይ የውስጥና የውጭ አድሃሪ ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ እያሴሩበት ነው:: እየተደራጁበትም ነው:: በውስጥ ፊውዳሎች የቢሮክራሲ ቱጃሮችና አናርኪ-ፋሽስቶች ከሰፊው ሕዝብና ከተራማጅ ኃይሎች ጋር በከፍተኛ ትንንቅ ላይ ይገኛሉ:: ከውጭ ሸሽተው የወጡ ፊውዳሎች፣ ተገንጣዮች አናርኪ-ፋሽስቶች በኢምፔሪያሊዝምና በአድሃሪ የዓረብ መንግሥታት ድጋፍ ተደራጅተው በመካሄድ ላይ ያለውን ሕዝባዊ ሪቮሉሽን ባጭር ለመቅጨት በመሯሯጥ ላይ ናቸው:: ባካባቢም የሚገኙት አድሃሪ መንግሥታት የነዚህ ፀረ ሪቮሉሽን ኃይሎች ደጀንና ምሽግ ሆነዋል:: በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ሪቮሉሽን ቢሳካ፣ የረጅም ጊዜ ውጤቱ በጎረቤት ሀገሮችና በአካባቢው ጂኦ ፖለቲካ ላይ ከፍ ያለ ሪቮሉሽናዊ ተጽእኖ ስለሚኖረው ዓለም አቀፍ አድሃሪ ኃይሎች ትግላቸውን ባጭር ለመቅጨት ተነሳስተዋል::

የሱዳንን፣ የሶማሊያና የኬንያ አድሃሪ መንግሥታት ባገራችንና በሪቮሉሽናችን ላይ ገሐድ ጠርነት ከመክፈት ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስላል:: በተለይም ሶማሊያ፣ በኛቱ ላይ የወሰደችው የመስፋፋትና የተምክህነኛነት አቋምና ለሠርጐ ገብ አድሃሪያን በምታደርገው እርዳታ በሶሻሊዝም ስም የአድሃሪን የትሮኛን ፈረስ ሆናለች::

ጠላቶቻችን በጣም ብዙ ናቸው:: ቢሆንም የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝባዊ ሪቮሉሽንን ከቶ ምንም ቢሆን ሊቀለበሱ አይችሉም:: ሪቮሉሽኑ ሊቀ ለበስ የማይችልበትን ሁኔታ መፍጠር ደግሞ ታሪክ በተራማጅ ኃይሎች ላይ የጣለው ግዴታ ነው:: የዚህ ግዴታ የመጀመሪያ ደረጃው የወዛደሩን ፓርቲ መፍጠር ነው:: ለዚህም ታሪካዊ ተግባር ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶችና ቡድኖች እንዲተባበሩት ማሳሰቡ ጥሪውን ደግሞ ደጋግሞ ያሰማል::

በተራማጆች ቁራጥ ትግል የወዛደሩ ፓርቲ ይመሠረታል
ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል::



## II ግ. ሶ. ሪ. ዶ. የሚታገለለት ዓላማ

1/ በመካሄድ ላይ ለሚገኘው ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ የትግል አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ካሉት ሃቀኛ ተራማጅ ድርጅቶችና ቡድኖች ጋር በመተባበር እስካሁን የተገኙትን ድሎች ለማስጠበቅም ሆነ ለበለጠ ድሎች በላቀ ኃይልና ጥንካሬ መታገል ስለሚጠይቅ ይህም ሊሳካ የሚቻለው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ትግል ሪቮሉሽናዊ አመራር ሲጨበጥ በመሆኑ፣ ይህንንም ሪቮሉሽናዊ የአመራር ቦታ ለመሊጡ የሚችለው ደግሞ በሣይንሳዊ የወዛደሩ ርእዮተ ዓለም የሚመራ የወዛደሩ መደብ ፓርቲ በመሆኑ፣ የዚህ ፓርቲ መመሥረትና ሉሎችን ኃይሎች መሰብሰብ የሪቮሉሽኑ ዴሎ ወሳኝ በለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ እዚህ ገበ ለመድረስ የሚጠይቀውን የትግል ዝግጅት ማጠናቀር::

2/ በሚቋቋመው በወዛደሩ ፓርቲ አማካይነት ሌሎቹን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች በማስተባበር ለዘመናት የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ሲበዘብዙና ሲጨቁኑ የኖሩትን ጠላቶች ማለት ፊውዳሊዝምን ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን በመደምሰስ በነሱ መቃብር ላይ አዲሲቱን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን መመሥረት::

## III የምነታገልላት አዲሲቱ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ፣

1/ ምን ዓይነት መንግሥት

በወዛደሩ ግንባር ቀደምትነት፣ በአርሶ አደሩ አጋርነት፣ በሌሎች ጭቁን የሕብረተሰብ ክፍሎችና ተራማጅ ወገኖች ተባባሪነት የሚቋቋም ሕዝባዊ የበላይነት ይሆናል::

2/ የአስተዳደሩ ይዘት፣

በኢምፔሪያሊስቶች አቃፊነትና ደጋፊነት የተመሠረተውን የፊውዳል ካፒታሊስት የመንግሥት መዋቅር ከሥረ መሠረቱ በመሰባበር በምትኩ ሕዝባዊ አስተዳደርን ማስፈን::

3/ የሰፊው ሕዝብ ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች

- የንግግርና የመጻፍ
- የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና የመታጠቅ
- ሥራ የማቆምና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ
- የእምነትና የጾታ እኩልነትን የሚመለከቱ መብቶችና ነፃነቶችን ማስከበር::

4/ <u>የብሔረሰቦች መብት</u>

ሀ/ በኢትዮጵያ መልክዓምድር ላይ ሰፍረው የሚገኙትን የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችን ፍጹም የሆነ የብሔረሰብ እኩልነትን ማክበር፤ እያንዳንዱ ብሔረሰብ በቋንቋው፤ በሃይማኖቱ፤ በባህሉና በሁለንተናዊ እሴቶቹ ከሌላው ብሔረሰብ ጋር እኩል መሆኑን ማወቅና ማስከበር፤ ከዚህም አልፎ እያንዳንዱ ብሔረሰብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ማርክሳዊና ዲሞክራሲያዊ መርህ እስከመገንጠልና የራስ የሆነ መንግሥት እስከ ማቋቋም መብት እንደሚደርስ ማወቅ::

ለ/ የብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን ዲሞክራሲያዊ መብት ዓለም አቀፋዊ መመሪያ እንደመሆኑ ሁሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚገኙ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ጭቁን ሕዝቦች ጥያቄ ላይ ይወሰናል:: ስለሆነም በብሔረሰቦች መሃል የነበረውን የተዛባና በጭቆና ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን አጥፍቶ በመተካት፤ በመፈቃቀድና ነፃ በሆነ ወዳጃዊ አንድነት ላይ መመሥረት ይኖርበታል:: በዚህም ባንድ ወገን የትልቅ ብሔረተኝነትን ትምክህት፤ በሌላ ወገን ደግሞ ጠባብ ብሔረተኝነትን በመዋጋት ሁለቱንም የአንድነት ጠንቆች ለማጥፋት የማያቋርጥ ትግል ማድረግ::

5/ <u>ለሰፊው ሕዝብ ለኑሮውና ለእድገቱ መሠረታዊ የሆኑ ብሔራዊ ጥቅሞች አደረጃጀት</u>

ሀ/ <u>ትምህርት</u> 1/ ሀገሪቱን ካሰራት አደንቋሪና ጎታች ፊውዳላዊ የትምህርት፤ የባህልና የእምነት ተጽእኖ አላቆ በቦታው ከኢምፔሪያሊስቶች ተጽእኖ ነፃ የሆነ ዲሞክራሲያዊ፤ ብሔራዊና ተራማጅ ሥርዓተ ትምህርትን በመገንባት መሠረታዊ የሆነውን የወዛደሩን ርእዮተ ዓለም የሚያንፀባርቀውን ማርክሳዊ ሌኒናዊ አስተሳሰብ በትምህርት፤ በባህል፤ በቲያትር፤ በስዕል በሙዚቃና በጠቅላላ በምርምር ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ እንዲይዝ ማድረግ::

2/ ነፃ ትምህርት ለሁሉም የሚደረስበትን ዘዴ በመተለም በአጭር ጊዜ ውስጥ መሃይምነትን ማውደም::

3/ የሥርዓተ ትምህርቱ አደረጃጀት ንድፈ ሃሳብን ከተግባር ለማገናዘብ የሚያመች እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ሣይንሣዊ ምርምርና ቴክኖሎጂን እንዲስፋፋ የሚያበረታታ መሆን አለበት::



ለ/ <u>ጤና</u> የያንዳንዱ ዜጋ ጤንነቱ መጠበቅ መብቱ ከመሆኑም በላይ ጤናማ ዜጋ ለሀገር እድገትና ልማት መሠረታዊ ኃይል በመሆኑ ነፃ ሕክምና ለሁሉም የሚደረስበትን መንገድ መሻትና በግብር ከሥራ ላይ ማዋል::

ሐ/ <u>ሥራ</u> የሰፊውን ሕዝብ አጠቃላይ ኑሮና እድገቱን ለመቀየስ የሚመሠረተውን የኢኮኖሚ መዋቅር ሕብረተሰቡ እንዲያንቀሳቅሰው ሕዝቡን በፈርጁ በፈርጁ አደራጅቶ መምራት ተቀዳሚ መሆኑ አይካድም:: ከዚህም ድርጊት አንፃር ዋናው በተዛባና የተገማማ ሥርዓት ውስጥ የተዝረከረከውንና ብላሽ የሆነውን የሰው ጉልበት በማስተባበር፤ መስክ በማስያዝና ሥራ መስክ በመክፈት ሴተኛ አዳሪነትንና ዘሙትን፤ ሥራ አጥነትንና ቦዘኔነትን ከሀገሪቱ ምድር ማጥፋት፤ ከዚህም የሕዝቡን ሠርቶ የመኖር መብት በማስከበር በአኳያው የሠርቶ አደሩን ሕዝብ በሥራው ላይ ሆነ ከሥራ ሲሰናበት /በጡረታም ሆነ በጉዳት/ የኑሮው ሁኔታ የሚሻሻልበትን ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ::

ሕዝቡ ከላይ እንደተገለጸው የሥራ መብቱን ሊጠቀምበት እንዲችል ያስፈልጋል:: ለዚህም ብቁ የሚያደርጉትን በኑሮው ላይ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን በተሟላ መልክ ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት ይኖራል::

6/ <u>ብሔራዊ ኢኮኖሚ</u> ለብዝበዛ ጥቅም ሊውል በማይችል መንገድና ለሶሻሊስት ሕብረተሰብ የኢኮኖሚ መሠረት ሊሆን በሚችል መንገድ ብሔራዊ ኢኮኖሚን መገንባት::

ሀ/ በሰፊው ሕዝብ ትግል የተገኘውን የየካቲት 25ቱን የመሬት ለአራሹን አዋጅ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ የሚውልበትን ተግባራት በማከናወን የብዙሃኑን አርሶአደር ጥቅም በማስጠበቅ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሠረት በሚያስችል መንገድ የሕብረት እርሻዎች እንዲስፋፉ ማበረታታትና መደገፍ::

ለ/ ከኢምፔሪያሊስቶች ከከሃዲ ቡርዧዎችና አቀባባይ ቡርዧዎች የተወረሱትን ኢንዱስትሪዎች ማጠናከርና ለከፍተኛ ለታዳጊ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ማደግ በር እንዲከፈት ማድረግ፤ ከኢምፔሪያሊስቶች የጥገኝነት ሰለወናው ተላቆ የዳበረ የኢንዱስትሪ ተቋም በመመሥረት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት እርሻ እንደመሆኑ መጠን በእርሻና በኢንዱስትሪ መሃል የተሳሰረና የተደጋገፈ ሰንሰለት በመፍጠር በከተማና በገጠር ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ማቀራረብ::

ሐ/ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ማዕድናት በቁጥጥር ሥር በማዋል በመሬት ማኅፀን ውስጥ የሚገኙትን ማዕድናት ፍለጋ በማሳደግ ለሀገሪቱ ከባድ ኢንዱስትሪያች መጋቢ እንዲሆኑ ማድረግ::

መ/ ከኢምፔሪያሊስቶች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥገኝነት የተነሣ የሀገሪቱ የንግድ ይዞታና ለውጥ በነሱው እጅ በመውደቁ ሀገሪቱ ነፃ የሆነ ድምጽ የላትም:: ስለሆነም ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ ከአገር ውጭ የምታደርጋቸውን የንግድ ለውጦች በሙሉ በቁጥጥር ሥር በማዋል በሀገር ውስጥ ያሉትን ታዳጊ እንዱስትሪያችና የገጠር ድርጅቶች ምርታቸውን እንዲያሳድጉ በመቆጣጠርና በመደገፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የንግድ ለውጡን ከውጭ ተጽእኖ በማላቀቅ ለሀገሪቱ በሚጠቅም አኳኋን የንግዱን ይዞታ እንዲስተካከል ማድረግ::

ሠ/ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን የመገናኛ ዘርፎች ማለት ራዲዮ ቴሌቪዥን ጋዜጦች የፖስት፣ የአየርና የባሕር መመላለሻዎችን ፍጹም በሆነ መንገድ በቁጥጥር ሥር በማድረግ ጥቅማቸው ለብዙኃኑ ሰፊ ሕዝብ እንዲሆን ማድረግ ይህም ማለት በፊውዶ ካፒታሊስት ሥርዓት ለጥቂቶች ብሎ የተዘረጋውን የመገናኛ አገልግሎት የተገላቢጦሽ በሰፊው ሕዝብ አካባቢም ለሰፊው ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ::

ረ/ በሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሶሻሊስታዊ ክልል ውስጥ ያሉትና በአብዮቱ የሚታቀፉ መካከለኛና አነስተኛ ባለ እንዱስትሪያችና በነዚሁ ደረጃ የሚገኙት ነጋዴዎች መንግሥት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትግበርት ውስጥ ተካፋይነት እንዲኖራቸው ማድረግ::

7/ የውጭ የፖለቲካ መመሪያ

የሀገሪቱ የውጭ ፖለቲካ መመሪያ ከባዕድ ተጽእኖ ነፃ የሆነ በታወቁት የገለልተኞች መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል:: የኢትዮጵያ አብዮት በዓለም ከሚካሄደው የጭቁን ሕዝብ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ና ፀረ ብዝበዛ ትግል አንዱ አካል እንደመሆኑ መጠን የነዚህ ሕዝቦች ትግል ደሉ መጉ ናጸፍ ጽኖም ነው፤ስለሆነም፣ በዓለም በየትም አካባቢ በተለይም በሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የሚካሄዱት ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ጽዮናዊነትና ፀረ ዘረኛነት ትግሎች መደገፍ ዓለም አቀፋዊ ሶሻሊስታዊ ግዴታችን ይሆናል:: በዚህ ረገድ ከሶሻሊስት መንግሥታትና ተራማጅ ኃይሎች ጋር የጠበቀ ትብብር ማድረግ ይኖርበናል::



ከአካባቢ ሀገሮች ጋር በመከባበርና ባለመፈላለግ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠርና ማጠንከር ሲያስፈልግ በንፃሩ ግን ከሀገሪቱ አካባቢም ሆነ ከኢምፔሪያሊዝም በተለይም ከአሜሪካው ኢምፔሪያሊዝም ለሚነዛ ፀረ ሶሻሊስት አመጽ ወይም በጦራዊ ለዕለናን ለማደፍር ወረራ የማያወላውል ቆራጥ ሶሻሊስታዊ አፀፋ መመለስ::

የመከላከያ ኃይል

ምንም እንኳን ጥቂቱ መለዮ ለባሹ ከየካቲት 66 ጀምሮ ከሰፊው ሕዝብ ጋር የተሰለፈ ቢሆንም የጦር ኃይሉ አደራጃጀት ለጭቁንና ለብዝበዛ ማስፈጸሚያ እንዲሆን ታስቦ በመሆኑ እንዳለ ወደ ሕዝባዊ ጦር ሠራዊትነት መቀየር አይቻልም:: የመለዮ ለባሹ ክፍል ከሕብረተሰቡ የተውጣጣ እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ መደብ አባላትን ያቀፈ ነው:: ከመካከሉ ለሶሻሊስቱ የተሰለፉ አሉ በንፃሩ ደግሞ በሶሻሊስቱ ላይ የተሰለፉ ይገኙበታል:: ስለዚህ ሀገሪቱን ከውጭ ወራሪ ኃይልም ሆነ ከሶሻሊስቱ የውስጥ ጠላቶች ለመከላከል በጾታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ሳይለይ በጠቅላይ ከሁሉም ተራማጅ ኃይሎች የተውጣጣ በወዛደሩ ርእዮተ ዓለም የታነፀ ሕዝባዊ ጦር እንዲመሠረት ይደረጋል:: ከዚህም በላይ የፊውዶ ካፒታሊስት ሥርዓት የኢትዮጵያን መለዮ ለባሾች እስከዛሬ ድረስ የምርት ተጠቃሚያች እንዲ በማምረቱ ተግባር ላይ ሊኖራቸው የሚገባቸውን ተካፋይነት ነፍጓቸው ቆይቷል:: ከዚህም የተነሳ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ የነበራቸው ድርሻ እጅግ አነስተኛ ሊሆን ችሏል::ስለዚህ በወዛደሩ ርእዮተ ዓለም ታንጾ የሚመሠረተው ሕዝባዊ ጦር በምርት ተግባር ላይም ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፍ ይደረጋል::

## IV የቅርብ ጊዜ የትግል ግቦች

1/ ስለ ዲሞክራሲያዊ መብት

በመካሄድ ላይ ያለው ሶሻሊስትን ወደፊት ሊራመድ የሚችለው በፊውዳሊስቶች፣ ቢሮክራቶችና በኢምፔሪያሊስቶች ላይ የማያዳግም የአመጽ እርምጃ ሲወሰድባቸው ብቻ ነው:: ይህን የሚያደርገውና የሚያደርግ ችሎታ ያለው ሰፊው ሕዝብ ብቻ ነው:: የሰፊው ሕዝብ የመንቃት፣ የመደራጀትና የመታጠቁ ትግል የተያያዘና የሚደጋገፉ ሂደቶች እንደመሆናቸው አድሃሪያንም እየደመሰሱ የመታጠቁ ወደፊት የመራመዱ ጉዳይ እንደዚሁ የተያያዘ ነው:: ይህንን በተግባር ለመተርጎም፣ በተለይም የሰፊውን ሕዝብ መደራጀት ለማፋጠን ለጭቁኖች ብቻ የሚሆን የዲሞክራሲ መብታቸውን የመገጠቁ ጉዳይ የጊዜው ዋና ጥያቄ ነው:: በሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲ በአድሃሪያን የሚወሰደው የአመጽ እርምጃ ተለያይቶ እንደማይታዩ የሰፊው ሕዝብ የመታጠቅ ጉዳይ ከዲሞክራሲው ጥያቄ ጋር

እንደ አውራ ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል:: በለሆነም ሪቮሉሽኑን ላለማስቀለበስ ስም ሆነ ወደፊት ይበልጥ በይበል እየተጋጸደ እንዲገሰገስ በሚደረገው መራራና ቀጣይ ትግል ውስጥ ይህ ድርጅት በቀደሚያ የሚታገልለት ይህ የሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲና የትጥቅ ጥያቄ በሪቮሉሽናዊ መንገድ ገቢን እንዲመታ ነው::

2/ <u>የግራ ኃይሎች የግንባር አስፈላጊነት</u>

ይህ ድርጅት ገና እንደተመሠረተ ከዋና ዋና ዓላማዎቹ አንዱና ተቀዳሚው ጠባብ የቡድን ስሜትን በመቃወስ በተለይ ደግሞ ጠባብ ብሔረተኛነትንና ትምህክተኛነትን ስሜት ለመዋጋትና በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ሃቀኛ ተራማጆች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን የተበታተኑ የግራ ኃይሎችን ለመሰብሰብና ከሰፊው ሕዝብ ጋር በመቀላቀል ግንባር ቀደም የወዛደር ፓርቲ እንዲመሠረት የትግል አስተዋጽኦ ለማድረግ ነበር ከዚህም አንጻር ቅንጣት ታህል ዝንፍ ሳይል በሰቆ ሰቆ አቅጣጫ የመጣውን የንዑስ ከበርቴ ርእዮተ ዓለምን በመዋጋት ሊተባበሩ ከቆረጡና ታሪካዊ ድርሻውን ከወቁ ሃቀኛ ታጋዮች ጋር የአንድነት መድረክ ሊሆን የሚችል ትግልና የትብብር መድረክ ከፍቷል:: ሌሎችንም ታጋዮች ፀረ ማርክሲስት የሆነውን ጠባብ የቡድን አመለካከትን በማስወገድና ጠባብ ብሔረተኛነትንና ትምህክተኛነትን በመጣል አብረውት እንዲታገሉ ይጋብዛል::

ከዚህ አንፃር ነው እንግዲህ ድርጅታዊ ህልውና እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገራችን በሰቆ ሰቆ ድርጅቶችና ቡድኖች ሥር ከተሰለፉት ተራማጆች ጋር ግልጽ በሆኑ በሪቮሉሽኑ በሚፈጠሩት ሁኔታዎች ማለት የታክቲክና የስትራቴጂ ጥያቄዎች ላይ ወይይት በማድረግ አጠቃላይ የሪቮሉሽኑን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የግራ <u>ኃይሎች የትግል አንድነት የጋራ ግንባር</u> መፍጠር የሚቻለው:: <u>ይህ የግራ ኃይሎች የግንባር ጥያቄ ከሕዝቡ አጠቃላይ የዲሞክራሲ ጥያቄ ተነጥሎ ስለማይታይ ለብዙኃኑም የዲሞክራቲክ መብት የመታገሉ</u> ጉዳይ የጋራ ሪቮሉሽናዊ ተግባራችን ይሆናል::



ኃ===ዩ===ኃ===ፒ

<u>የመደራጃ ጋዜጣ</u>

ቁጽ 1 ቁ.2

ታህሣሥ 19 ቀን 1968 ዓ.ም.

ሕዝቡን ለማደራጀት የተከሰፈ ጓደኞቻችን ሁሉ ለመሰብሰብና ከሕዝቡ ጋር ለመደራጀትም ሆነ የመነሻ መሠረትና መተማመኛ ይሆነን ዘንድ የመደራጃ መሥመራችንን ቀድሰን ማቀረብ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው ከዚህ የሚከተለውን አነስተኛ ፕሮግራም አቅርበናል::

<u>የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል ፕሮግራም፣</u>

1ኛ/ <u>ዓላማ፣</u>

1. እስከዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሲጨቁን የኖረው የፊውዳል ሥርዓት በተደራጀ ሕዝባዊ ፓርቲ አማካይነት ለመደምሰስ ከሌሎች ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች፣ ድርጅቶችና ግንባሮች ጋር በመተባበር ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለማቋቋም፣

2. የሀገራችን ኢኮኖሚ ከውጭ አገሮች ተጽዕኖ ነፃ በማድረግ በተከታተለና ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመገንባት፣

3. በብሔሮች መካከል እንዲፈጠር የተደረገውን ጥላቻ ለማስወገድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሠረቱን አስተካክሎ በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ የአገር አንድነትን ለመገንባት ነው::

2ኛ/ <u>የኢኮኖሚ አቋም፣</u>

በማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ፓርቲው የሚከተለው ዘዴ ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት ይሆናል::

1. <u>እርሻ፣</u>

ሀ/ የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በእርሻ ላይ ስለሆነ የመጀመሪያው የኢኮኖሚ መሠረት በእርሻ ላይ ያተኩራል::

ለ/ መሬት ላራሹ የሚለውን መሪ ሃሳብ ከሥራ ላይ እያዋለ እንደየአካባቢው ሕዝብ የኢኮኖሚ አቋምና የፖለቲካ ንቃት፣ ትምህርት እየተሰጠ የሕብረት እርሻዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል::

ሐ/ በየካቲት 25 ቀን 67 ዓ.ም. የታወጀው የመሬት አዋጅ በትክክል በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ::

መ/ ዘላን የሆኑ ኢትዮጵያውያን የከብት እርባታቸውን የሚያስፋፉበትና እርሻም የሚጀምሩበት መንገዱ ተፈልጎ በአንድ አካባቢ እየሰፈሩ የተሻለ ኑሮ የሚገነቡበትን ዘዴ ይከፍታል::

2. <u>ኢንዱስትሪ፣</u>

ሀ/ ከእርሻ ውጤቶች ጋር ተያያዥ በሆኑ መለስተኛ ኢንዱስትሪዎች ደረጃ በደረጃ ማንኛቸውም የኢንዱስትሪ ውጤቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ይደረጋል::

ለ/ አንዳንድ መለስተኛ ኢንዱስትሪዎች በግል የሚካሄዱበትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማረጋገጫ ገለፃ ባለ መልክ ይረጋገጣል::

3. <u>ንግድ፣</u>

ሀ/ የውጭ ንግድ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይካሄዳል::

ለ/ መለስተኛና የችርቻሮ የሀገር ውስጥ የንግድ ሥራዎች በመሠረታቸው በግለሰቦች የሚካሄዱ ሆነው እንደየአስፈላጊነቱ መንግሥትም ተሳትፎ ይኖራል::



35/ <u>የመንግሥት አቋም፣</u>

መንግሥቱ የፖለቲካና የርእዮተ ዓለም አቋም በሕብረተሰብአዊነት የተመሠረተ ሆኖ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚፈቅደው እየተተረጎመ ይሠራበታል::

1. <u>ሸንጎዎች፣</u>

ሀ/ የአገሪቱን ከፍተኛ ሥልጣን የሚይዘው በየደረጃው በሰፊው ሕዝብ ተመርጦ የሚቋቋመው ብሔራዊ ሸንጎ ይሆናል::

ለ/ በየመንግሥቱ የአስተዳደር ደረጃዎች ከፍተኛውን ሥልጣን የሚይዙት ሕዝባዊ ሸንጎዎች ይሆናሉ::

ሐ/ ሸንጎዎች ለሰፊው ሕዝብ አገልጋይ እንጂ ተገልጋይ ባለሥልጣናት እንዳይሆኑ በሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ::

2. <u>አስተዳደር፣</u>

ሀ/ የአስተዳደር ዘርፎች በጠቅላላ በሕዝብ ቁጥጥርና ምርጫ ተመሥርተው የሚካሄዱ ይሆናሉ::

ለ/ አዲስ የአስተዳደር መመሪያ ወጥቶ ለሕዝቡ በሚስማማ፣ ለብዙ በዛና በሥልጣን ለመባለጊያ ግን በማያመች መንገድ ይደራጃል::

3. <u>ፍርድ፣</u>

ሀ/ በየደረጃው በሕዝብ የተመረጡ የፍርድ ሸንጎ አባላት እንዲኖሩ ይደረጋል::

ለ/ የፍርድ ሸንጎው አባላት የሚመረጡት በብሔራዊ ሸንጎው በሚወጡት ሕጎች ሆኖ ኃላፊነታቸውም በቀጥታ ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል::

4. <u>መብቶች፣</u>

1. የኢትዮጵያ ዜጋ ሰብአዊ መብቶች፣ ማለትም የመሰብሰብ፣ በፖለቲካ የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመጻፍና የሰላማዊ ተቃውሞ መብቶች ይከበራሉ::

2. መንግሥት ከማንኛውም ሃይማኖት ገለልተኛ ይሆናል። ሆኖም ግን ማንኛውም ዜጋ ያሻውን ሃይማኖት መከተል ይችላል።

3. በሃይማኖትና በጾታና በዘር ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እያንዳንዱ ሰው በመንግሥት ጉዳይ መሳተፍ ይችላል።

4. ብሔረሰቦች በጠቅላላ በቋንቋቸው የመናገር፣ የመስተዳደር፣ የመማርና ባሕላቸውን የማስፋፋት መብታቸው ይከበራል።

5. የእያንዳንዱ ዜጋ ሠርቶ የመኖር መብት ይከበራል።

5ኛ/ <u>ሕብረተሰብአዊ አገልግሎቶች</u>

1. <u>መጦሪያና ጡረታ</u>

ሀ/ ማንኛውም ዜጋ ከ60 ዓመት እድሜው በኋላ ወይም በአካል ጉድለት ምክንያት ምንም መሥራት ካልቻለ በመንግሥትና በሕብረተሰቡ የጡረታ አገልግሎት ይሰጠዋል።

ለ/ በመጠነኛ የአካል ጉድለትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እንደ ሙሉ ጤናማ ሰው ለሠራ የማይችሉትን ያቋቁማል ሥራም ይሰጣል።

2. <u>ስለ ትምህርት</u>

ሀ/ ሥርአተ ትምህርት እያንዳንዱ ዜጋ በአገሪቱ የኢኮኖሚ እቃ ተሳትፎ ለራሱና ለሕብረተሰቡ ጥቅም እንዲሰጥ የሚያስችል ሆኖ ይዘጋጃል።

ለ/ ነፃ ትምህርት የእያንዳንዱ ዜጋ መብት ሆኖ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትምህርት ለሁሉም የሚዳረስበት መንገድ ይዘጋጃል።

ሐ/ በአገር ውስጥ በየብሔረሰቡ ቋንቋ ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት የትምህርት ዝግጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።



መ/ በየገበሬ ማህበራትና በከተማዎችም ከሌሎች ውስጥ ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በመንግሥትና በሕዝቡ ተባብር እንዲከፈቱ ይደረጋል።

ሠ/ መሃይምነትን ከአገር ለማጥፋት የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም በሰፊው እንዲካሄድ ይደረጋል።

3. <u>ባሕላዊ ጉዳዮች</u>

ሀ/ በቅርቡ ወደአገራችን ሰርጎ የገባውን የኢምፔሪያሊስት ባሕል ተጽዕኖዎች በማጥፋት የየብሔረሰቡ ባሕል እንዲስፋፋ ጥረት ይደረጋል።

ለ/ የሥነጽሑፍ፣ የኪነጥበብ፣ የሙዚቃ የቴያትር ድርጅቶች በየብሔረሰቡ ባሕልና ቋንቋ እንዲስፋፋና እንዲደራጁ ይደረጋል።

ሐ/ ይስፖርትና ልዩ ልዩ መዝናኛ ስፍራዎች እንዲዘጋጁ አስፈላጊው እርዳታ ይሰጣል።

4. <u>ጤና</u>

ሀ/ የጤና ፕሮግራም <u>አስቀድሞ መከላከል</u> በሚል መመሪያ የተመሠረተ ሆኖ ለሰፊው ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደራጃል።

ለ/ በየአማካይ ቦታዎች ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ለመስጠት የሚችሉ የጤና ጣቢያዎችና ክሊኒኮች እንዲደራጁ ይደረጋል።

ሐ/ ነፃ ሕክምና የሚሰጡ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል።

መ/ የኢምፔሪያሊስት አገሮችን ተጽዕኖ ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑት መድኃኒቶች በአገር ውስጥ እንዲዘጋጁ ጥረት ይደረጋል።

6ኛ/ <u>ስለ ሠራተኞች</u>

1. የላብ አደሩ መብትና ጥቅም ተከብሮ ከብዝበዛ ነፃ እንዲሆንና የጉልበቱ ውጤትም በቀጥታ ሥር እንዲውል ይደረጋል።

2. በተለይ ላብአደር የሆኑ የቢሮ ሠራተኛ የሆኑ ሴቶች ከወሊድ በፊት የ15 ቀኖችና ከወሊድ በኋላ የ45 ቀኖች የእረፍት ጊዜ ተሰጥቷቸው ለሕፃናቱ መዋዕለ ሕፃናት እንዲዘጋጅ ይደረጋል::

3. የቢሮ ሠራተኞች በቢሮ ከበርቴ አለቆቻቸው መገለሉና መጨቆን እንዳይደርስባቸው መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበር እንዲደራጁ ይደረጋል::

4. ማንኛውም ሠራተኛ በሳምንት ውስጥ ቢያንስ የአንድ ቀን እረፍት እንዲኖረው ይደረጋል::

5. የእያንዳንዱ ሠራተኛ የጡረታ መብት በማያወላውል ሁኔታ ይከበራል::

6. ሠራተኞች በሙሉ በአገራቸው በፖለቲካ ተካፋይ እንዲሆኑ ከእረፍት ጊዜአቸው ሌላ የፖለቲካ ትምህርትና ጥናትና የሚያደርጉበት መንገድ ይዘጋጃል::

7. የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የሚያገኙበት መንገድ ይዘረጋል::

7ኛ/ <u>ስለወጣት ድርጅቶች፣</u>

1. ወጣቶች በቀበሌያቸውና በትምህርት ቤታቸው ተደራጅተው ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋም በመያዝ የመሰላቸውን ፖለቲካ ፓርቲ በመከተል እንዲደራጁ ይደረጋል::

2. በተለይ የወጣቶች አደራጅ ክፍል በማቋቋም በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ወጣቶች በመቀሳቀስ የፖለቲካ ንቃታቸው ከፍ እንዲል ይደረጋል::

3. ወጣቶች ከአርሶ አደሩና ከላብ አደሩ የሚማሩበትንና መልሰውም የሚያስተምሩበትን የትምህርት ፕሮግራም በተስተካከለና በሚያስተማምን አቋሙን ይዘጋጃል::



8ኛ/ <u>ስለሴቶች ድርጅት፣</u>

1. ሴቶች ካለባቸው ድርብርብ ጭቆና ነፃ እንዲወጡ አስፈላጊውን የፖለቲካና የኤኮኖሚ እርዳታ ይሰጣል::

2. በፓርቲው ድርጅት ውስጥ ለሴቶች አደራጅ ኮሚቴ የተለየ ሥፍራ በማስያዝ በፍጥነት እንዲደራጁ ይደረጋል::

9ኛ/ <u>መ ከ ላ ከ ያ፣</u>

1. አገራችንን ከውጭም ሆነ ከውስጥ ጠላት ለመከላከል የመከላከያ ኃይላችን በሕዝባዊ ጦር ሠራዊት ላይ የተመሠረተ ይሆናል::

2. የሕዝባዊ ጦር ሠራዊት አባላት ተጨማሪ እውቀት እንዲኖራቸውና ቢያስፈልግም እንደ የዝንባሌያቸው በሌላ የሥራ መስክ መሠማራት እንዲችሉ ሰፋ ያለ የልማት ትምህርት እንዲገበዩ ይደረጋል::

3. ማንኛውም የመከላከያ ባልደረባ በሰላም ጊዜ በልማት ሥራዎች እየተካፈለ ኑሮውን እንዲያሻሽል ይደረጋል::

4. ማንኛውም ዜጋ ለትምህርት ከተሰማራበት ጊዜ አንስቶ የጦር ትምህርት እንዲያገኝ ይደረጋል::

10ኛ/ <u>የውጭ ፖሊሲ፣</u>

1. የውጭ ፖሊሲያችን በገለልተኝነትና በሰላም አብሮ መኖር ላይ የተመሠረተ ይሆናል::

2. በተለይ ከጐረቤት አገሮች ጋር የቀረበ ግንኙነትና ወዳጅነት ኖሮን ሰፋ ያለ የኤኮኖሚና የባሕል ትብብር እንፈጥራለን::

ሰፊው ሕዝብ ይደራጃል
ሰፊው ሕዝብ ይታገላል
ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል ነፃ ይወጣል::

_______///_______

## የወዛደር ሊግ ፕሮግራም

### 1. የወዛደር ሊግ የትናው ነው

"" የወዛደር ሊግ፣ የኢትዮጵያን የወዛደር ፓርቲ ለማቋቋም በሚደረገው ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግን እንደ አጣዳፊ አላማው አድርጎ የወሰደ፣ ማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅት ነው:: ይህ የወዛደር ፓርቲ ሲቋቋም የሚቸለው በማርክሲስት—ሌኒኒስት ቡድኖች መዋሃድ መሆኑን ሊግ ያምናል:: የወዛደሩ መደብ የደሃ የመካከለኛ ገበሬ ክፍሎች፣ እንዲሁም ሌሎች ጭቁንና ተራማጅ ሕዝቦች፣ የወዛደሩን መደብ የበላይ ገዥነት በኢትዮጵያ በመመስረት ከበዝባዥ መደቦች ጋር የሚያደርጉትን ትግል ሁሉ መምራት የወዛደሩ ፓርቲ ተግባር ነው::

"" የወዛደር ሊግ፣ የበዝባዥ መደቦችን ገዥነት ገልብጦ፣ በወዛደሩና በአጋሮቹ በተለይም በደሃ በመካከለኛ ገበሬዎች የሚመራ መንግሥት ለመመስረት የሚቻለው፣ ቀጥታ በሆነና አመፅ ላይ በተመሠረተ አብዮታዊ ትግል መሆኑን ያምናል:: በዝባዥና ገዥ መደቦች ስልጣናቸውን በሰላም፣ ያለ ደም መፋሰስ፣ ለወዛደሩ መደብ ያስረክባሉ ብሎ ራሱን አያታልም::.....

"" የወዛደር ሊግ ማርክሲዝም—ሌኒኒዝምን የተገበረን የአስተሳሰቡ መምሪያ ቲዎሪያዊ መሰረት አድርጎ ይቀበላል:: ማርክሲዝም—ሌኒኒዝም፣ የዓለም ወዛደሮች ትግልና አብዮታዊ ልምድ ዘገባ ነው:: የተመሠረተውም በታላላቅ አብዮታዊውያን የወዛደሩ መሪዎች በካርል ማርክስ፣ በፍሬደሪክ ኤንግልስ፣ በቪ.አይ. ሌኒን፣ በጆሴፍ ስታሊንና በማኦ ሴ ቱንግ ትምህርቶች ላይ ነው::""

### ከወዛደር ሊግ የመተዳደሪያ ደንብ መግቢያ

ከላይ የተጠቀሰው፣ በወዛደር ሊግ የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በገጽ 1 ላይ ይገኛል:: በአጭሩም ቢሆን፣ የወዛደር ሊግን አጣዳፊ ዓላማ፣ የወዛደር ሊግ በፓርቲ አመሠራረት ላይ ያለውን አቋም፣ የወዛደር ሊግ በመንግሥት ሥልጣን አያያዝ ላይ ያለውን አቋም፣ የወዛደር ሊግ የሚከተለውንና የሚመራበትን ሀይገስ፣ የወዛደር ሊግ የሚያምንባቸውንና የሚቀበላቸውን ታላላቅ አብዮታውያንና የዓለም አቀፍ የኮሚኒስት ንቅናቄ መሪዎች አድርጎ የሚወስዳቸውን፣ ስለሆነም በትሮትስኪዝምና በሪቪዥኒዝም ላይ ያለውን አቋም ግልጽ በሆነ መንገድ ያመለክታል::

የወዛደር ሊግ እስከዛሬ ድረስ እንደ ልሳኖች አድርጎ በሶስት ጋዜጣዎች ተጠቅሞአል:: በመጀመሪያ <u>ወዛደር / LABOURER /</u> የተባለውን ጋዜጣ ያወጣ ነበር:: በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ይህንን ጋዜጣ ማውጣት አቆመ:: በአሁኑ ጊዜ የሚያወጣቸው ልሳኖች <u>ወዝ</u> እና <u>የወዛደር ድምፅ</u> የሚባሉት ናቸው::



ስለወዛደሩ ሊግ በበለጠ ለመረዳት ለሚፈልጉ ታጋዮች፣ልሳኖቹን በተከታታይ እንዲያነቡ እንጋብዛለን::

### 2. በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ማዕበል ውስጥ እንገኛለን

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያችን ውስጥ አብዮት በመካሄድ ላይ ነው:: ይህም አብዮት የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሂደት አካል ነው:: የካቲት 1966ን እንደ አብዮቱ ሂደት መጀመርያ አድርገን አንወስደም:: በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት፣ በባሕርዩ ሆነ በይዘቱ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት፣ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት የሆነ የመደብ ትግል ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት የሆነ ትግል ትናንት የተጀመረ አይደለም:: በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ እንኳ፣ በአፄ ቴዎድሮስ፣ በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የእንግሊዝ፣ የኢጣልያን፣ የኦቶማን ቱርክ፣ የፈረንሳይና የሩሲያ ኢምፔሪያሊስቶች በኢትዮጵያ ላይ ዓይናቸውን ከመጣላቸው በላይ በተለይም እንግሊዝና ኢጣሊያን ጦር ድረስም ሄደው የኢትዮጵያን ሕዝቦች ለመውረር አያሌ ሙከራዎችን አድርገዋል::

እነዚህን የኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አኩሪ በሆነ መንገድ ተቋቁመው እንደነበር የጭቁን ሕዝቦች የትግል ታሪክ በማኅደሩ ውስጥ አስፍሮአል:: ከአርባ ዓመታት በፊትም ከፍተኛ የሆነ የኢምፔሪያሊስት ወረራ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ በኢጣሊያን ፋሽስቶች ተካሂዶ ነበር:: ያ የአምስት ዓመት የመከራ ዘመን፣ ያ የአምስት ዓመት የትግል ዘመን፣ ያ የአምስት ዓመት የጭቁን ሕዝቦች አብዮት ዘመን የኢትዮጵያን ሕዝቦች ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል በሚት ወደከፍተኛ ደረጃ አድርሶታል:: ከዚህ ሁሉ እንገኘሁ የምናውቀው፣ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ከጀመረ ከመቶ ዓመታት አያንስም::

ፀረ—ፊውዳል፣ ፀረ—መሬት ከበርቴ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያችን ውስጥ መካሄድ የጀመረው የዛሬ ሁለት ዓመት አይደለም:: አያሌ መቶ ዓመታት አልፈውታል:: ፀረ—መሬት ከበርቴ ትግል እጅግ የተፋፋመው ኢትዮጵያን በጉልበት አንድ ለማድረግ አፄ ምኒልክ የግዛት መስፋፋትን ዘመቻ ሲያካሂዱ በነበረበት ወቅት ነው:: በዚያን ጊዜ፣ በደቡብ ምሥራቅ፣ በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና በማዕከላዊ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አካባቢው ሰፊ ሕዝብ መሬቱንና ንብረቱን ተዘርፎ ከበረን ተገፍፎ ወደ ገባርነት፣ ወደሎሌነት ተለወጠ:: በዚያን ጊዜ፣ በከፍተኛ ደረጃ የተጀመረው ፀረ—ፊውዳል ትግል እስከዛሬ እንደቀጠለ ነው:: በአለፈት ዘጠና ዓመታት ውስጥ በእነዚሁ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተካሄዱት ፀረ—ፊውዳል ትግሎች ሰበት የትግል ገጾችን በአንድነት አዘለው እናገኛቸዋለን::

በአንድ በኩል፣ ፀረ—ፊውዳል ትግሉ፣ ሰፊው ሕዝብ መሬቱን ከወራሪና ተባባሪ ከሆኑት የአካባቢው የመሬት ከበርቴዎች /ወይም ባላባቶች/ እፍ ፈልቅቆ ለማውጣት የሚያደርገው ትግል ነው::

በሌላ በኩል፣ ፀረ–ፊውዳል ትግሉ፣ ጭቁን ብሔረሰቦች ከአማራውና ከትግሬዉ በተለይም ከአማራውና ተባባሪው ከሆኑት የአካባቢ ብሔረሰቦች የገዥ መደቦች ቀንበር ሥር ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉት ትግል ነው:: ሶስተኛው ፀረ–ፊውዳል ትግሉ ገጽ፣ በሃይማኖት መስክ /ክርስትና የገዥው መደብ ሃይማኖት መሆኑና አብዛኛው ጭቁን ሕዝብ ግን የሚከተለው ሃይማኖት ሌላና በተለይም እስልምና መሆኑ/ የሚደረገው ትግል ነው:: በየተጠቀሱት የኢትዮጵያ ክፍሎች እንግዲህ ፀረ–ፊውዳሉ ትግሉ፣ ለመሬት ጥያቄ፣ ለብሔረሰብ ጥያቄ ለሃይማኖት ጥያቄ፣ ለሰው ጥያቄዎች በአንድነት መፍትሔን ለማግኘት የሚካሄዱ ትግል ነው::

በሰሜን ኢትዮጵያም ቢሆን ፀረ–ፊውዳሉ ትግሎች በየጊዜው ተካሂደዋል:: በቅርብ ጊዜ እንኳን የምናስታውሳቸውን የወያኔን ንቅናቄ፣ የጎጃምን ንቅናቄዎች፣ የወሎን ንቅናቄዎች የበጌምድርንና የኤርትራን ደሃ ገበሬዎችና ቀጥረኛ ገበሬዎች ንቅናቄዎች ለመጥቀስ ይቻላል:: የፊውዳሉ ሥርዓት፣ በሰሜንም ጠንክሮ በሚገኝ፣ ለሰሜን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰጠው የቃላት ሽንገላ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም:: ያው፣ እንደ ደቡብ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦችም አፀማቸው እስኪጋለጥ ድረስ በነበረውና በመንኮታኮት ላይ ባለው የፊውዳል ሥርዓት ተገጠዋል፣ ተበዝብዘዋል::

ከዚህ ሁሉ እንግዲህ የምናየው፣ ፀረ–ፊውዳል እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ከጀመረ ረዥም ዘመናት አሰፈውታል::

ፀረ–ቡርዧ ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ መካሄዱ የጀመረው የዛሬ ሁለት ዓመት አይደለም:: የኢትዮጵያ የወዛደር መደብ፣ ፀረ–ቡርዧ ትግል ማካሄዱ ከጀመረ ቆይቷል:: የወዛደር ፀረ–ቡርዧ የትግል ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ የታየው በኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር መመሥረት እንደሆነ ለማየት አዳጋች አይደለም:: የኢትዮጵያ ወዛደር፣ በትግሉም ውስጥ በቀላሉ የማይገመቱ ድሎችን ተቀዳጅቷል:: ለኢትዮጵያም የጭቁን ሕዝቦች አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: በተለይም በአክሲሉ ላይ ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማን በማድረግ፣ በየካቲት እንቅስቃሴ ወቅት የተጫወተውን ሚና ማንም ሊረሳው አይችልም::

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው፣ ፀረ–ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ–ፊውዳል እና ፀረ–ቡርዧ ትግል በኢትዮጵያ መካሄዱ ከጀመረ ብዙ ዘመናት አልፈውታል:: የካቲት 1966 የዚህ ትግል መጀመርያ አይደለም:: አብዮት የትግል ሂደት ነው:: የትግል ዕድገት ሂደት ደግሞ፣ ከግብታዊ ወደ ንቃታዊ፣ ዲያሌክቲካዊ በሆነ መንገድ የሚሸጋገር ነው:: የካቲት 1966ትን ለዩ ከአደረጉት ነገሮች፣ አንደ ዐቢይ መቀመር ያለበት ነገር፣ ቀደም ሲካሄዱ የነበረት የተበታተኑ ያልተያያዙ ትግሎች



አሁን መያያዛቸውና ጭቁን ሕዝቦች ከዳር እስከዳር መነሳሳታቸው በተለይም ደግሞ ከፊውዳሉ ቡርዧው ጦር ጭቁኑና ተራማጁ ብዙኀን ወታደር ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ፣ ከፍተኛ ትብብር በኅብረተሰቡ ውስጥ ተፈጥሮ ፀረ–ቡስት የሆነው የአብዮት ማዕበል በይፋ መፈንዳቱ ነው:: ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄዱ ላይ ነው የምንለበት ምክንያት ለዚሁ ነው:: ይሁንና አንድ ዐቢይ ነገርን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ ነው:: ይኸውም አንዱ አብዮት በመካሄዱ ላይ ነው ማለት፣ ያ አብዮት ድልን የግድ ይቀዳጃል ማለት አይደለም:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ድልን የግድ ይቀዳጅ ዘንድ ቢያንስ ቢያንስ ሰባት ዐበይት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል::

አንደኛ:: የኢትዮጵያ ወዛደር ፖርቲ መቋቋም ይኖርበታል:: መቋቋም ብቻ ሳይሆን በአለኝታዊነት በሰፊው ሕዝብ ተቀባይነት በትግሉ መድረክ ላይ አይሎ፣ ገናናነቱን ተቀዳጅቶ የአብዮቱን አመራር መያዝ ይኖርበታል:: በተጨማሪም ከሚቋቋሙትና ዴሞክራቲክ ከሆኑ የንዑስ ከበርቴ ፖርቲዎችና ድርጅቶች ጋር የጋራ ግንባር ለመፍጠር መቻል ይኖርበታል:: የወዛደር ፖርቲ መሪነት የሌለው ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ድልን ለመቀዳጀት አይችልም:: ገቡን አይመቷም!

ሁለተኛ:: የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ጦር፣ የወዛደሩና የገበሬው አብዮታዊ ጦር፣ መቋቋም ይኖርበታል:: ያለ አብዮታዊ ጦር የገዥ መደቦችን ከሥልጣን ለማውረድ አይቻልም:: በአሁኑ የኢትዮጵያ ጦር ላይ፣ የወዛደር ሊግ ያለው እምነት በክፍል አምስት ተመልክቷል::

ሶስተኛ:: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች ንቃተ–ኅሊና ከፍ ብሎ መገኘት ይኖርበታል:: ግብታዊ እንቅስቃሴ፣ ድልን የመቀዳጀት ኃይሉ አናሳ ዝቅተኛ ነው:: ንቃታዊ እንቅስቃሴ ግን፣ በተለይም የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ አመራር ያለው እንቅስቃሴ ግቡን ለመታ ይችላል:: በአሁኑ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ የአብዮታቸውን ትርጉም፣ የወደፊት ዕጣቸውንና ተስፋቸውን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአብዮቱ ምክንያት ሊደርሱባቸው የሚችሉትን ችግሮች ሁሉ በሚገባ መረዳት ይኖርባቸዋል:: አብዮት የሚያመጣውን የአጭር ጊዜ ችግሮችና የሚያስገኛቸውን የረዥም ጊዜ ድሎችና ነፃነት የማይገነዘብ ሕዝብ አብዮቱን ከግብ ለማድረስ ይሳነዋል:: ይህ እንዳይሆን የኢትዮጵያ ተራማጆች ሰፊውን ሕዝብ የማንቃት ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው:: የፖርቲው አስፈላጊነትም ከዚሁ ላይ ነው::

## 3. ዐብዮትና ፀረ—አብዮት በአሁኑ ወቅት

መደቦች በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ እስካሉ ድረስና ዐብዮት በመካሄዱ ላይ እስካለ ድረስ፣ ፀረ—አብዮትም በአንፃሩ ይካሄዳል:: ሌላው ይቅርና፣ የወዛደሩ የበላይ ገዥነት በተቋቋመባቸው በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ እንኳ፣ በዓለም ላይ ገና ካፒታሊዝም እስከሰፈነ ድረስ ይህ የወዛደሩ መደብ የበላይ ገዥነት ፀረ—አብዮትን ለመቋቋም መቆየት ያለበት መሣሪያ ነው፣

አንደኛ:: በዛሬው ወቅት፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በአገራችን ውስጥ አብዮት በመካሄዱ ላይ ይገኛል:: የአብዮት ኃይሎች በነፃና በተደራጀ መልክ ባይሆንም በአጠቃላይ ሲታይ፣ የወዛደሩ መደብ የደኸ የመኸከለኛው የገበሬ መደብ ክፍሎች፣ የዝቅተኛውና የመካከለኛው ንዑስ ከበርቴ መደብ ክፍሎች ናቸው:: በተለይም ደግሞ ጥቂቶ ወታደሮች የያዙትን መሣሪያ አፈሙዝ በፀረ—አብዮት ካምፕ ላይ ካዞረበት ከሁለት ዓመታት ወዲህ ጀምሮ፣ በየጫፉ፣ በየገደሉና በየጫካው ከታጠቁና ከተደራጁ አድሃሪያን ጋር በሚያደርጉት ጠርነት በጥቂት የማይቆጠሩ፣ ሕይወታቸውን ሰውተዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ተራማጅ ዘማቾች ለአሥራ አምስት ሰምንት ወራት ያህል በየገጠሩ ከሰፊው የገበሬ ሕዝብ ጋር በመኖር፣ ከእርሱም በመማርና መልሰም በማስተማር፣ በተለይም ደግሞ የመሬትን አዋጅ በሥራ ላይ በማዋሉ ረገድ ያደረጉት አስተዋጽኦና በዚህም ዘመቻ ላይ ከአድሃሪያን ጋር ባደረጉት ትግሎች በጥቂት የማይቆጠሩ ሕይወታቸውን ሰውተዋል:: በአንዳንድ መንግሥታዊ ድርጅቶችም ውስጥ በተለይም በመሬት ይዞታና በሕዝብ ማስፈር ሚኒስቴር አማካኝነት የመሬትን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል ከተሰማሩት አብዮተኞች አያሌዎቹ በአድሃሪያን እጅ ደማቸው እንደፈሰሰ ታሪክ ያስታውሳቸዋል::በዚህ አጋጣሚ የወዛደር ሌግ በአብዮቱ የተሰውትን ተራማጆች በሙሉ በማስታወስ የእነርሱን አብዮታዊ ፈለግ በመከተል በአብዮቱ ለመሰዋት የተዘጋጀ መሆኑን ለመግለጽ ይወዳል::

አነስተኛም ቢሆን በፍጥነት ለሚካሄደው ለኢትዮጵያ አብዮት አጋዥ ነው ሊባል የሚችል አስተዋጽኦ ባያደርጉም፣ አያሌ የነፃና የተደራጁ ፀረ—ፋሽስት የሆኑ አብዮታዊ ድርጅቶች ከየካቲት ወዲህ ብቅ ብቅ ብለዋል:: ወደፊትም ሌሎች እንደሚፈጠሩ እርግጠኞች ነን:: እነዚህ ድርጅቶች፣ የሚያወጡዋቸው ጋዜጦች፣ አጋጣሚያቸውን በመፍጠርና በእነርሱም በመጠቀም አብዮቱን ለማራመድ የሚያደርጉት ትግል፣ ጉልቶ የማይታይ ቢሆንም የማይናቅ አይደለም:: እርግጥ በአሁኑ ወቅት እነዚህ ተራማጅ ድርጅቶች ተከታትነው ይገኛሉ:: ሁሉም የየራሱን እንደየራሱ ያካሄዳል:: በመካከላቸው የጋራ ትብብርና የሥራ ቅንጅት አይታይም:: ጥቃቅን ነገሮች፣ እንደከፍተኛ ነገሮች ታይተው ተራርቀው ይመቀየቀን ጉዳይ ያጠነክራሉ:: <u>አንዳንዶቹም፣ በጊዜያዊ ዱሎች የመደባቸን ደካማ ስሜት ያስያሉ:: በድርጅቶቹ፣ መካከል ማለትም ፀረ—ፋሽስት በሆኑ ድርጅቶች መካከል መከባበር አይታይም::</u>



የርዕዮተ ዓለም ትግል በምን አይነት ዘዴ መካሄድ እንዳለበት በዙዎቻቸው ገና አላወቁ ነውም:: ማርክሲስት—ሌኒኒስት የሆነን የርዕዮተ ዓለም ትግል ከንዑስ ከበርቴ መበጣጠቅና መነካከስ ጋር እናምታታለን:: እርግጥ ነው፣ የእነዚህን ሁሉ ችግሮች መንስኤ ዝርዝር ባለ መልክ ለመተንተን ይቻላል:: ይሁንና በዚህ፣ የወዛደር ሌግን ለማስወቅ ባዘጋጀነው አጭር ጽሑፍ ውስጥ አንገባበትም:: ዋናው ቁም ነገር፣ እነዚህ አብዮታዊ የሆኑ ድርጅቶች የነገው የኢትዮጵያ ወዛደር ፓርቲ አስኳል ናቸው የሚል እምነት አለን:: የወዛደር ሌግም ከእነዚሁ ድርጅቶች አንዱ ነው::

በአጠቃላይ እንግዲህ፣ የአብዮቱን ኃይሎች ስናይ ማለትም በዛሬው ወቅት፣ ነቅተውና ተደራጅተው አናገኛቸውም:: በልዩ ልዩ ምክንያቶች ትብብርን፣ ቅንጅትን፣ አንድነትን በመካከላቸው ገና አልመሠረቱም:: ይህ ሁኔታ ይህ ደካማ ጎን፣ ለፀረ—አብዮት ኃይሎች ተጨማሪ ኃይልን ሰጥ በቅቷል::

ሁለተኛ:: አብዮቱ በይፋ ከፈነዳበት ወቅት ጀምሮ የፀረ—አብዮቱ ካምፕ እየተደራጀ፣ እየነቃ እያየለ ሄዷል:: በአሁኑ ወቅት፣ ይህ ካምፕ ከአራት የነቁ፣ የታጠቁና የተደራጁ ፀረ—አብዮት ኃይሎች የተገነባ ነው ለማለት ይቻላል::

ሀ/ <u>የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች</u>:: በመንግሥት ላይ የሚገኘው የፊውዳል—ቡርዧ ሥርዓት መልሶ ለማንሠራራት ይህ ነው የማይባል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል:: በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው ይህ ታላቅ የፀረ—አብዮት ምሽግ፣ ምዕራብ ጀርመንን፣ እንግሊዝን፣ እሥራኤልን፣ ኢጣሊያንና ፈረንሣይን በከፍተኛ ደረጃ ያዘላል:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ የያንኪ ኢምፔሪያሊዝም / " The Small Nation Approach " / የሚለውን አዲስ መርህ በመከተል ትናንሽ በሆኑት የካፒታሊስት አገሮች /በቤልጅግ፣ ኖርዌይ፣ ዴንማርክ፣ ስዊዘርላንድ ወዘተ.../ በመጠቀም ፀረ አብዮትን ለመፈጸም ይጥራል:: የአሜሪካኖች ጦር በአሁኑ ወቅት በሜዲቴራንያን ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ ውስጥ ብቻ የማዘዋወር ሳይሆን በቀይ ባሕርም ውስጥ በምፅዋና በአሰብ አካባቢ ተዘጋጅቶ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል:: ምን ቢነሳ፣ ምን ለማድረግ የሚለውን ማንም ተራማጅ የሚያውቀው ነገር ነው:: ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ወኪሎች አማካኝነት /በጠፊ ውስጥ በልዩ ልዩ መንግሥትና የግል ድርጅቶች፣ በመረዳጃና በሚሲዮን ድርጅቶች፣ ወዘተ.../ ብዙ ብዙ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የስለላ ሸጥሮችን እንደሚፈጽም ሰፊው ሕዝብ የሚያውቀው ነገር ነው::

ለ/ <u>ኢትዮጵያን የሚያከብቧት የፊውዳል ቡርዡ አገዛዞች</u>:: በሱዳን፣ በሳውዲ አረቢያ፣ በሶማሊያና በኬንያ፣ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀወትና ለመቀልበስ የማይመለሱ መንግሥታት ይገኛሉ:: ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ነች:: በሕዝብ ቁጥርም ከአፍሪካ በሶስተኛውን ቦታ ይዛ ትገኛለች፣ በተፈጥሮ ሀብት በኩልም ቢሆን በግልጽ የሚታይ ባለጸጋነት እንጂ ድሀነት የሏትም፣ በዚህ ምክንያት ይህ አብዮት በአገራችን ቢሳካ በሚያከብቧት አገሮችና ሕዝቦች ላይ ተራማጅ ተፅእኖን ማሳረፉ አይቀርም:: በእነዚህ አገሮች ደግሞ ተራማጅ እንቅስቃሴዎች ቢካሄዱ ይህን በቀጣይ ለኢምፔሪያሊዝምም ሆነ ለገዥ መደቦች መጥፎ ሁኔታ እንደሚፈጥር ጥርጥር የለውም:: ሌላውም እንኳ ቢቀር የኢትዮጵያ አብዮት ይህን ቢቀጣይ የአገሪቱ የምርት ተግባር፣ በተለይም በእርሻ መስክ፣ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚንቀሳቀስ በወንዞቹና በአፈር ጉዳይ ላይ በሱዳን፣ በግብፅና በሶማሊያ ላይ የሚኖረው ተፅእኖ ግምጡ ግልጽ ነው:: እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ምክንያቶች እንገነዘብ፣ እነዚህ አድሀሪ አገዛዞች በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የፀረ-አብዮት ኃይሎች የሞራልና የማቴሪያል ዕርዳታ በከፍተኛ ደረጃ ይሰጧሉ፣ በሉቀ ለቀ ድንበሮቹም ላይ ከዛሬ ነገ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ጦር እንከፍታለን በማለት ሽበርን በመፍጠር ላይ ይገኛሉ:: በርግጥ ገበቸን እያሰለጠኑና እያስታጠቁ በኤርትራ፣ በባሌ፣ በአፋርና በሲዳሞ እንደሚያስገቡ ዕውቅ ሆኗል::

ሐ/ <u>የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት /ኢ.ዲ.ዩ./</u>:: ይህ የፀረ-አብዮት ድርጅት በመሠረቱ በአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ የሚመራ ድርጅት ነው:: አመራሩን የያዙት የቀደሞው የንጉሥ ዘርያቸው፣ መሳፍንቶችና መኳንንቶች ናቸው:: የኢ.ዲ.ዩ. ማዕከላዊ አመራር በውጭ አገር ውስጥ ይገኝ እንጂ፣ በአገር ውስጥ ያሉትና አብዮቱ የመታቸውና የፈረጠጡ አድሃሪያን በሙሉ በኢ.ዲ.ዩ. ጃንጥላ ሥር ተደራጅተውና ታጥቀው ፀረ-አብዮት ተግባር በማካሄድ ላይ ይገኛሉ:: በተለይም ደግሞ፣ ዝነኛው ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የቀደሞውን ቢሮክራሲና የስለላ ድርጅት እንዳለ በመውረሱ፣ ኢ.ዲ.ዩ. ቀንደኛውን አይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የመንግሥት ሥልጣንን በእጁ ይዞ ይገኛል:: ይህን ሁኔታ በመመልከት እንገነዘብ፣ የኢምፔሪያሊዝምንና የአካባቢው አድሃሪ አገዛዞችን ከፍተኛ ዕርዳታ ስለሚያገኝ፣ እራሱም በቂ ትጥቅና ድርጅት ስላለው፣ ይህ አድሃሪ ኃይል በአብዮቱ ላይ ከፍተኛ አደጋን ለመጣል ይችላል:: እያሉ ዐቢይ መከራዎችን አድርጓል! የአብዮት ኃይሎቻችም በፍጥነት ካልተባበሩና ካልጠነከሩ ይህ አብዮት ከመቀልበስ ለመዳን ያስቸግረዋል::



መ/ <u>የኢ.ህ.አ.ፓ ና መሰሎቹ ግንባር</u>:: በዚህ ግንባር ውስጥ የሚገኙት አንዳንዱ ድርጅቶች የተራማጅነት ጠባይ ያሳዩበት ወቅት ነበር:: ይሁንና አብዮቱ እየገፋ ሲሄድ፣ ይሰን በይል ላይ እየተቀናጀ ሲሄድ፣ የመደቦች አሰላለፍም በበለጠ እየጠራ ሲሄድ፣ አሁን የወዛደሩ ፓርቲ ለመሰረት በተቃረበበት ወቅት፣ እውነተኛ ገጻቸው እየተጋለጠ መታየት ጀመረ:: በዚህ ግንባር ውስጥ የሚገኙት ድርጅቶች፣ በተግባራቸው ሄደው እላይ ከተጠቀሱት ሰባት ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር ተሰልፈዋል:: ከዚህም በላይ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በማወናበድና በማሳሳት በኢትዮጵያ አብዮት ላይ በአሁኑ ወቅት በመፈጸም ላይ የሚገኙት ታሪካዊ ወንጀል ምን ጊዜም ቢሆን አይረሳም::

እንደሚታወቀው ወከኙ የኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በወዛደሩም ሆነ በምሁሩ በተለይም በወጣቱ አንጓል ውስጥ ጠንካራ የሆነን ፀረ መንግሥት አቋም ቀርጾ ነበር:: ከዚህም ሌላ፣ ይህና ግምት ሊሰጠው የሚችል የፖለቲካ ንቃተ ኅሊና አልነበረም:: ከየካቲት በፊት እንገደሁ፣ ወጣቱ ምሁሩ፣ ያልነቃና ያተደራጀ ቢሆንም ጠንካራ የሆነ ፀረ መንግሥት አቋም ነበረው:: የተጠቀሱትም አናርኪስቶችና ትሮትስኪዎች እነሳቸው የፖለቲካ ትምህርት ሳይሰጡ /በርዕዮተ ዓለማቸው ምክንያት ይህን ለማድረግ አይችሉምና!/ የወጣቱንና የምሁሩን ነባር ፀረ መንግሥት አቋም በመጠቀም ብዙዎችን አብዮታውያን ለማሳሳት በቅተዋል:: ይህም የኢትዮጵያን ተራማጆች ኃይል ሊከፋፍልና ሊያዳክም አጀን ሊያራርቅ ለጊዜውም ቢሆን ችሏል::
የኢትዮጵያ ተራማጆች ይህንን እውነት ተገንዝበን፣ ትግላችንን ከምንጊዜም ይልቅ በበለጠ ማጠናከር ይኖርብናል::

እናጠቃልለን፣ በአሁኑ ወቅት የአብዮትና ፀረ-አብዮት ኃይሎች በመዋጋት ላይ ይገኛሉ:: የፀረ-አብዮት ኃይሎች ከፍተኛ ትብብር፣ ቅንጅትና አንድነት በመካከላቸው አላቸው:: የአብዮት ኃይሎች ግን እነዚህንና ለአብዮት አጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አሟልተው አይገኙም:: ከዚህ በቀላሉ የምንደመድመው፣ በአብዮቱ ኃይሎች፣ በተለይም በነቁና በተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የመቀራረብ የመተባበርና ሊቻልም የመዋሀድ ጉዳታቸው ከነባራዊው ሁኔታ የሚፈልቅ ነው:: የወዛደር ሊግ ይህን መደምደሚያ በሥራ ለመተርጎም የበኩሉን ከመታገል አይቆጠብም::

## 4. የወዛደር ሊግ — የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም

አያሌ የፖለቲካ ድርጅቶች "በኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት" አርማ ሥር የወጣውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የደርግ ፕሮግራም በለው ይጠሩታል:: ይህ አጠራር እጅግ የተሳሳተ ይመስለናል።

ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም መለስተኛ ፕሮግራም ነው:: መለስተኛ የሆነውም ለኮሚኒስቶች ብቻ ነው:: ፕሮግራሙን ለሚቀበሉ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ መለስተኛ አይደለም:: ኮሚኒስቶች ከዴሞክራቲክ ኃይሎች ጋር እንዲተባበሩ የሚያስችላቸውን የአብዮት ፕሮግራም አውጥተው መለስተኛ ፕሮግራም ይሉታልና:: ይህም ሲሆን የራሳቸው የውስጥና ከፍተኛ የሆነ ፕሮግራም ይኖራቸዋል::

በክፍል አንድና በክፍል ሁለት የተመለከተውና ዘጠኝ ነጥቦችን የሚያዘለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በመሠረቱ የምንቀበለው ፕሮግራም ነው:: ስለሆነም የወዛደር ሊግ ፕሮግራም ነው ብንል እንችላለን:: ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን ያካሄዱና የሚያካሄዱ ኮሚዩኒስት ፓርቲዎችና ድርጅቶችን በተመለከተ፡ ፕሮግራሞቻቸውን በናሙና፡ በይዘታቸው ከዚሁ ሌላ ሆኖ አናገኘውም:: በአንዳንድ ዝርዝር ነጥቦች ላይ፡ የአገሩና የኅብረተሰብ ተጨባጭ ነገሮችና ሁኔታዎች የግድ ይገሀባረቃሉ:: ጊዜአዊ ወታደራዊ መንግሥት ይህንን ፕሮግራም ከሰማይ አላወረደውም:: በአጠቃላይ ከዓለም-አቀፍ የኮሚዩኒስት ንቅናቄ ልምድ በተለይም ደግሞ ከከፊል-ፊውዳል ከፊል-በርዢ ኅብረተሰብ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮቶች ልምድ የተገኘ ፕሮግራም ነው::

የወዛደር ሊግ፡ አጠቃላይ ፕሮግራሙን እንደራሱ ፕሮግራም አድርጎ ሲቀበለው ቀጥሎ የተመለከቱትን አጫጭር ማብራሪያዎችንና ማሻሻያዎችን ጨምሮ ነው::

አንደኛ:: የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዋና ዋና ጠላቶች ስንዘረዝር፡ የሶስቱ ጠላቶች ቅደም ተከተል እጅግ አሳሳቢ ነው:: የአጻጻፉ ቅደም ተከተል የጠላቶቹን የክብደትና የከፍተኛነት ደረጃ ማመልከት ይኖርበታል:: ስለሆነም የወዛደር ሊግ ሰፋ ያለ ቅራኔዎችን ትንተና ካደረገ በኋላ፡ አጻጻፉ ኢምፔሪያሊዝም፡ ፊውዳሊዝም እና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም የሚል ቅደም ተከተል እንዲኖረው ያስፈልጋል ብሎ ያምናል:: እርግጥ ነው፡ ለታክቲክ ሲባል ፊውዳሊዝም፡ ኢምፔሪያሊዝም እና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ተብሎ ሊጻፍ ይችላል:: ይሸውም ሰፊው ሕዝብ ኢምፔሪያሊዝምን በሚገባ ለማየት ችሏል፡ ጥብቅ በሆነ መንገዱ ሊያየው ችሏል ለማለት አይቻልም በሚለው ነገብ ምክንያት ነው::



ይሁንና ይህ የንቃተ-ኅሊና ዝቅተኛነት ጉዳይ እንጂ፡ ተጨባጭ ሁኔታውን በትክክል የሚያንፀባርቅ አይደለም:: ኢምፔሪያሊዝም ባይኖር ኖሮ ወይም ኢምፔሪያሊዝም በአገራችን ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ባይገባ ኖሮ የመሬት ከበርቴውን፡ አድሃሪ ቢሮክራሲውንና ጥፍሮቻቸውን የኢትዮጵያ አብዮት ካለብዙ ችግር ሊደመስሳቸው በቻለ ነበር:: ይህን ግን ስላልሆነና የኢምፔሪያሊዝም ፀረ-አብዮት ክንዱ እጅግ ከባድ በመሆኑ፡ በቅራኔዎች አተናተንም ሆነ ቅራኔዎችን ለመፍታት በሚደረገው ተግባራዊ ጥረት በተቻለ ፍጥነት ኢምፔሪያሊዝምን ከአገራችን ውስጥ ማስወጣትና በሮቻችንም ለፀረ-አብዮት ድርጊቶች ዝግ እንዲሆኑ ያስፈልጋል::

ሁለተኛ:: በኢኮኖሚው አንፃር ስንመለከት፡ የትራንስፖርት ኢንዱስትሪ፡ የአስመጪና ላኪ ድርጅቶች፡ በአገር ውስጥ የታላላቅ ማከፋፈያ ተግባሮች በሙሉ አሁኑኑ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋል ይኖርባቸዋል:: ይህ እርምጃ በተደራጀ መልክ በአስቸኳይ ካልተወሰደ የገበያው ሁኔታ በበለጠ እየዘበ እንደሚሄድ ግልጽ ነው:: የሸቀጥ ዋጋዎችንም ለመቆጣጠር አዳጋች ይሆናል:: የኅብረት ሱቆችንና ገበያዎችንም በማስፋፋት ረገድ መንግሥት ከፍተኛ የማቴሪያልና የቴክኒክ ዕርዳታ ማድረግ ይኖርበታል::

ሦስተኛ፡ በብሔረሰቦች ጉዳይ ላይ የወዛደር ሊግ፡ በማዕከላዊ ልሳኑ /ወዝ/ አማካኝነት ብዙ ጽሑፎችን አቅርቧል:: አንባቢያችን ወ.ዝ ቁ. 7፡ 11፡ 12፡ 13፡ እና 14ን እንዲያነቡ እንጋብዛለን:: ከእነዚሁ ጽሑፎች ለመረዳት እንደሚቻለው፡ የወዛደር ሊግ በዚሁ ጉዳይ ላይ ግልጽ ያለ አቋም አለው:: የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል ድረስ የሚለው ሌኒኒስት-ስታሊኒስት መርህ ሳይገባኝ ትክክለኛ የሆነ መርህ መሆኑን ይቀበላል:: ይሁንና በተለይ አሁን በአለበት ወቅት መርሁን በቃል የመቀበል እርሱን ብቻ የማስተጋባት ጉዳይ እስከዚሁ ፋይዳ የሚሰጠው ነገር አይደለም:: ምክንያቱም ኢምፔሪያሊስቶችም በቃል ይቀበሉታልና:: የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊስቶች የጂቡቲን ጭቁን ሕዝብ /ቀን ስለሆነ/ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን ተገንጥሎ ራሱን የቻለ ነፃ መንግሥት እስከማቋቋም ድረስ ያለውን መብት በቃል አውቀዋል:: ደጋግመውም ይህንኑ ይወተውታሉ:: የናይጄሪያ ጭቁን ሕዝቦች እንዲገነጠሉ፡ ኢምፔሪያሊስቶች ይህንን መርህ ደግመው ደጋግመው ተጠቅመውበታል::

በኢትዮጵያችንም ቢሆን፡ አናርኪስቶችና ትሮትስኪስቶች፡ ኢ.ጌ.ዩ.ም ጭምር የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እንዲገነጠሉ ይህን መርህ ከማንገት አልቦዘኑም በተግባርም እየታየ ነው:: በአሁኑ የኢትዮጵያና የዓለም ሁኔታ እነዚህን አባባቢ ሁኔታዎች በሚገባ በማጤን፡ ይህ የሌኒኒስት መርህ ካሉት ሁለት ገጾች /የመገንጠል ገጽና የአንድነት ገጽ/ በአንደኛው ገጽ ላይ፡ በአንድነት ገጽ ላይ እናተኩራለን::

ይህ አንድነት የሪጅናል አውቶኖሚን /የራስ በራስ አገዛዝን/ ቅርጽ መያዝ አለበት ብለን እናምናለን:: ስለሆነም የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች ችግር በአሁኑ ጊዜ ለመፍታት የሚቻለው በእኩልነት መርህ ላይ በመመሥረት እንጂ እስከ መገንጠል ድረስ የሚለውን ሐረግ ያለቦታው፣ ያለጊዜው፣ ከተጨባጭ ታሪክ ውጪና ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ፍላጎት ውጪ ከወረቀት ላይ በመጻፍ አይደለም::

ሪጅናል አውቶኖሚ ወይም የራስ በራስ አገዛዝ አከባቢዎች በኢትዮጵያ ከመቋቋማቸው በፊት ግን በቂ ሕዝባዊ ውይይትና ሳይንሳዊ ጥናት ያስፈልጋል:: ይህም ጥናት በፍጥነት ይጀመር ዘንድ አንድ ማዕከላዊ የሆነ የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም ያስፈልጋል:: ከዚያም በኋላ እንደአስፈላጊነቱ በየቦታው ቅርጫፍ የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩቶች እንዲቋቋሙ መደረግ ይኖርበታል::

_____/////_____

## 5. በኢትዮጵያ አብዮት ጉዳይ ላይ አንዳንድ ዐበይት ነጥቦች

ሀ/ የፓርቲ አገነባብ ጉዳይ :— ቀደም ሲል በገለጽ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ላይ የወዛደር ሊግ ያለው አቋም በመርሆዊ ትግል ላይ የተመሠረተ ነው:: የድርጅትም የመተዳደርያ ደንብ፣ "የወዛደር ፓርቲ ሊቋቋም የሚችለው በማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅቶች ውህደት መሆኑን ሊግ ያምናል" ይላል::

ለ/ የግንባር አመሠራረት ጉዳይ :— ይህንን ዐቢይ ጉዳይ በሁለት መስክ እንመለከተዋለን:: አንደኛው መስክ በአሁኑ ተጨባጭና አሳሳቢ የኢትዮጵያ ሁኔታ አብዮታዊ ማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅቶች ከመዋሃዳና ፓርቲ ከመፍጠራቸው በፊት አያሌ የትብብርን፣ የመረዳዳትና አብሮ የመሥራት ደረጃዎችን ማለፍ፣ በዚህም ወቅት በፖለቲካ መሥመራቸው ላይ የአስተሳሰብንና የተግባር አንድነትን መቀዳጀት አለባቸው:: ያለበለዚያ ፓርቲው ራሱ ስሜታዊና አየር ወለድ ይሆናል::

አሁን በሚገኙት ሀቀኛ የኮሚዩኒስት ድርጅቶች መካከል የመተባበር አሠራር /ኮኦፕሬቲቭ ወርክ/ በከፍተኛ ደረጃ መጀመር ይኖርበታል:: እስካሁን ድረስ እርግጥ አንዳንድ የመተባበር እርምጃዎች ተወስደዋል ብለን እንገምታለን፣ ግን አጥጋቢና አቀራራቢ በሆነ ደረጃ ተካሂደዋል ብለን አናምንም:: ይህ የትብብር አሠራር፣ ድርጅት ለድርጅት በአሳሳቢ የአብዮት ጉዳዮች ላይ መወያየትን፣ ሰነዶችን መለዋወጥና ማጥናትን አንዱ በሌላው ልሳን ላይ በድርጅቱ ስም ጽሑፎችን ማውጣትን፣ ሰነዶችን አንዱ ለአንዱ ማሰራጨትን፣ ወዘተ... የሚመለከት ነው::



የትብብሩ ደረጃ አጥጋቢ ውጤትን ሲያሳይ ወደ ግንባር ደረጃ ለመሄድ ይቻላል:: በማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅቶች መካከል የግንባር አሠራር የመቀየሩ ቀንና ወደ ፓርቲ መመሥረት የሚደረገው ጉዞ ያፋጥነዋል:: የግንባር አሠራር፣ የትብብር አሠራር የሚያዝሏቸውን ፍሬ ነገሮች ከማዘለም በላይ ተጨማሪና የበለጠ አቀራረብ የሚያደርጉት እርምጃዎችን የሚያዝል ነው:: በግንባር አሠራር ውስጥ፣ የድርጅቶች አመራሮች በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ የጋራ መግለጫዎችን በማውጣት የድርጅቶቹ ካድሬዎች ከላይ እስከ ታች በመተባበር እጅ ለእጅ ተያይዘው አብዮቱን እንዲያራምዱ ይደረጋል:: ግባር የሚመሠረተው በእኩልነትና በድርጅት ነፃነት መርህ ላይ ነው:: ድርጅት ለድርጅት በበሰበ ለበሰበ ሊገባበዘ ይችላል:: የግንባር አሠራር በሕዝብ ሊሳሰስና ሊጠበቅ የሚችል መሆን ይኖርበታል::

የግንባር ደረጃ አጥጋቢ ውጤትን ሲያሳይና ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ፈቅደው በሚገኙበት ወቅት የውህደትና የፓርቲ ማቋቋም ደረጃ ሊከተል ይችላል:: እነዚህን ሶስት ደረጃዎች ገንጥሎ ማየት ተገቢ አይሆንም:: ሶስቱም አንደም ናቸውና:: የአብዮት ማዕበል፣ ሂደቱ የሚወስናቸው ነገሮችና ደረጃዎች ናቸው:: በአንድነት ሊካሄዱ ይችላሉ፣ ደረጃ በደረጃም ሊካሄዱ ይችላሉ::

በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ የትብብርንና የግንባር አሠራርን እናራምዳለን:: ለዚህም፣ ለማገናወም ፀረ—ሶስት የማርክሲስት—ሌኒኒስት ድርጅት አሁን ያለውን ፀረ—አብዮት ሁኔታ በበለጠ ለመቋቋም እንዲችል በእኩልነትና በድርጅት ነፃነት ላይ የተመሠረተ ግንባር እንዲንፈጥር የወዛደር ሊግ ጥሪ ያደርጋል:: የወዛደሩን ፓርቲ የመመሥረቱን ጉዳይ ለማፋጠን የምንችለው በዚሁ ዓይነት እርካብ መሆኑን እናምናለን::

ሌላው ግንባር በሁለተኛው መስክ ላይ ሊፈጠር የሚችለው ግንባር ሰፊ ሰፊ መደቦች በሰፊ ሰፊ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ወይም ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካኝነት የሚፈጠር ፀረ—ሶስቱ ግንባር ነው:: የአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ፊት የጠቀስነውን ግንባር በቅድሚያ እንድንመሠርት ያስገድደናል:: ያንን ግንባር ሳንመሠርትና ከሚቀጥሉትን ሳናጠናክር ሌላ ርዕዮተ ዓለም ከሚከተሉት ጋር ግንባር፣ ግንባር ብለን ጥሪ ብለን የአብዮታችን ሂደት እንዲዛነፍ ልናደርግ እንችላለን::

## ጠ/ በኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ላይ* የወዘደር ሴግ በአሁኑ ጊዜ ያለው

### አቋም

በአሁኑ ወቅት፣ በኢትዮጵያችን ስለመንግሥት ሥልጣን ጉዳይ አጢነን ስንመለከት የሚከተለውን ሀቅ እናገኛለን:: ወይ ሥልጣኑ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት እጅ መቆየት አለበት፣ ወይም ደግሞ ከአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ እጅ መግባት አለበት ከእነዚህ ሁለት ኃይሎች ውጪ በውነቱ ሥልጣን ለመያዝና ለማቆየት የሚችል ኃይል በአሁኑ ጊዜ የለም:: በተለይም ደግሞ፣ ተራማጅ የሆነ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ታዋቂነት ያለው ኃይል ወይም ጦር ያለው የፖለቲካ ፖርቲ ወይም ድርጅት የለም:: "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ተብሎ በአድሃሪያንና በአናርኪስቶች የሚነፋፋው ቅዠት በተግባር ላይ ሊውል አይችልም:: ሰፊው ሕዝብና አብዮተኞችም ሊቀበሉት አይችሉም::

እንግዲህ ባለው የውስጥ ተጨባጭ ሁኔታ ቀደም ሲል በተተነተነው የውጭ /ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢ ፊውዳል-ቡርዧ/ ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ ጦር በአሁኑ ጊዜ መከፈል፣ ወደ እርስ በርስ መታከስ ሊያመራ ይችላል:: እርስ በርስ መታከስ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የሚበጀው ለአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴና ለመንገሻ ሥዩም ብቻ ነው:: ሰፊው ሕዝብ ሲጨሰ፣ ሲታከስና ሲዋጋ ሁኔታው፣ የመንግሥት ሥልጣን የመያዙ ዕድል ለፀረ-አብዮት ኃይሎች እንጂ ለአብዮት ኃይሎች አይደለም:: ስለሆነም፣ በኢትዮጵያ ጦር ውስጥ የተደራጀና የተቀናበረ የሶሻሊስት ሳይንስ የፖለቲካ ትምህርት በማያደርጥ ሁኔታ መስጠትና በመለስተኛ ፕሮግራም አካባቢ አንድነትን መቀዳጀትና ማጠናከር በየጊዜው ተቀዳሚ ተግባር ነው:: ይሀንን፣ ዐብዮቱ በአሁኑ ጊዜ እጅግ የሚፈለገውን የሠራዊት አንድነት ለማግኘት ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ነው::

1. በሠራዊቱ ውስጥ ያለውን የፊውዳል-ቡርዧ ቢሮክራሲ መደምሰስ
2. በሠራዊቱ ውስጥ ያሉትን የፊውዳል-ቡርዧ ስለላ ድርጅቶች መደምሰስ
3. በሠራዊቱ ውስጥ ያሉትን አድሃሪያን መንጥሮ ማውጣት
4. የሠራዊቱን ጊዜያዊ ኤኮኖሚያዊ ችግሮች ማቃለል
5. በመኮንኖችና በባለሌላ ማዕረጎች መካከል ያለውን የፊውዳል-ቡርዧ ግንኙነቶች ከአሁኑ ማጥፋት

---

* በአሁኑ ጊዜ ስለፖሊስ ሠራዊት ለመሰንዘር የምንፈልገው አቋም፣ ደረጃ በደረጃ አብዛኛውን ተግባሮችን ለሰፊው ሕዝብ እንዲያስተላልፍ ሆኖ ወደፊት ሕዝባዊ የሆነ ፖሊስ እንዲደራጅ ነው:: የስለላው ድርጅት ግን ያለጥርጥር መጥፋት ይኖርበታል:: የፀረ-አብዮት ኃይሎች ስላይ ለአብዮት ኃይሎች ደህንነት ሊሠራ አይችልም::



6. ሠራዊቱን ከአሁኑ፣ በምርት ተግባር ላይ ማሠማራትና ከሰፊው ሕዝብ ጋር እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ::

ብዙዎች የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች በትምህርትና በትግል ወደ ሶሻሊዝም ሊሳቡና ለነገው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ቀይ ጦር መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ የሚል እምነት አለን::

## ጡ/ ነፃነትና ትጥቅ ለገበሬው

የኢትዮጵያ ገበሬ፣ መሬቱን ካገኘ እነሆ ሁለት ዓመታት ሊሆኑት ነው:: ይሁንና፣ በዚህ በተቀዳጀው የኤኮኖሚ ድል በሚገባ ለመጠቀም የሚችለው የፖለቲካ ኃይሉንም ጭምር ሲጎናጸፍ ብቻ ነው:: ነፃነት፣ ድርጅትና ትጥቅ ስለሌለው፣ የተወረሰው የመሬት ከበርቴ ሁሉ ከቢሮክራሲው ጋር በመመሳጠር ገበሬው የኤኮኖሚ ድሉን ፍሬ ያለስጋት እንዲበላ አላስቻሉም:: ስለሆነም፣ በአሁኑ ጊዜ አንገብጋቢ የሆነው የገበሬ ጥያቄ፣ የአድሃሪ የመሬት ከበርቴዎችንና የጭፍሮቻቸውን ትጥቅ ለማስፈታትና አስፈላጊውን አብዮታዊ እርምጃ እንዲወስዱበት የሚያስችለውን ሥልጣንና ነፃነት ማግኘት ነው:: በተጨማሪም የተደራጁት የገበሬ ማኅበራት ሠራዊት በአስቸኳይ ትጥቅን እንዲያገኙ ያስፈልጋል::

ነፃነትና ትጥቅ የገበሬው
ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይታወቁ
የኮሚኒስት ድርጅቶችን ግንባር እንመሥርት

# የአብዮታዊ ሰደድ ፕሮግራም

## ክ ፍ ል 1

### መ ግ ቢ ያ

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ብዙ መራራና መስዋዕትነት የተሞላበት ትግል አካሂዷል::

በዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ በኢምፔሪያሊስት የጭቆና ቀንበርና ቀኝ ተገዥነት ሥር ለነበሩ አያሌ ሐገሮች አንጋፋና አርአያ መሆኑ ለአዲሱ የኢትዮጵያ ትውልድ የወዝ አደሩ ርዕዮተ ዓለም ደመኛ ጠላት የሆኑትን ኢምፔሪያሊዝምን፣ ፊውዳሊዝምንና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝምን ለመውጋት የሚያኮራ የታሪክ መነሻ ሆኖታል::

ኢምፔሪያሊስቶችና ሌሎችም የመስፋፋት ዓላማ የነበራቸውን የየጊዜውን አምባገነኖች የወረራ ሙከራ አሳፍሮ በመመለስ የታወቀ ቆራጥና ለነፃነቱ ተጋዳይ ሕዝብ በውስጡ ያሉትን ጨቋኝና በዝባዥ የገዢ መደቦች በማስወገድ መሠረታዊ ለውጥ ለማድረግ ተስኖት ኢትዮጵያ እጅግ ወደኋላ ቀር ተብለው ከሚባሉ ደሃ አገሮች አንዷ ሆና የጭቁኖች እስር ቤት እስከመባል በተደረሰ አብዮት የዘገየበት ምክንያት ምን ይሆን የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል::

የዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ መልሱ ጭቁኑ ሕዝብ በያለበት ሲያደርግ የነበረው ጥረት የሚያስተባብር ድርጅትና ጠቅላላ የፖለቲካ ንቃት ጉድለት ቢሆን ለእነዚህ ጉድለቶች ምክንያት የሆኑ ሐቆች አሉ::

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ፀጋና ውበቷ እንዲሁም የሚያግራራ አቀማመጥ ኢምፔሪያሊስቶችና ቀኝ የግዛት አስፋፊዎችን ዓይን ማራኪ በመሆኗ የተደጋገሙ አያሌ ጥቃቶች ደርሰውባታል:: ይህንኑ ለመቋቋም ሰፊው ሕዝብ የውጪ ወራሪ ኃይላት የሰነዘሩበትን የተደጋገመ ጥቃት ለዘመናት ተንሰራፍተው ሲመዘብሩት ለመኖር ችለዋል::



ሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ኑሮ እድገቱን እንዳያሻሽልና በጊዜው ተራማጅ ከነበሩ የዓለም ሕብረተሰቦች ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ የባሕር በሮቹ በኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ተዘግተው ኖረዋል::

የአካባቢው አድሓሪ ኃይሎች በየጊዜው እየተባበሩና ፀብ እየጫሩ ፋታ ከመንሳታቸውም ሌላ በሕብረተሰቡ እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሲያደርጉ ኖረዋል:: እያደረጉም ናቸው::

በውስጥም ነገሥታቱ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ሰለጣኑ ባላባቱ ሹገሬቶንና ሕዝቡን በጎሣ፣ በቋንቋ በሃይማኖት ከፋፍለው ይረግጡትና ይመዘብሩት ስለነበረ ጭቁኑ ሕዝብ የተለያዩ የተበታተነ ትግል እንዲያካሂድ መገደዱ ሐቅ ነው::

እነዚህ የተለያዩ የገዢ መደቦች በግል ጥቅም ዝናና እንዲሁም በሥልጣንና በዘውዱ ፍላጎት እርስ በርሳቸው በተጋጩ ቁጥር ሰፊውን ሕዝብ እርስ በርሱ ሲያፋጁት ከመኖራቸውም በላይ አልፎ አልፎም አንዳንዱ ከጠላቶች ከባዕድ ጋር እየተመሳጠረ የውጪ ኃይል በማስመጣት ጭቁኑን ሕዝብ የማገዱበት ጊዜ አለ::

አብዮት የዘገየበትን ምክንያትና ስለ ኢትዮጵያ የኅብረተሰብ እድገት አንዳንድ ሐቆችን ለመግለጽ በተለይ በመሳፍንቱ ዘመን ላይ ብናተኩርም የተለያየው ፊውዳላዊ የገዢ መደብ በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ዘውድ ከተጠቃለለበት ጊዜም ወዲህ የነበረው ሁኔታ ጭራሽ የከፋና የመረረ ነበር::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በረጅም ዘመን የትግሉ ታሪኩ የተደራጁ ፊውዳላዊ የገዢ መደቦች እየተፈራረቁ በማቆጥቆጥ ቢጨቁኑትም ግፋንና በደሉን አሜን ብሎ የተቀበለበት ጊዜ ሳይኖር የተበታተነም ቢሆን እየወደቀ እየተነሳ ትግሉን ቀጥሏል::

ወደ ኃይለሥላሴ ጊዜ ማለትም በፍጹም ፈላጭ ቆራጭ በሆነው ጉልታዊ ሥርዓት ማህበር ውስጥ የካፒታሊስት ስልተ ምርት ከተቀላቀለ ወዲህ የአርሶ አደሩና የወዝ አደሩ ንቃተ ሕሊና ከፍ እያለ በመሄዱ ጭቆናውና ምዝበራው ይበልጥ ይሰማውና ይቆጠቁጠው ጀመር:: አልፎ አልፎም አጠገቡ በሚያገኛቸው የጉልታዊው ሥርዓት ተጠሪዎች ላይ አመጸ::

የኢትዮጵያ ተራማጆች በግለሰብና በቡድን ደረጃ በግልጽም በስውርም፣ በውስጥና በውጭም ሕዝቡን ለማንቃትና ለመቀስቀስ ቢሯሯጡ ከጨቋኙ የገዥ መደብ ጋር ፊት ለፊት እየተጋፈጡ ሕይወታቸውን የሰዉና የተሰደዱ አያሌ ናቸው:: አብዮቱና አንጃ አቢዮተም አደጋተም እንጂ አሁን በመካሄድ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የረጅም ጊዜና የብዙሃኑ የትግል ውጤት ነው::

ክ ፍ ፍ 2

አብዮታዊ ሰደድ

አብዮታዊ ሰደድ የትኛው ነው

አብዮታዊ ሰደድ በነፃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ ትግል በሚያምኑ ጠቁና ታጋዮች የተገነባ፣ ለኢትዮጵያ ጭቁን መደቦችና ጠቁና ተራማጆች ኃይሎች የትግል አጋርና መከታ፣ በመሆን አቢዮታዊ ድርሻውን የሚያበረክት፣ ለኢምፔሪያሊዝም፣ ለፊውዳሊዝምና ለቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መቅሰፍት ነው::

አብዮታዊ ሰደድ የኢትዮጵያን የወዝ አደር ፓርቲ ለማቋቋም በሚደረገው ትግል ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግን አጢኖና ዋና ተቀዳሚ ዓላማው አድርጎ የተነሣ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት ነው::

አብዮታዊ ሰደድ ይህ የፈጠነና የተፋፋመ አብዮት በአስቸኳይ በወዝ አደሩ ፓርቲ ካልተመራ ከቀለበሰ እንደሚይዉንና የወዝ አደሩንም ፓርቲ ለማቋቋም የሚቻለው በጠቁና ተራማጅ ድርጅቶች ኅብረት መሆኑን አጥብቆ የሚያምን ድርጅት ነው::

አብዮታዊ ሰደድ ጠቁና ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ የተገነዘቡ፣ ለዘለቄታ ትግልና ድል የሚደራጁ፣ በወዝ አደሩ የበላይ መሪነት የሚያምኑ በቁራጥ አቢዮተኞች የተገነቡትን ማርክሲስት-ሌኒኒስት ድርጅቶች ነው::



ክ ፍ ል 3

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም:

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መለስተኛ ፕሮግራም የሰደድ አቋም ከብዙሃኑ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ-ፊውዳሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ማርክሲስት-ሌኒኒስት ድርጅቶች የተለየ አይደለም::

ኢትዮጵያ አብዮታዊ ማዕበል ውስጥ ከገባችበት ወቅት አንስቶ በፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመደብ ጠላቶቹ ላይ አያሌ ድሎችን ተቀዳጅቷል :: የተገኙትን ድሎች አጠናክሮና ዘላቂነታቸውንም በሚገባ አረጋግጦ ሌሎች ድሎችን ለማስፋፋት የሚቻለው በኢምፔሪያሊዝም፣ በፊውዳሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መቃብር ላይ በመሆኑ ወደዚህ ግብ የሚያመራው ትግል ለአድኃሪ ኃይሎች አንዳችም ፋታ ሳይሰጥ ወደፊት መገስገስ ይኖርበታል::

የአብዮቱን ወዳጆችና ጠላቶች በጥንቃቄ ተተንትኖ ነው መለየት ይኖርባቸዋል:: የአብዮቱን ወዳጆች በሙሉ መሰብሰብና ማጠናከር፣ የአብዮቱን ጠላቶች ማዳከምና መበተን ያስፈልጋል:: በሁለቱ አጋዦች መሃከል ሆነው ግራና ቀኝ የሚያስተውሉት ወገኖች የፀረ አብዮት ኃይሎች ጎራ እንዳይጠናከር በብልሃት መያዝና ወደ አብዮቱ ሠፈር እንዲገቡ መታገል ያስፈልጋል::

ይህንን የትግል ስልት በሥራ ላይ ለማዋል የአብዮቱ ኃይሎች በሙሉ ዓላማቸን በለጠ የሚያጠናክሩበትና የሚተባበሩበት የጋራ መድረክ ያስፈልጋል:: የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ፊውዳሊዝምና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት የሆኑ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎችን የጋራ በሆነ ዓላማ ላይ የሚሰበስብ፣ ለዚህም የሚያስፈልጉትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ጉዳይ መሠረታዊ ፈለጎች በሚገባ የሚጠቅም በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል የተገኘ ሳይንሳዊ ፕሮግራም በመሆኑ አብዮታዊ ሰደድ ይህንን ፕሮግራም ከሚደግፉ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ የወዝ አደሩን ፓርቲ መመስረት ተቀዳሚ ዓላማው አድርጎ የተነሣ ድርጅት ስለሆነ፣ ይህንን ፕሮግራም የራሱና የመላው ሰፊ ሕዝብ አብዮት ፕሮግራም እንጂ ከወታደራዊው ደርግ የተሰጠ ምፅዋት አድርጎ አይመለከተውም::

አብዮታዊ ሰደድ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በአጠቃላይ እንደ ራሱ ፕሮግራም አድርጎ ሲቀበለው ከዚህ የሚከተሉትን አጭር ማብራሪያና ማሻሻያ ጨምሮ ነው::

ሀ./ <u>በገጠር መሬት አዋጁ ረገድ</u>

የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገው የየካቲት 25/67 ዓ.ም አብዮታዊ አዋጅ በሥራ ለመተርጎም የተቋቋመው የመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስቴርና በዚሁ አንፃር የተከሰፈው የእድገት በሕብረት ዘመቻ መምሪያ አቅዶቹ፣ ዝግጅቶችና እንዲሁም ሰምሪቶች ይህ ታሪካዊ አዋጅ ከሚጠይቀው የሥራ ስፋትና ጥራት ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆናቸው የተፈጠሩትን ጉድለቶች እያሻሻሉ ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል የሰፊው ሕዝብ አጋሮች ሲታገሉና ሲገነቡ፣ ያለ ጥናት የተሳኩት አድኃሪዎች ያፈርሱ ስለ ነበር፣ ሰምሪቱ በከፊል ፀረ-አብዮት ሰምሪት ነበር ለማለት ይቻላል::

ከዚህ ሌላ አዋጁ መሬትን ለአራሹ ያደርግ እንጂ በሬት ባለሀ አርያ ሆኖ ይታያል:: ስለሆነም በለምና በጠፍ፣ በጠባብና በሰፊ የቀደሞ ጢሰኞች ይዞታ በሩ፣ እትክልት፣ ወዘተ... የመሰሰሉ ድሚ ባለሆኑ ከፍያዎች በጠቅላላው እንደ መሬቱ እንደገበሬው ቸሉታና እንደ ቤተሰቡ ብዛት ፍርጉ ለማቀራረብና ለማመሳሰል የሚለው የአዋጁ አንቀጽ ኃሳብ በአብዛኛው ክፍል በሥራ ላይ ባለመዋሉ፣ ሁለት ዓመት ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ የተለያዩ የገበሬ መደቦች ሲፈጠሩና በአንዳንዱ ቦታ ለምሳሌ በጭላሎ፣ በአርሲ፣ በሀመራ፣ በከፍለ ጠገርም ደረጃ በወለጋ፣ በከፋና በጠረርጌ የገጠሬ አብዮት የመሬት ከበርቶቹን በማደራጀት ላይ ይገኛል:: በአብዛኛው ሰሜን ኢትዮጵያ የመሬት አዋጁ ወረም የቀነሰ ስለማይመስል ይህ አደገኛ ፀረ አብዮት ሁኔታ ስር ከመሰደዱ በፊት ተራማጅ ኃይሎች መረባረብ ይኖርባቸዋል:: በገጠሬ አርስ አደር መካከልም የተለያዩ መደብ እንዳይፈጠር ጠቅና ተራማጆች ገበሬው በሬ ያጡ የሀብረት እርሻዎችን እንዲያቋቁም ማነቃቃትና መገፋፋት አለባቸው::

ለ./ <u>ስለ ብሔረሰቦች</u>

በብሔረሰቦች ጉዳይ ላይ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የተሰኘው ማርክሲስት-ሌኒኒስት መርህ ሳይንሳዊና ትክክለኛ መርህ መሆኑን ሰደድ ይቀበላል::

ይህ መርህ ለሶሻሊስቶችም ለኢምፔሪያሊስቶችም የሚደገፍበት የተለያየ መልክና ይዘት አለው::



ሶሻሊስቶች ለሰው ልጅ ፍትህ ነፃነትና እኩልነት ብለው ሲገለገሉበት ኢምፔሪያሊስቶች ደግሞ ሶስተኛውን ዓለም ለመከፋፈልና ለመበዝበዝ ዋና መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል::

በመሠረቱ የብሔሮችና የብሔረሰቦች የመገንጠል ጥያቄ ከመደብ ትግል ተገንጥሎ የማይታይ ቢሆንም ጥያቄው የሚመጣው ከወዝ አደሩ ሣይሆን ከቡርዧው መደብ ነው::

የዓለም ሕብረተሰብ በመደብ፣ ዓለም በጠቅላላ በኢምፔሪያሊስትና በሶሻሊስት ሁለት ፊና ተከፋፍለው በሚገኙበት በአሁኑ ጊዜ ሶሻሊስቶች ለዚህ ጥያቄ አቋም ከመውሰዳቸው ወይም ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት የትኛውን መደብ ለመጥቀም፣ የትኛውን ወገን ለማጠናከር ብለው መጠየቅ ይኖርባቸዋል::

አብዮታዊ ሰደድ ይህንን መርህ የሚቀበለው የጥያቄውን መሠረታዊ ምክንያት፣ መነሻ፣ መድረሻ የአከባቢውንና እንዲሁም የጊዜውን የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ከዓለም ጭቁን ሕብረተሰብ ነፃነት፣ የመደብ ትግልና ከዓለም አቀፋዊው ኮሚዩኒስቶች ንቅናቄ ጋር አዛምዶ በማየት ማርክሳዊ የሆነውን ጽንሰ ኃሳብ በተግባር አተረጓጎም ጋር ነው::

ሐ./ <u>በትምህርት ረገድ</u>

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዘጠኝ ነጥቦች ውስጥ በተራ ቁጥር 4 ፊደል ተራ /ሀ/ ""ለሰፊው ሕዝብ እድገትና የተሟላ ኑሮ የሚያገለግል ለሰፊው ሕዝብ ልጆች በሙሉ የሚዳረስ፣ ለፀረ-ፊውዳል፣ ለፀ ለፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስትና ለፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያግዝ ነፃ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እንዲስፋፋ ይደረጋል""ይላል::

አብዮታዊ ሰደድ በነዚህ በሚማርኩ ቃላት ብቻ በመርካት ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ አድበስብሶ አያልፈውም::

ትምህርት በነፃ ሲባል ምን ማለት ነው? ደረጃ በደረጃ ሲባልስ ከየት በመጀመር ነው? ከዚህ ሁሉ በፊት እስከ አሁን ማነው የተማረው? ማነው ያል ተማረው? ማነው የሚማረው? ማነው የሚያስተምረው? እንዴትስ? በተከታይ ጥያቄዎች ይነሳና በዚህ ላይ ያለውን አቋም ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል::

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከትውልድ እስከ ትውልድ ያለፈ ዘመኑን የፈጀው ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ በሆነ የፊውዳል ሥርዓተ ማህበር ውስጥ ሲሆን፣ የካፒታል ስልተምርት ሥር የተከለው ባለፈው አርባ ዓመታት ውስጥ ነው::

ኢትዮጵያ በከፊል ገባርታዊና በከፊል ከበርቴያዊ ስልተምርት ውስጥ ነበረች ብለን የምንቆጥረው ከአንድ ጉልማሣ መጠነኛ እድሜ ያልበለጠ ጊዜ ነው::ይህም በተለይ ኃይለ ሥላሴና ገበረአበረቹ ከአውሮፓ ሸበታቸው ተመለሰው የበዘበዛ ቃል ኪዳን ጌቶቻቸውን የካፒታሊስት ስልተምርት በኢትዮጵያችን እንዲያስፋፉ በረገ ወለል አድርገው ከከፈቱላቸው በኋላ ነው:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ለከፊል ገባርታዊና ለከፊል ከበርቴያዊ ስልተምርት ተስማሚ የሚያገለግሉ ባለሞያዎችና ቢሮክራቶች የሚፈጠርበት ሥርዓተ ትምህርት ተቀየሰና ትምህርት ቤቶችም ለዚሁ ዓላማ ብቻ መስፋፋት ጀመሩ::

በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የተገለገሉባቸውና ወደ ውጭም እየተላኩ የተማሩት የመሳፍንቱና የመሬት ከበርቴው ልጆች ብቻ ሲሆኑ በዚህ እድል የተጠቀሙ የሰፊው ሕዝብ ልጆች በጣም ጥቂት ናቸው:: ሰፊውን የትምህርት እድል በሰፊው የተካፈሉት ከስልተ ምርቱ ጋር ግንኙነት የነበራቸው የመሬት ከበርቴ ልጆች ከፊል ገባርታዊና ከፊል ከበርቴያዊ ስልተምርት የፈጠረላቸውን የሥራ መስኮችና ወገኖች ተሸምተው ይዘዋል::

ከሰፊው ሕዝብ ወገኖች በስተቀር ከፊሉን የትምህርት መስክ የያዙት የእነዚህ አድሃሪያቶች ሕልምና ቅዠት በኢትዮጵያ ሥሩን የተከለው የካፒታሊስት ስልተ ምርት ያበባል ይጎመራል እንጅ አብዮት መጥቶ ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል፣ የሰፊው ሕዝብ ልጅ ይማራል የሚል አልነበረም:: ለዚህም ጠበቃ ማስረጃው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መካሄድ ከጀመረበት ወቅት አንስቶ ተማሪያቸውን ትምህርት ቤቶችን በፀረ—አብዮት ካምፕ ውስጥ አሰልፈው በሰፊው ሕዝብ አብዮት ላይ ታሪክ የማይረሳውን ወንጀል በመፈጸም ላይ መገኘታቸው ነው::

ደግሞ እነዚህ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስቶች ለፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያገዝ ትምህርት ይሰጣሉ ብሎ በአሁኑ ዘመን መቀበል አስቦ እንደሆነ እጅግ ተሳስቷል:: ስለሆነም:—



1. ትምህርት በነፃ ማለት ማእከላዊው መንግሥት በመላው ኢትዮጵያ ት/ት/ቤቶችን ሠርቶ የትምህርት መረጃዎችንና መምህራንን ሰጥቶ፣ በነፃ ያስተምራል ብቻ ሣይሆን ተቀዳሚ መሠረታዊ ከሆኑት ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ፣ እንደ መጠለያ፣ እንደ ሕክምና ሰፊው ሕዝብ እራሱን በራሱ መርዳት ከተሰኘው መሁ ግንኙሎ እንዳይመለከተው ግልጥልጥ አድርጎ ማስረዳት ያስፈልጋል::

2. በፊውዳሉ ሥርዓተ ማህበር ሲደረግ እንደነበረው ሁሉ የሚጀምር ተውና የትምህርት ታክስ የሚከፍለው ሌላ፣ የሚማረው ሌላ ሣይሆን የትምህርት ደረጃው ከእናቱ ጡት፣ ከታች በመስፋት ለሰፊው ሕዝብ ልጆች ቅድሚያ መስጠት አለበት::

3. ነፃ ትምህርት ለነፃ ሕዝብ የተሰኘውን መሁ የሚያስፈጽመው ቢሮክራቱ ሣይሆን ሰፊው ሕዝብ ስለሆነ ከከሉጆችና ከእንዳንዱ ጭራ ትምህርት ቤቶች በስተቀር የተቀረት ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ከፍተኛ ት/ቤቶች ድረስ በሰፊው ሕዝብ ቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው::

ይህንን ለማስተባበርና ለመርዳት የመንግሥትም ኃላፊነትና ድርሻ በአንጻሩ ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል::

መ./ <u>ስለ ኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች፣ የፀጥታ አስከባሪና ሕዝባዊ ሠራዊት</u>

አብዮታዊ ሰደዱ እንዳንዱ በተራማጅ ለሰጠን የሚናገሩ አድሃሪ ቡድኖች የጭቆናን መሳሪያ ለባሽ ጠቋሚ ትግልና የሰፊው ሕዝብ አጋርነትን በሙሉ <u>አረም ለማለብበ</u> የሚስነዝሩትን ፀረ አብዮት አስተያየት አጥብቆ በመቃወምና ሠራዊቱ የአብዮት ኃይለት መሆኑን በማመን አጽመን ከዚህ እንደሚከተለው ይገልጻል::

1. የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች፣ የፀጥታ አስከባሪና የሕዝባዊ ሠራዊት አባሎች ኢምፔሪያሊዝምን ፊውዳሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን፣ ከኢትዮጵያ ፈጽሞ ለመደምሰስና ሕብረተሰባዊ /ሶሻሊዝም/ሥርዓት ገንብቶ ሰፊውን ከጭቆናና ከበዝበዛ ነፃ ለማውረግ የሚያስችለውን ርዕዮተ ዓለም /ማርክሲዝም—ሌኒኒዝምን/በሚገባ መታጠቅ አለባቸው::

2. የመከላከያው ኃይል ባዕድ ሠራሽ በሆነ መሣሪያ ብዛትና ጥራት ላይ ብቻ ያዘነበለ ሣይሆን ከመሣሪያው ኋላ ባለው ቆራጥ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብአዊ ወታደርና አርሶ አደር ብቃትና በራስ የመተማመን ችሎታ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት::

3. በጦር ኃይሉ፣ በፀጥታ አስከባሪውና በሕዝባዊ ሠራዊት ውስጥ ያሉ ተቋሞች ሁሉ እራስን በራስ መርዳት /ሰልፍ ሪሊያንስ/ በተሰኘው መርህ መሠረት ማናቸውንም በወታደራዊ ግዳጅና እንዲሁም ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች ከአካባቢ በአካባቢው ለመፍጠር፣ ለማምረትና ለመጠቀም መቻል አለባቸው::

4. መለዮ ለባሾች ከመደበኛ ሥራቸው ሌላ ከወዝ አደሩና ከአርሶ አደሩ ጋር ተባብረው የሐገራቸውን ኢኮኖሚ መገንባት የሚችሉበት አቅጣጫ ለምርት ሥራ መሰማራት ይኖርባቸዋል::

5. ከመለዮ ለባሹ መካከል በቀደመው ሥርዓት የተበከሉ አድሃሪያዊያንና ወላዋዮች መጋለጥ አለባቸው::

6. የኢትዮጵያ አንድነትን፣ ብሔራዊ ነፃነትና አብዮቱም የሚጠበቀው በጥቂት መለዮ ለባሾች ብቻ ሣይሆን በሰፊው ሕዝብ ስለሆነ ወዝ አደሩና ገበሬው በአጠቃላይ መታጠቅና በጦር ስልትም መደራጀት አለባቸው::

## ክ ፍ ል 5

## ስብሰባ ጉዳዮች

### ሀ./ የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች

በአብዮት ወቅት የኢምፔሪያሊዝም አደገኛነት በኢትዮጵያችን በትክክል የታወቀ አይመስለም:: አብዮት በያለበት በመፈንዳቱ በአሁኑ ጊዜ የሰፊው ዓለም ሕዝብ ድምጽ በጥቂቱም ቢሆን በማስተጋባቱ፣ የወተርጌት ቅሌት፣ የሲ አይ ኤ መጋለጥና በተለይም በቬትናም በደረሰበት ወደር የሌለው ውርደት ተደናግጦ ስልቱን ለመለወጥ ስለ አደባ ደርጎ ኢምፔሪያሊዝም የተኛ መስሎታል::



ኢምፔሪያሊዝም ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች ቀስቅሶ የብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ደም ከጠጣ በኋላ ከጭቆናና ከብዝበዛ አርነት ነፃ ለመውጣት በሚታገሉት በሩቅ ምሥራቅ ሕዝቦች ላይ በጽኑ በማተኮር ላለፉት ሃያ ዓመታት ጭቁኑን ሕዝብ በቦምብና በናፓል ማቃጠሉን የዘወትር ሥራው አድርጎ ስለነበር፣ የአፍሪካ ሕዝብ በመጠኑም ቢሆን ንቅናቄ ማድረግ ችሎ ነበር::

ኢምፔሪያሊዝም የኮሪያ፣ የቬየትናም፣ የካንቦዲያና የላኦስ ተጋዳይ አርበኞች ረግጠው ስለአስወጡት ፊቱን ወደ መካከላዊ ምሥራቅና በተለይም ወደ አፍሪካ በማዞር፣ በዛየር፣ በግብጽ፣ በሳውድ አረቢያ፣ በሰሜን የመን፣ የሱዳንና በኬንያ ውስጥ ሲ አይ ኤን በማጠናከርና በሕንድ ውቅያኖስና በአትላንቲክ ውቅያኖስ በደቡባዊ ክፍል የሚያደርገውን ንቅናቄ አጢኖ ለተመለከተው የአንጎላን፣ የኢትዮጵያንና የደቡብ የመንን ሕዝባዊ አብዮት ለማነቅ መሆኑ ገለጽ ነው::

ኢምፔሪያሊዝም በአፍሪካ ላይ የነበረውን ንቀትና የተዛባ አስተያየት የኢትዮጵያና የአንጎላ ሕዝብ ንቅናቄ እንዲለውጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያና የአንጎላ ሕዝብ ንቅናቄ እንዲለወጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያ አብዮት አነሳሱና ሂደቱ ባላሰበውና ባልጠበቀው ሁኔታ ደርሶ ቢያደናግረውም እስከ አሁን ምንም የፀረ-አብዮት ሙከራ አላደረገም ማለት አይደለም::

ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ከአንዱ ስልት ጊዜ አደገኛ ሙከራ አድርጎ ከሽፍበታል:: ሌላ የተቀነባበረ ሙከራ ለማድረግ ኢ.ዲ.ዩ. ወይም የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ዩኒየን በማለት እራሱን የሚጠራውን ፀረ-ሕዝብ የመሳፍንት ቡድን በለንደን፣ በጅዳ፣ በሱዳንና በኬንያ ለፀረ-ሕዝብ ስራ ያዘጋጃል::

የሱልጣን አሊ ሚራህን ቡድን በጅቡቲ፣ ኢ.ኤል.ኤፍን በኤርትራና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን የተሰኘውን የመሳፍንት ገለገል በአሜሪካ ያደራጃል::

### ለ./ ሉ ሎ ች

በኢትዮጵያ ላይ ጊዜ የማይሽረው ጥላቻ ያደረባቸውና የመስፋፋት ዓላማ ያላቸው አንዳንድ የአካባቢው አድሃሪ የገዥ መደቦች ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመመሳጠርና የጊዜውን አጋጣሚ በመጠቀም በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ላይ ፀረ-አብዮት ዘመቻቸውን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ:: ለማስረጃ ያህል :-

1. ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት የኤርትራን መገንጠል ንቅናቄ በስውርና በተመጠነ ደረጃ ሲረዱ የነበሩ ሐገሮች የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከተጀመረ ወዲህ በግልጽና በገፍ የመሣሪያና የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣሉ::

2. የኃይለ ሥላሴ ወዳጅ የነበረው የሱዳን የገዥ መደብ ከኃይለ ሥላሴ ዘውዱ መገርሰስ ወዲህ በኤርትራ የመገንጠል ንቅናቄ ግንባሮች ለመሳፍንቱ ቡድንና ሌሎችም ፀረ ሕዝብ ድርጅቶች ዋና ደጋፊና አስተባባሪ ሆኗል::

3. አብዮታዊ ነኝ የሚለው የጄኔራል ሲያድ ባሬ አምባገነን መንግሥት የጦር ኃይሉን አሰልፎ አስዘምቶ እንኳ አብዮታችንን ለመቀልበስ ያላደረገው ሙከራ የለም::
ለምሳሌ ከአራት ሺህ ያላነሱ ሰርጎ ገብ ወንበዴዎችን አሰልጥኖና አስታጥቆ ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት በኦጋዴን በባሌ የገበሬ ማሕበራት ላይ አያሌ ፀረ-አብዮት ፕሮፓጋንዳና የነፍስ ግድያ ወንጀል በማካሄድ ላይ ይገኛል::

4. አብዮታችን ያስደነገጣት ናይሮቢ የምዕራባውያን መናኸሪያ የኢትዮጵያን ሕዝብ እየገፉ የሚኮበልሉ አድሃሪያዎች ምሽግ ነች::

5. የአረብ ሐገር የልማት መንግሥቶች በ1967 ዓ.ም ካይሮ ላይ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ሱዳን ውስጥ ስድስት ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያስወጣ የአረብ ሐገሮች የጋራ የእርሻ ፕሮጀክት ከተጀመረ አንድ ዓመት ሆኖታል:: ይህንን ታላቅ የእርሻ ፕሮጀክትና የተቀረፁትንም የጎረቤት ሐገሮች ልማት ዘጠና አምስት በመቶ ውሃ የምትመገብ ኢትዮጵያ ስትሆን፣ ኢትዮጵያን የጥቅሙ ተካፋይ ማድረግ ቀርቶ በተመልካችነት እንኳ አልተጋበዘችም::

6. ለአያሌ ዓመታት በፈረንሣይ ኢምፔሪያሊዝም የጭቆና ቀንበር ተጨቁኖ የኖረው የጅቡቲ ሕዝብ ነፃነቱን እንዲያገኝ ከሚደረገው ሻጥር ጋር የኢትዮጵያም ሕዝብ የባሕር በር የለሽ /ላንድ ሎክድ/ ሆና ለእጅ አዙር በዝበዛ እንድትበረከክ የተቀነባበረ ሴራ እየተካሄደ ነው::



7. በውስጥ ደረጃ በሚያባብለው የፊውዳሉ ቢሮክራሲና በሰፊው ሕዝብ መሐከል ታሪካዊ የሆነ የገመድ ጉተታ ትርኢት እና ያለን::

ጠ./ <u>የአብዮቱ ኃይሎች</u>

የኢትዮጵያ አብዮት የለየላቸው ኃይላቸውን አስተባብረው የጭቁኑን ሕዝብ ትግል ለማፈን በሚፍጨረጨሩበት በአሁኑ ወቅት ኃይላቸውን አስተባብረው መደበኛ ጠላታቸውን መደምሰስ ያለባቸው የሕዝብ ወገን የሆኑ ተራማጅ ኃይሎች ቡድናዊና ቀጥኛ ፍልስፍና በሚያጠቃቸው ጠላትና ወዳጅን ለይቶ ባለማወቅ የመደቡን ትግል በማመሰቃቀልና እርስ በርሳቸውም ለመጠፋፋት በማድባት አብዮቱን ሲያዳክሙና ሰፊውን ሕዝብ ሲበድሉ ይታያሉ::

በተለይም የተወሰኑ የሰፊው ሕዝብ ወገን ነን፣ የወዝ አደሩ ፓርቲ ነን የሚሉ ድርጅቶች ወዝ አደሩ እንዳይነቃ፣ እንዳይደራጅ ገበሬው እንዳያርስ፣ ወጣቱ እንዳይማር፣ በጠቅላላው ምርት እንዳይዳብርና በተባበረ ተራማጅ ኃይሎች ትግል የአብዮቱ ሂደት እንዳይሰምር በማድረግ የትግል ዘዴ ብለው የተከተሉት በንኩል የፖለቲካ ዘዴ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ታሪክ የማይረሳው ታላቅ ወንጀል ስለሆነ በአስቸኳይ እንዲታረም ሰደድ እያሳበበ የሚቀጥል ቢሆን ይህን ፀረ-አብዮት ተግባር በቃላት በማውገዝ ብቻ ሳይሆን በተግባር ይቃወማል::

አብዮታዊ ሰደድ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲህ የሚያዝናና ሆኖ አያየውም::

ለጭቁን ተራማጆች፣ ለኢትዮጵያ ወዝ አደሮች አርሶ አደሮች ለጭቁን ወታደሮችና እንዲሁም የአብዮቱ ደጋፊ ለሆነው ሰፊ ሕዝብ ብዙ ውጣ ውረድ የበዛበት ጠመዝማዛና እረጅም የትግል ጉዞ የሚጠብቀን ቢሆንም በተለይ ከፊት ለፊታችን ያለው ጉዞ ታላቅ የፈተና ጉዞ ነው::

የፀረ አብዮት ኃይሎች ከፍተኛ ትብብር፣ ቅንጅትና አንድነት ሲኖራቸው በአብዮቱ ኃይሎች ዘንድ እነዚህ ተሟልተው አይታዩም:: በአብዮቱ ኃይሎች መሐከል በአስቸኳይ ሕብረትን መፍጠር የአብዮቱና የአብዮተኞችም የሞትና የሽረት መጀመሪያ ምዕራፍ ነው::

አብዮታዊ ሰደድ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ አብዮት ከግብ ለማድረስ በትግል ላይ በሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቡድኖችን፣ የአርነት ግንባሮችንና ሌሎችንም ሕዝባዊ ድርጅቶች በሚመለከት ሕብረት የሚጠበቀውን ዝርዝር አቋም በሚቀጥለው ልሣኑ ለሕዝብ ይገልጻል::

በሐቀኛ ተራማጆች መሐከል ኅብረት ይፈጠር::

ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል::

ሰ ደ ድ
=========

ለወገኖች መብራት፣ ለአድሐሪዎች መቅሰፍት::

======////////======



## የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የጋራ መግለጫ

### መ ግ ቢ ያ

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዘመናት እየወደቀ እየተነሳ በደሙና በመስዋዕትነት ያቀጣጠለው የየካቲት 1966 ዓ.ም. አብዮት ዛሬ ይህ ጅምሩ በተነሳ በሦስተ ዓመቱ አደገኛ ከፍተኛና አሳሳቢ የሆነ መድረክ ላይ ቆሞ እናገኘዋለን ::

አብዮታችን ድል በድል እየተጎናጸፈ ወደፊት ሲገሰግስ ሊቋቋሙት ፋታ ያሳጣቸው አድሃሪዎች ዛሬ በውስጥና በውጭ ያሉ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመከራና በትግል፣ የተጎናጸፋቸውን ድሎችና የጉልሙ ፍሬ የሆነውን አብዮቱን ሊነጥቁት አሰፍስፈው ይገኛሉ :: እስካሁን በትግል ከዚህ ደረጃ የደረሰው ሰፊ ሕዝባችም የተጎናጸፋቸውን ድሎች ላለማስደፈርና ሌሎች አዳዲስ ድሎችን ተጎናጽፎ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ከግቡ ለማድረስና ወደሶሻሊዝም ለመሸጋገር የነቃት የድርጅትና የትጥቅ ፋና ብትትሉ ወጣ ውረድ የሞላበትን የአብዮታዊ ትግል ጎዳና በመገፋት ላይ ይገኛል ::

የዘውዱ አገዛዝ ሲገረሰስ፣ መሬት ላራሹ ሲመለስ፣ ወጪቶች ከሰፊው ሕዝብ ሲቀ ሁኑ፣ የማምረቻ የማከፋፈያ ድርጅቶች ወደሰፊው ሕዝብ ባለቤትነት ሲዞሩ፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች የግል ከበርቴዎች የበዝባዥ ምንጭ መሆኑ ሲያከትም፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያ አብዮት ፕሮግራም ታወጀ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የአብዮታችን ይፋ መመሪያ ሲሆን፣ በትግሉና ለመጥፋ ትግል ከአብዮታዊው መለዩ ለበጠ ጉን የሚቆም የነቃ የተደራጀ ሕዝባዊ ጦር በያለበት ሲገነባ፣ አርሶ አደሩ፣ ወዝአደሩ፣ ወጣቱ፣ ጭቁኗ ሴት፣ ተራማጅ ምሁሩና ሰፊው የከተማ ነዋሪ ሕዝብ በትግሉ፣ ለትግል እየተደራጀ አብዮቱን ፈር ሲያስይዝ ይህን ሁሉ እየተመለከቱ አድሃሪ ኃይሎች የሰፊውን ሕዝብ ድሎች አምነው ከመቀበል ፋንታ ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው መሰለፋቸው የጉበኛ ተመሬታቸው ወግ በሰሆነ ተደራጅተውና ታጥቀው በወገኝ ፍልሚያ አብዮታችንን በመፈታተን ላይ ይገኛሉ ::

በዚህ አንፃር ሲታይ ገበታዊ በሆነ ትንንቅ ፈንድቶ ከዚህ የደረሰው አብዮታችን ድሎችን ለመጠበቅና ወደፊት ለመራመድ የሚያስፈልጉት የድርጅትና የትጥቅ ሁኔታዎች በሚገባ እስኪሟላ ድረስ በይበልጥ ለተደራጁትና ለታጠቁት አድሀሪ ኃይሎች የቀለበሳ ሴራ የተመቻቸ ሁኔታ ኃኖራል ::

የኢትዮጵያ ተራማጆች በፊውዶ ፋሽስትም ሥርዓት ዘመን ሆነ ከየካቲት ወዲህ የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄዎች በግንባር ቀደምነት እያነሡ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን ተሰልፈው ሲታገሉ የጻፉት አኩሪ የሆነ ታሪክ በኖራቸውምና አሁንም ቢሆን በተከበረና በተቀነባበረ ሁኔታ የሰፊውን ሕዝብ ገበታዊ አንቀሳቃሹ ከዳር እስከዳር አስተባብረው የሚመሩበትና በዚህም ታሪካዊ አብዮታዊ ግዳጃቸውን በሚገባ የሚወጡበት ድርጅታዊ ዱላ ገና አልተቀዳጁም :: የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከገቡ መድረስ አንድ ግንባር ቀደም የሆነ የወዛደር ፓርቲ፣ በዚህ ፓርቲ የሚመራ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር እንደሚያስፈልገው እሙን እንደመሆኑ መጠን ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮታውያን እነዚህን የአብዮቱ ጥያቄዎች አሟልተው ለወሳኙ ድል ብቁ ሆነው እንዲገኙ ከፍተኛ መስዋዕትነት፣ ታታሪነትና ተጋድሎን የሚጠይቃቸው አደራ ከፊታቸው ተደቅኖ ይገኛል ::

ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች ከየካቲት °66 አብዮታዊ ማዕበል ድንጋጤ ተላቀው ነፍስ ዘርተው በውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ኃይላቸውን አስተባብረው አብዮታችን በፋና የሚፈታተኑበት ወቅት ነው :: እነዚህ አድሀሪ ኃይሎች በአብዮቱ ወደፊት መገፋት የተነሳ እየከረሩ ከመሄዳቸውም በላይ ጥቃትን ልዩነታቸውን አቻችለው ፀረ አብዮት ግንባር ፈጥረዋል :: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይህንን ሁኔታ ተገንዝቦ ድርጅታቸውን በድርጅት ትጥቃቸውን በትጥቅ እስካልተጋፈጠ ድረስ፣ ለዘመናት ከጉኑ ቆሞ ለክብሩና ለነፃነት በሚያደርገው ትግሉ የመራት አብዮታውያን ለዚህ አዲስ አደራ ራሳቸውን ብቁ አድርገው ሰፊውን ሕዝብ ብቁ እስካላደረጉት ድረስ የኢትዮጵያ አብዮት አስተማማኝ የሆነ ፈር ይይዛል ማለት አይቻልም ::



ይህ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በፊደጅ በፋርኛ በየደረጃው አደራጅቶ አስተባብሮ ወደድልና ወደ ነፃነት የመምራት ታሪካዊ ግዴታ ከማንም ይልቅ በኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ትከሻ ላይ የሚወድቅ ግዴታ ነው ::

በኢትዮጵያና ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶችና ግለሰቦች ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ የቀኝ አድርባይነትና "የግራ" አድርባይነትን በጥቀን ሕዝቦች ፊት እያጋለጡ፣ በጊዜው፣ ከትግሉ ሂደትና ከአብዮቱ የሚገናዘቡ መፈክሮችን እያነሱ በግንባር ቀደምነት የተሰለፉበትና ሰፊውን ሕዝብ ያሰለፉበት፣ የተቀጣጡና ሰፊውን ሕዝብ ያቀጣጡበት አኩሪ የሆነ ታሪክ አላቸው :: ነገር ግን በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጉዳና ላይ ወሳኝ ለሆነው ድል የሚያበቃቸውን የወዛደር ፓርቲ እንዳለመሠረቱ፣ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር አቀናጅቶ አስተባብሮ በቀንደኛ ጠላቶች ላይ የሚያሰልፍበት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርን ገና ያላስተባበሩ መሆናቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ :: ይኸ ብቻ አይደለም :: የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ወደወዛደር ፓርቲ ወደሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር በሚደረገው ጉዞ ላይ የምታሰፈው አያገናኙ ቀን በድርጅትና በትጥቅ ቀድመው ለሄዱት አድሀሪያኖች የቀለበሳ ፋታ የምትሰጣቸው መሆኗንም ተገንዝበው ኃይላቸውን በሙሉ አስተባብረው ወደዚህ ግብ ባፋጣኝ ማምራት የአብዮቱ የሞት ወይም የሽረት ጥያቄ መሆኑን ይገነዘቡታል ::

ስለሆነም እስከዛሬ ድረስ በሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ውስጥ በግንባር ቀደምነት ተሰልፈው የሚታገሉ ማርክሲስት ሌኒኒስት ጓዶች በአብዮታዊው ትግል እሳት ውስጥ ለመገናኘት፣ ለመተዋወቅና ለአብዮቱ ሂደት ለመወያየት በቀተው የጊዜው ዋና ጥንድ ተግባሮች የወዛደሩን ፓርቲ መፍጠርና ለሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ድርጅታዊ መሠረት መጣል መሆኑን ተገንዝበው በዚህ አቅጣጫ የኢትዮጵያን ተራማጅ ኃይሎች ሰብስበው ትግላቸውን ማስተባበር እንዳለባቸው ተስማምተዋል ::

እነዚሁ ቡድኖች በማለትም የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/ የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል /ኢጭአት/ የወዝአደር ሊግ /ሊግ/ አብዮታዊ ሰደድ /ሰደድ/ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት /ማሌሪድ/ በመሀከላቸው ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሰፊ ውይይት ካካሄዱ በኋላ አብዮትን በሚመለከቱ አበይት ጥያቄዎች ላይ የጋራ አቋም በመውሰድ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎችን ሰብስበው በሕብረት ለመታገል አንድ የጋራ መርሀ ግብር አውጥተዋል ::

## ፲፭. የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዋና ዋና ቅራኔዎችና የጊዜው ሁኔታ

የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ አውተብትበው አስረው ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በድንቁርና በበሽታ በድህነት ፍዳውን ሲያስቆጥሩና ሲበዘብዙት የቆዩት ቀንደኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መሆናቸው ተደጋግሞ የተነገረ ሀቅ ነው :: እንደዚሁም በመሆኑ በዚች በከፊል ፊውዳልና በከፊል ካፒታሊስት ቅይጥ ሥርዓት ውስጥ ታስራ በተያዘች አገር ሊደረግ የሚችለው አብዮት ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት የሚመሠርት ለሶሻሊስት ሥርዓት መሸጋገሪያ መሠረት የሚጥለው ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ነው ::

ዛሬ በተለይ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. ወዲህ አቀጣጥሎ በሚያካሂደው የተፋፋመ አብዮት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚሁ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጉዳይ ላይ የማይናቁ ድሎችን ተጎናጽፏል :: የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዋና ዋና ይዘት መሬትን ለአራሹ ማደላደል፣ ታላላቅ ባንኮችን ኢንሹራንሶችን፣ ኢንዱስትሪዎችንና የማምረቻ የማከፋፈያ ድርጅቶችን ከመንግሥት ቁጥጥር ስር ማድረግ፣ ኢኮኖሚውን ከኢምፔሪያሊስቶች ቁጥጥር ስር አላቅቆ በማዕከላዊ ፕላን የሚመራ ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ መገንባት፣ የሰፊውን ሕዝብ ሰብዓዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማረጋገጥ፣ በኢምፔሪያሊዝምና በፊውዳሊዝም መቃብር



ላይ በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነት በአርሶ አደሩ ተባባሪነትና በንዑስ ከበርቴው ግራ ክንፍና በሌሎች ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ድጋፍ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ነው ::

ከላይ እንደተጠቀሰው ለዚሁ ዓላማ የአብዮቱን ወዳጆች በሙሉ አደራጅቶ አስተባብሮ ወደመጨረሻው ድል የመምራቱ ጉዳይ ገና አስተማማኝ የሆነ ፈር ባይዝም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቃት፣ በድርጅትና በትጥቅ ትግሉ ገፍቶ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ወደሕዝባዊነት ዲሞክራሲያዊነት ኢትዮጵያዊ ወደሶሻሊዝም ተቃርቧል :: በዚሁ አገባብ ደግሞ ቀንደኛ ጠላቶች በረድፍ በረድፍ ተደራጅተውበት ኢዲዩ፣ ኢህአፓ ኢሌሌፍ ብለው ራሳቸውን ሰይመው በአካባቢው አድሀሪ መንግሥታትና በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት እስካሁን የተቀዳጃቸውን ድሎች ሊነጥቁት መልሰውም ከዚያ ከሰው በላ ሥርዓት ውስጥ ሊጨምሩት ኃይላቸውን አስተባብረውበታል ::

ነገር ግን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአብዮቱ ሂደት ጋር እየተጋለጡ ርጃቸውን ከቀሩት ጠላቶች ጋር በገጠር በከተማም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያደርገው ትግል ይበልጥ ተፋፋመ እንጂ በዚሁ በአድሀሪዎች የተቀነባበረ ሴራ አልተፈታም ::

በገጠር ቅስቀሳቸው የተከበረ የመሬት ከበርቴዎች ከነሱም ጋር በሺህ የጥቅም ክሮች ተወሳስቦ የታሰረው ቢሮክራሲ ጋር በመመሳጠር ተራማጅ የገበሬ ማኅበራት መሪዎችን ያሳስራሉ፣ ያስገድላሉ፣ በብሔረሰብና በሃይማኖት ያሉትን መለስተኛ ቅራኔዎች ያባብሳሉ :: በተወናበዱ ሪፖርቶች መንግሥት ፀረ ሕዝብ ርምጃዎችን እንዲወስድ ይገፋፋሉ :: ቀን የሆኑ በዚሁ ፀረ አብዮት ሴራ ተባባሪነትን የማያሳዩ አስተዳዳሪዎችና የመንግሥት ሠራተኞችን ... በልዩ ልዩ ወንጀል ከሥራ ያባርራሉ :: ከዚህም አልፈው በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ በኢምፔሪያሊስቶች በአድሀሪ አረብ መንግሥታትና በሶማሌ መንግሥት ድጋፍና

አስተካካሪነት ደፋ በሆነ አመጽ ተነሳስተው ከመለዮ ለባሾች ከጭቁኑ ገበሬ ጋር ከፍተኛ ውጊያ በማካሄድ ላይ ናቸው ::

በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነዚህ በልዩ ልዩ አቅጣጫ አድሀሪያት የሚሰነዝሩቸውን ሴራዎች እየተቋቋመና እያከሸፈ በንቃት በድርጅትና በተጥቅ ወደፊት እየገሰገሰ ነው :: በገጠሪቱ ኢትዮጵያ 22 000 የገበሬ ማኅበራት ተቋቁመው በሰፊው ሕዝብ በነሱ ስር እየታገለ የየካቲት 25 ቀንን የመሬት አዋጅ ከሥራ ላይ እያዋለና አዲስ ኑሮውን እየገነባ ነው :: ከአድሀሪያት በሚያሰነዝሩት ጥቃት ራሱን እያስጠበቀ በመታገሉ ገጠሩን ለአብዮቱ ያቆመ አካባቢ አደርጉታል ::

በዚህም የተነሳ አድሀሪ ኃይሎች ምንም እንኳን በገጠር ትግላቸውን ቢያፋፍሙም የቀለበሳ ተስፋቸውን ያገጠለጡት በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ ላይ እንደሆነ ግልፅ ነው :: ከተሞች ከገጠር የተከረፉ አድሀሪያት የመሸሸጊያቸው ናቸው :: ከተሞች ቢሮና መሬት የተወረሰባቸው ከበርቴዎች የሚገኙባቸው ናቸው :: ከተሞች በአብዮቱ ላይ ሴት ተቀን የሚያሰረው ቢሮክራሲ ቀንጮ የተከገበገበባቸው ናቸው :: ከተሞች የነዚሁ ፀረ ሕዝቦች ሁሉ ልጆች በት/ቤቶች ተሰግስገው የሚያውናብዱባቸው ናቸው :: በእነዚሁና በሌሎች በብዙ የተከበጠጠሩ ምክንያቶች የተነሳ በጊንበር የተባለው የአሜሪካን በለይ እንደ ዳ ገረው ከተሞች የአድሀሪ ኃይሎች ቁጥ ተከማችተው የሚገኙባቸው ለቀለበሳ የሚያመቹ አካባቢዎች ናቸው ::

ነገር ግን በከተሞችም ከጥቂት ወራት ወዲህ የሰፊው ሕዝብ ንቃትና ድርጅት እየዳበረ በመሄዱ የአድሀሪያትን የተቀነባበረ ሴራ ለመቋቋም አመቺ የሆነ ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ይቻላል :: ኢሀአፓ የተባለው የግልገል ፋሽስቶች ድርጅት ከጥቂት ወራት ወዲህ ሙሉ በሙሉ ተጋልጦ ከወዝአደሩ አካባቢ ተፍቷል :: ከፀረ አብዮት ኃይሎችም የፀና የመሰ



ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ከረጅም ጊዜ የተወሳሰበ ትግል በኋላ ተቋቁሟል :: የከተማ ማኅበራትን ከፀረ አብዮት ኃይሎች ለማጽዳት የተደረገው ዘመቻ ከሞላ ጎደል በመጠናቀቁ በከተሞች በዙ ተራማጅ የሆኑ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ተቋቁመዋል :: በአርሶ አደሩና በወዝአደሩ በመቀላቀሉም በሰፊው ሕዝብ ተፋቶ ርቆ የቀረው ኢሀአፓና የተቀሩት አድሀሪ ኃይሎች ዛሬ የመጨረሻ ምሽግ አድርገው የያዙትና ሊሟሟቡትም ቆርጠው የተነሱት በት/ቤቶች አካባቢና በቢሮክራሲው አካባቢ በቀራቸው ምሽጋቸው ነው ::

ፀረ አብዮት ኃይሎች በዚሁ መስክ ከጥቂት ወራት ወዲህ የደረሰባቸውን ኪሣራ ለመሸፈኛ አብዮቱን ለመቀልበስ የሚያደርጉት ሙከራ የሰርጎ ገብነት ዘመናቸው ማክተሙን ተረድተው ደፋ በሆነ አመጽ በአብዮቱ ላይ ማስነሳት መሆኑን በመገንዘብ በከተሞች ሽብር የመፍጠር ዘመቻ በማፋፋም ላይ ናቸው :: ይህ የአድሀሪያቶች የሽብር ፈጠራ ዘመቻ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ መሽገው ያሴሩ በነበሩ ጥቂት የውስጥ አርበኞች ድጋፍና ከፍተኛ ዕርዳታ ሲካሄድ ስለነበረ የሰፊው ሕዝብ የትግሉና የቢሮክራሲ ጥያቄዎች ባይመለሱም ቆርጠው አብዮታችን በተከላካይነት ደረጃ ተወስኖ ቆይቷል :: የነዚሁ ፀረ ሕዝብ የውስጥ አርበኞች ፋሽስታዊ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከከሸፈ በኋላ ግን የዲሞክራሲና የትግሉ ጥያቄ ባፋጣኝ የሚመለስበት ጥርጊያ ጎዳና በመከፈቱ አብዮቱን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ደረጃ ለማሸጋገር አመቺ ሁኔታ መፈጠር ላይ ነው ማለት ይቻላል ::

በዓለም አቀፍ ደረጃም የኢትዮጵያ አብዮት አድሀሪያትና ኢምፔሪያሊስቶች የጣሉትን በተገቢ በቻይነት በመሰባበር ዛሬ የዓለም ጭቁን ሕዝቦች አብዮት የሚደነቅበት አካል መሆኑ ተረጋግጠለት፤ ለአፍሪካና ለአካባቢው አገሮች የነፃነት ተጋድሎ የሚያደርገው የማይናቅ አስተዋጽኦ ታውቆለት የአፍሪካ ተራማጆችና ጭቁን ሕዝቦች፤ የአካባቢው ተራማጆች በሶሻሊስት አገሮችና የዓለም ተራማጆች ያቀፉትና የደገፉት አብዮት ሆኗል :: ስለ በዚሁ አንፃር ደግሞ የውስጥ አድሀሪያት፤ ምስሉነቱን የፈረ የጎረቤት አድሀሪያት ዓለም አቀፍ

ኢምፔሪያሊዝም በተቀነባበረ ሴራ ሊያጠፋት የሚያሴሩበት የከበበ አብዮት እንደሆነ ግልፅ ነው ። እንዲያውም ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀነባበረው ፀረ አብዮት ሴራ በኢትዮጵያ በሜዳ ላይ የቺሊን የመሰለ የቀለበሳ አደጋ እንዲያጋጥመው አድርጎ እንደ በርና ሊያደርግ እንደሚችልም ለማንም ግልፅ የሆነ ሀቅ ነው

እንግዲህ በዚህ በአንድ በኩል የአብዮቱ ኃይሎች ነቅተው ተደራጅተውና ታግለው ለአብዮታችን ያመቻቸ ሁኔታ ላይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ አብዮት ኃይሎች ተደራጅተውና ታግለው ኃይላቸውን አስተባብረው አብዮቱን ለመቀልበስ ከፍተኛ ያሰፈሰፉበት እጅግ የተወሳሰበና የተፋፋመ የትግል ወቅት ላይ እንገኛለን ። በሁሉም ወገን የሚደረገው መፎካከርና መሰናዶ ሲታይ ወሳኙ የሆነው ፍልሚያ ገና ከፊታችን እንደሚጠብቀን ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገኝበት የንቃት የድርጅትና የትጥቅ ደረጃ አብዮታችንን ከቀለበሳ ተከላክሎ የማያወላውል ፈር ለማስያዝ የሚያስችለው አይደለም ። የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ይህንን ሀቅ ጠንቅቀው በማወቃቸው አብዮትን ወደፊት ለማራመድ አማራጭ የሌለውን የወዛደሩ ፓርቲ ለመመስረት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩ መሠረት መጣል የተራማጆችን ሕብረት መፍጠር የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጡት የአብዮቱ አመራር ታሪካዊ ኃላፊነት የተጣለበትን የወዛደር ፓርቲና በሱ የሚመራውን ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመስረት በነዚህ እጅግ በተከበሩ ጥንድ ተግባሮች ዛሬ ነገ ሳይሉ መስማራት እንዳለባቸው ያምናሉ ።

2ኛ. <u>ስለወዛደሩ ፓርቲ አመሠራረት</u>

የወዛደሩን ፓርቲ መስርቶ አብዮትን በግንባር ቀደምነት መምራት የአብዮቱ አበይ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ይህ ፓርቲ በሚመሠረትበት ሁኔታ ላይ አምስቱ ድርጅቶች ጋር ታክቲክ ቁሰዋል ። እንደሚታወቀው በአንድ አገር ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ



ከመፈጠሩ በፊት የሚታገሉት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ እያስገደዳቸው ማርክሳዊ ቡድኖች ሳይተዋወቁና ሳይተባበሩ በየፊናቸው ይደራጃሉ ። ከእነዚህ የተለያዩ ቡድኖች በምን ዘዴ የወዛደር ፓርቲ ሊመሠረት ይችላል ለሚለው ጥያቄ የብዙ አገሮችን የአብዮታዊ ትግል ታሪክና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርመር ከተለያዩ የወዛደር ፓርቲ አመሠራረት ዘዴዎች ፍቱንና ሳይንሳዊ የሆነው ዘዴ ልዩ ልዩ ማርክሳዊ ቡድኖች ኃይላቸውን አስተባብረው፣ የትግል አንድነት መስርተው፣ በመሀከላቸው በታክቲክና በስትራቴጂ ጥያቄዎች ላይ ሀቀኛ የሆነ የርዕዮት ዓለም ትግል እያካሄዱ የሚዋሃዱበት ዘዴ መሆኑን አምነውበታል ።

በኢትዮጵያ ሁኔታ አሁን በሕቡዕ የሚታገሉት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ቡድኖችና ሌሎችም በትግሉ ውስጥ የፈጠሩ ቡድኖች ተዋህደው እንጂ አንድ ድርጅት ብቻውን ተስፋፍቶና አድጎ ወይም ደግሞ ከውስጡ ፀረ ወዛደር የሆኑ ኃይሎችን አጽድቶ ብቻውን ወደወዛደር ፓርቲነት የሚለወጥበት ሁኔታ የለም ።

3ኛ. <u>የዲሞክራሲ ጥያቄ</u>

በመደቦች በተከፈለ ማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ዲሞክራሲ ለአንዱ መደብ ነፃነት በሌላው መደብ ላይ ደግሞ ባርነትን የሚያጸድቅ ዲሞክራሲ እንጂ ለጠቅላላው ሕብረተሰብ እኩል ከሥራ ላይ የሚውል ዲሞክራሲ እንደሌለ ተደጋግሞ የተነገረ ሳይንሳዊ ሀቅ ነው ። ስለሆነም አብዮታውያን የዲሞክራሲያ ጥያቄ ከመደቦች ትግል ለይተው አይመለከቱትም ። የዲሞክራሲ መብቶችን የሚታገሉላቸው የተያያዙትን የነፃነት ትግሉን ለማፋፋም እንዲረዷቸው ስለሆነ እነዚህን መብቶች በትግል ይጎናጸፏቸዋል ። ለትግል መሣሪያ ያደርጓቸዋል ። የትግል መሣሪያ እንደመሆናቸው መጠን፣ ከመደቦች ትግል አንፃር እንደሚመለከቷቸው ሁሉ አብዮታውያን የሚታገሉት ለጠላት መደቦች ለሚሆን ዲሞክራሲ ሳይሆን ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ብቻ የሚውሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ነው ።

በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሀሪያን በበለጠ ለመቋቋም በስወር ታፍነው የሚሠሩ ተራማጅ ድርጅቶች ትግላቸውን በሰፊ ለማካ ሄድ እንዲችሉና በተለይ ደግሞ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመስረት የሚያስችሉትን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲያቸውና በሰፊ ድርጅቶች ለማቋቋም እንዲችሉ ባስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው ። ለዚህም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒ የጋራ ትግል ያደርጋሉ ።

4ኛ. የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ

የማንኛውም አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ነው ። የኢት ጵያም አብዮት ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በሚገባ እንደተገለጸው ፀረ ፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ በወዝአደሩ መሪነት በአርሶ አደሩ አጋር ነትና በንዑስ ከበርቴው ተባባሪነት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ማቋቋም ነው ። በሰ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደዚህ ሕዝባዊ ሥልጣን በሚያደርገው ጉዞ የሚከተለው ፋና የጎታት የድርጅትና የትጥቅ ትግል መሆኑ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በሙሉ የተቀበሉት እምነት ነው ። አድሀሪ ኃይሎች በውዴታ ሥልጣንን ለሰፊው ሕዝብ ያስረከቡበት ወቅት በታሪክ ስለሌለ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ ለሚገነባው ሕዝ ባዊ ሥልጣኑ የሚከተለው ጎዳና የሕዝባዊ አመጽ ጎዳና ይሆናል ። ስለሆነም ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የወዝአደሩን ፓርቲ መስርተውና ሕዝባዊ ግንባሩን አስተባብረው በአመጽ ድሉን ለመጎናጸፍ ማንኛውንም ዝግጅት ማድረግ አለባቸው ።

5ኛ. ስለመለዮ ለባሹ ሠራዊት

የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ከየካቲት ጀምሮ ከጭቁን ሕዝቦች ጎን በመሰለፍ በት ግሉና በመስዋዕትነት የሳፉት አኩሪ ታሪክ አላቸው ። በመጭውም ትግል ለመጨረሻው ድል



የሚያስፈልጉት ነገሮች የወዝአደር ፓርቲ ሕዝባዊ ግንባር ብቻ ሳይሆን ሕዝባዊ አብዮ ታዊ ጦር እንደሚያስፈልግ ሁሉ ይህንን ሕዝባዊ አብዮታዊ ጦር ከወዝአደሩ፣ከአርሶ አደሩ፣ ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎችና አሁን ካለው መለዮ ለባሽ ለአብዮቱ ከሚቆመው ወገን ማቋቋም የሚቻልበት ሁኔታ አለ ። አሁን ያለው የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ በመደብ ምንጩ ከደሀው ገበሬ እንደመሆኑ መጠን ከውስጡ የሚገኙትን ፀረ አብዮት ኃይሎች በማጽዳት ከሠራዊቱ ይበልጡን ወደሕዝባዊው አብዮታዊ ጦር ለመሳብ መጣር የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ተግባር መሆን አለበት ። የቆየው የፊውዳል ቡርዧዋ ሚሊታሪ ቢሮክራሲ እንዳለ ለአብዮቱ መቆም እንደማይችል ተገንዝበው ይህ ቢሮክራሲ እንዲሰበር መታገል ይኖርባቸዋል ።

6ኛ. ስለብሔረሰቦች ጥያቄ

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ የታሪክ ዕድገት ደረጃ ሲመረመር ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከብሔር ነት ደረጃ የደረሱ ሕዝቦች እንደሌሉና ብዙ ብሔረሰቦች እንደሚገኙ ግልፅ ነው ። በነዚህ ብሔረሰቦች መሀከል በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ቅራኔዎች አሉ ። የማርክሲዝም ሌኒ ኒዝም መርህ አበጥሮ እንደሚያስረዳን በመደቦች በተከፋፈለ ሕብረተሰብ መሠረታዊው ቅራኔ በመደቦች መሀከል ያለው ቅራኔ እንደመሆኑ መጠን በብሔረሰቦች መሀከል ያለው በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ቅራኔ ነው ።

ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተሉት ሳይንሳዊ አቋም ከጭቁኖች አንድነት ጋር የሆኑት የብሔር ትምክህተኝነትና የጠባብ ብሔርተኝነት የሚቃወሙትን የሚ ያገነት አቋም ነው ። ለዚህም በአንድ በኩል የእያንዳንዱን ብሔረሰብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ የሚጨምር መብት አውቀው በሌላ በኩል ደግሞ ብሔ ረሰቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ከብረት የጠነከረ አንድነት እንዲመሠ ርቱ ይታገላሉ ። ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ይህንን መርህ ይቀበላሉ ።

ነገር ግን መርሁን ተከትሎ ለአለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ መፍትሔ ማለትም "ሪፎርሚስ ስትራቴጂን" አብረን ማቅረብ አለብን በሚልና ለጥያቄው በቅድሚያ አጠቃላይ መፍትሔ አሁን ከማቅረብ መርሁን ብቻ አውቆ ለእያጋጣሚው በሚነሳ ችግር እንደ የሁኔታው መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል በሚሉ ወገኖች መሀከል ስምምነት ያልተደረሰ በመሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይ ለመድረስ ሰፊ የሆነ ውይይትና ክርክር ለማድረግና ወደጋራ አቋም ለመድረስ ቡድኖቹ ተስማምተዋል ::

ከላይ እንደተገለው የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በግንባር ቀደምነት በተሰለፉበት የነፃነት ትግሉ ሰፊውን ሕዝብ አስተባብረው ወደወሳኙ ድል ለመምራት ባላቸው ኃላፊነት መሠረት በመሀከላቸው የተሟላ ሕብረት ፈጥረው በትግልና በጠራ አብዮታዊ መስመር ላይ ለመዋሀድና የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረት በኢትዮጵያ የሚገኙትን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በየደረጃውና በየፈርጃቸው አስተባብረው ሕዝባዊ ግንባር ለመመስረት በጋራ ለመታገል ተስማምተዋል :: በዚህም መሠረት በ15 ነጥቦች በተዘረዘረው መርሀ ግብር መሠረት ትግላቸውን ለማስተባበር ወስነዋል ::

## የጋራ መርሀ ግብር

1. የኢትዮጵያ አብዮት ግቡን የሚመታው በወዛደሩ ፓርቲ በሚመራ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ኃይሉን አስተባብሮ ሲታገል ብቻ በመሆኑ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች በፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት መድረክ ላይ ተባብረው እንዲታገሉ ለማድረግና ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በሕብረት ከመታገል አልፈው በመዋሀድ የወዛደሩን ፓርቲ እንዲፈጥሩ መታገል ::



2. ይህንን የሰፊውን ሕዝብ መንቃትና በየፈርጁና በየደረጃው መደራጀት በማገዝ አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ እንዲለቀቁ በሕብረት መታገል ::

3. ሰፊው ሕዝብ አሁን የደረሰበትን የንቃትና የድርጅት ደረጃ አድሀሪ ኃይሎች በትጥቅ እየተፈታተኑት ስለሆነ ይህንን መክቶ ይበልጥ እንዲነቃ ይበልጥ እንዲደራጅ አሁን ባለበት የንቃትና የድርጅት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ ትጥቅ እንዲያገኝ መታገል ::

4. ከኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ብዙኃኑ በአብዮቱ ሰፈር የቆሙና የጸኑ በመሆናቸው በሠራዊቱ ውስጥ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም እንዲስፋፋ፣ የግራ ክንፍ ኃይሎች እንዲጠናከሩ፣ በውስጡ ያለው የሚሊታሪ ቢሮክራሲ እንዲዳከም መታገል ::

5. በወዛደሩ አካባቢ

በየፋብሪካውና በየማከፋፈያ ድርጅቶች በተካሄደው የከረረ ትግል በአያሌ ፋብሪካዎች ሀቀኛ የሆነ የማኅበር አመራር ያለውና በቅርቡ የተቋቋመው የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር በተመሰከረ አመራር ተመስርቷል :: ድርጅቱ የሙያ ማኅበር ጠባይ ያለው ቢሆንም ለወዛደሩ የፖለቲካ ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ስለሚችል በየደረጃው የተመሠረቱትን የወዛደር ማኅበሮችን ለማጠናከር ሰፋ ያለ የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማካሄድና የውይይት ክበቦች የአብዮታዊ ንቃት መድረኮች እንዲሆኑ ለመታገል በወዛደሩም ድርጅት ውስጥ የጥናት ጓዶች እንዲመሠረቱ እንዲስፋፉና እንዲታጠቁ በየደረጃው የኢህአፓ ኢዲዩ ቅጥረኞችን ወርስ ለመመንጠርም መታገል ::

6. <u>በገበሬው አካባቢ</u>

የንቃት ቀስቃሾችን ለማስፋፋት፣ ማኅበራትን ከአድሀሪና ሀብታም ገበሬዎች ለማንፃት፣ አድሀሪያንን ትጥቅ ማስፈታትና የመሰበሰቡትን አብዮታዊ ርምጃዎች በራሳቸው እንዲወስዱ ለማገዝ፣ ከአድሀሪው ቢሮክራሲ ጋር ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ለመቀስቀስና የገጠርን ኢኮኖሚ ለማዳበር የመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር እንዲቋቋም ይታገላሉ ።

7. <u>በወጣቶች አካባቢ</u>

ወጣቶች የሕብረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው ሁሉ፣ እንደቤተሰቦቻቸው የመደብና የፖለቲካ አቋም፣ የተለያዩ ሚና ይጫወታሉ ። የፖለቲካ አቋማቸው የጠራ አብዮታዊ ወጣቶች ለትግላችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ኃይሎች ናቸው ። ወጣትን ወደ አብዮት ሰፈር ለመሳብ ከወዝአደሩና ከደሀ ገበሬው በይበልጥ እንዲዋሀዱ፣ በትምህርትና በምርት ላይ እንዲያተኩሩ ሰፋ ያለ ቅስቀሳ ማድረግ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚካሄደው ትግል ተጠናክሮ የኢዲዩና የኢህአፓ ርዝራዦችን ፈጽሞ ለመደምሰስ ታጋይ ወጣቶችን በንቃትና በድርጅት በትጥቅ ማገዝና ወጣት ወዝአደሮችና ተማሪዎችን የሚያቅፍ የኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር የሚቋቋምበትን ሁኔታ ለመፍጠር ።

8. <u>በሴቶች አካባቢ</u>

በመደብና በጾታ ተጨቁነው በገጠርና በከተማ የሚኖሩትን ጭቁን ኢትዮጵያውያት ከመደብ ጠላቶቻቸውና ከወንድ ትምክህተኝነት ጋር የሚያደርጉትን ትግል ለማገዝ ጠንካራና አብዮታዊ የሆነ መላ የኢትዮጵያ ጭቁን ሴቶች የሚወክል ድርጅት ለማቋቋም የሚደረገውን የአብዮታዊ ሴቶች ትግል ማገዝ ።



9. በቢሮክራሲው አካባቢ አድሀሪ ቢሮክራቶችን ማጋለጥና መታገል፣ ተራማጅና ዲሞክራት ኢትዮጵያውያን የኃላፊነት ቦታ እየተሰጣቸው ለአብዮቱ አገልግሎታቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ ።

10. የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሶሻሊስት አብዮት የማይነጠል አካል እንደመሆኑ ሁሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ወዳጆችና ጠላቶች እንዳሉት ግልፅ ነው ። በዚህም መሠረት ከውስጥ በአድሀሪ ኃይሎች የሚበረበረው አብዮታችን ከውጭ የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች ከበውት ሊቀለብሱት ኃይሎቻቸውን በማቀነባበርና በማስተባበር ላይ ይገኛሉ ። በዚህ አንፃር ደግሞ የኢትዮጵያ አብዮት የአፍሪካ ተራማጆችና ጭቁን ሕዝቦች፣ የሶሻሊስት አገሮችና የመላ ዓለም ተራማጆች ያቀፉትና የደገፉት አብዮት ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ተራማጆች በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ተራማጅ ኃይሎችና ከሶሻሊስት አገሮች የጠበቀ ግንኙነት ለመመስረት፣ ኢምፔሪያሊዝምና በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ለማጋለጥና ለመዋጋት መነሳት ።

11. በነዚህና በየጊዜው በአብዮቱ ሂደት ላይ የሚመጡ አዳዲስ ሁኔታዎች እየተመከሩ የጋራ አቋም ለመውሰድና በጠባብ ድርጊቶች ላይ የጋራ ክንዳቸውን ለማንሳት ።

12. ይህንን የጋራ አቋምና የጋራ ትግል ታክቲክ ከሥራ ላይ ለማዋል ለሚደረገው ቅስቀሳ ይረዳ ዘንድ አንድ በየጊዜው የሚወጣ የጋራ ልሳን ለማውጣት ።

13. ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ከሥራ ላይ የሚውሉበትንና ሕብረት እየተጠናከረ የሚሄድበትን ጥርጊያ ጎዳና ለመጥረግ ምቹ የሆነ አንድ ከየቡድኖቹ የተውጣጣ የጋራ ኮሚቴ ለመመስረት ከላይ የተጠቀሱት አምስት ድርጅቶች ተስማምተዋል ።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ አብዮታውያን ከላይ በተጠቀሰው መርህ ግብር መሠረት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች በሕብረት ወደውህደት ተሸጋግረው የወዛአደሩን ፓርቲ እንዲመሠርቱ፣ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች ደግሞ ተባብረው የሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ጽኑ መሠረት እንዲጥሉ አብዮታዊ ተግሳጻችንን እናካሄዳለን። በዚህ መርህ ግብር ተስማምተው ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ነፃነት፣ ለአብዮታዊት እናት አገራችን አንድነት፣ ክብርና ሕልውና በግንባር ቀደምነት ተሰልፈው ለመታገል ለሚሹ ኃይሎች ሁሉ የሕብረት እጃችንን ዘርግተን የትግል አንድነታችንን እንደናጠነክር አብዮታዊ ጥሪያችንን እናቀርብላቸዋለን። ተራማጆች በሙሉ በሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር አማካኝነት ኃይላቸውን ማስተባበራቸው ማርክሲስቶች በሕብረት ደረጃ ተሸጋግረው የግንባር ቀደምነት ታሪካዊ አደራ የተጣለበትን የወዛአደር ፓርቲ መመስረታቸው የአብዮታችን ወሳኝ ጉዳይ የሚጠይቀው አጣዳፊ ተግባር በመሆኑ አብዮታውያን በሙሉ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በቀልጥፍና መወጣት ይኖርባቸዋል። በመላ ኢትዮጵያ ሰሸሌብት ገፍና ቹ፣ በኢትዮጵያ ጭቆኖች አብዮታዊ ትግል፣ ሰወዛአደር ሊግ በአብዮታዊ ሰደድና በማርክሲዊ ሌኒ ዊ ሪቮሉሽና ዊ ድርጅት ስር የተደራጁት አብዮታውያን ያላቸውን ኃይል በሙሉ በማስተባበር ለዚህ ታሪካዊ ግዳጅ ተሰልፈዋል። ሌሎች አብዮታውያን የነሱን ዓላማ በመከተል የተፋፋመውን አብዮት ወደወሳኙ ደረጃ ለማምጣት በሚደረገው ታሪካዊ ትግል ከነትፉቸውን እንዲያስተባብሩ አብዮታዊ ጥሪ ያቀርብላቸዋል።

የወዛአደሩን ፓርቲ ባስቸኳይ እንፍጠር

በሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር የፀረ ሕዝቦች
ግንባር ይደመሰሳል

የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል ያሸንፋል!

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

0156/2223 60
60

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጩን ጥቃትና ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከጥቅና ቋያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ደዎሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚሁ አስር ዓመታት ያለተሰጣቸውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፣ከየትኛውም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል።። የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው።።እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ውዥንብር በመገዛት ለማፋፋም ነው።።ይህም አገደማይባካ የተረጋገጠ ነው።። ለማንኛውም፣የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣ የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የሚያመለክት ግን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንዲታወቁልንና እንዲታስታውቁልን እንጠይቃለን።።ለእነዚሁ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው "ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን" በሚባል ስም የታወቀው የነ አስፋወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው።።

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ